በፍቅር፤በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንዳፍታ



ትሁት ዘመድአገኘሁ



ዮዲት ሰብስቤ



በተጠለፈው አይሮፕላን
ህይወታቸው ያለፈው
ሆስቴሶች
3ቱም የናዝሬት ት. ቤት
ተማሪዎች ነበሩ።

ጽጌረዳ
እስጢፋኖስ


ህዳር / ታህሣስ
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት
ቁጥር ፫


# LANDAFTA


An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
Nov/Dec 1996
Vol.5 No.3

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በጎደሎ ፊደላት ማንኛውም ፎንት የሚቀበል የዊንደውስ ፕሮግራም ውስጥ በማንም ፎንት ለመጻፍ ግዕዝኤዲት GeezEdit $99.00 ። ኢትዮወርድ/ግዕዝኤዲት EthioWord/GeezEdit $199.00 - for use in any Windows 3.1 and Windows 95 program which allow font substitution. ግዕዝን ከዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማተምና ለመፈለጊያ ኢትዮሳይበር EthioCyber $495.00 ። (Multi-lingual hyper linked documents) ምሳሌ፡- ዐረብኛ/Arabic (جثجرغخثث) ግሪክ/Greek (Σ'Ωϱ,ϋώεϑ) ሕብራይስጥ/Hebrew (ፕ"፡ን‟ኂ) ጃፓን/Japanese (ムラモトメヤメトニ) etc. Type, publish and search Ethiopic documents on the Internet and enjoy it on Windows, Macintosh an UNIX platforms. Check out the Ethiopic pioneers at *http://www.ethiopic.com* and get **FREE** software.

### የኢትዮጵያ ኮምፕዩተሮችና ሶፍትዌር

### Ethiopian Computers and Software

**9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA**

**Fettan Graphics 1209 U St. NW, Washington, DC 20009**

Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail:*Ethiopian@aol.com* – ዶ/ር አበራ ሞላ ኢ-ሜል በግዕዝ (Ethiopic E-Mail)

# በኮምፒውተር
# የአማርኛና የእንግሊዝኛ ሥራዎች

**መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣ ወይም የተለያዩ የአማርኛ ጽሑፎችን**
**በኮምፒውተር ለማሠራት ለምትፈልጉ ሁሉ!!**

ርካሽ በሆነ ዋጋ ከጥራት ጋር ማንኛውም ዓይነት ጽሑፍ
በአስቸኳይ ለማሠራት የምትፈልጉ ሁሉ
በስልክ ቁጥር (404) 508–4657 ደውለው ገነትን ያነጋግሩ።
ጽሑፎችዎንም በፋክስ ቁጥር (404) 508–2447 መላክ ይችላሉ።
ማስታወቂያዎች፣ የትርጉም ሥራዎች፣ የመጣጥፍ ረቂቆች፣
የጥሪ ካርዶች በፈለጉት ዲዛይን እንሠራለን።
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችንም በማዘጋጀት
በአስቸኳይ በኢ ሜይል ለመላክ እንችላለን። ደውሉልን።

# ማ ውጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

7 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

17 ከአንባብያን

19 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደርን)

23 "ደበበ በችሎት ላይ"
ግጥም (ልሳኑ ስምረት)

27 ኑሮ በአሜሪካ
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!" (አትናትዮስ)
አዲሱ የዌልፌር ሕግ
"የአባትና የእናት አደራ ልጅ . . ."
(ሴንት ሉውስ ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ)

33 ልቦለድ
"የመታጠቢያዋ ሳህን" (ጌታቸው ገ.ወ.)

36 "እምነት ወይስ ክህደት" (እያዩ በልልኝ)

40 አዳምና ሔዋን
"ዕጣዬ" (አብረኸት"

42 ከአበው
ታሪክና ምሳሌዎች (መጋቤ አእላፍ መክብብ)

43 እንዳው ለምክር ያህል!

45 "እኔ የምለው!!"
ወፈር አበጥ ያለ ንቀት (ውሂብ ጥሩነህ)

47 የቃላት በሰንጠረዥ ጨዋታ






እንኳን
ለብርሃን ልደቱ
አደረሳችሁ!!




ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1996

ላንዳፍታ
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት ቁጥር ፫
LANDAFTA
NOV/DEC 1996 Vol. V- No.3

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*

**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Gebrie (Pen Name)*
*Wuhib Tiruneh*
*Eyayu Beleigne (pen name)*

**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**DISTRIBUTION**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Durham, NC
Blue Nile Ethiopian Cusine
Houston
Queen Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Emebet Worku
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል። ይኸው ደግሞ ብቅ ብለናል። ዘገየን እያልን ይቅርታ መጠየቁ ሳያሰለቻችሁ አልቀረም። ምክንያታችሁ አበዛዙ እንዳትሉን እንጂ ችግር እየገጠመን ነው።

ዝግጅታችን ሰፋ ያለ ነው። ዛሬም ትምህርት አዘል የሆነው ወርቃየሁ ከአገር ቤትና ገብርዬ ደግሞ ከአሜሪካ የሚጻጻፉት የሰላምታ ልውውጥ አለን። በዚህ እትም አንዳንድ አንባብያን ሊያውቁት ይገባል ያልናቸውን ዜናዎች አክለናል። የአውሮፕላናችን ትራጄዲያዊ ጠለፋና የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ አወዳደቅ አበይት ዜናዎች በመሆናቸው ሰፋ አድርገን ተመልክተናቸዋል።

ልሣኑ ስምረት ደግሞ በሸጋ ብዕራቸው በሳል የሆኑ ግጥሞቻቸውን ጀባ ብለውናል። መጋቢ አዕላፍ መክብብ አበውን የምናስታውስባቸውን ተረትና ምሳሌዎች አቅርበውልናል። በይቀጥላል ከሚፃፉት የገጠመኝ ታሪኮች "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ" የሚለውን የአትናትዮስን ተከታታይ ጽሁፍና የአብረኸትን "ዕጣዬ" ተከታታይ ታሪክ አቅርበናል።
እያዩ ቢልልኝ በተከታታይ በሃይማኖት ስም የሚደረገውን እሱ በቅርብ የሚያውቀውን ይነግረናል። ውሂብ ጥሩነህም የታዘበውን አስፍሮልናል።

እንግዲህ እኛ ይህን እንድትቋደሱልን ሰጥተናል፤ አንብቦና አጣጥሞ የዝግጅቱ ተሳታፊ መሆኑን ለእናንተው ትተናል።
በደህና እንሰንብት።

በዚህ አጋጣሚ ጽሑፍ የምታበረክቱልን ቋሚ ጸሐፊዎቻችንም ሆናችሁ ሌሎች በላንዳፍታ ላይ እንዲወጣ የምትፈልጉትን ጽሑፍ ቀደም ብላችሁ እንድትልኩልን አደራ እንላለን።

## እንኳን
## ለብርሃን ልደቱ
## አደረሳችሁ!!

**የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል**
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- mgessesse@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com.landafta.htm

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት ከወርቃየሁ

ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? ኑሮና ብልሃቱስ እንዴት ያደርጋችኋል? እኛ እንዳለን አለን።

ወዳጄ ገብርዬስ አንተስ እንዴት ከርመሃል? እኛ በአውሮፕላኑ አደጋ ሳቢያ ሰሞኑን ትንሽ ሐዘን ብጤ ይዞን ከረመ። መቼም ዜናውን ከእኛ የበለጠ እናንተ በደንብ ሳትሰሙትና ሳታዩት የቀራችሁ አይመስለኝም፤ በአደጋው ከ100 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ህይወታቸውን እንዳጡ በግልፅ ታውቋል። በአውሮፕላናችን ላይ የነበሩ የተለያዩ አገር ሰላማዊ ተጓዞች የአደጋው ሰለባ መሆናቸው በጣም ያሳዝናል። ለአውሮፕላናችንም ታሪክ ጥሩ አይሆንም።

ይኸው እንግዲህ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለት አውሮፕላኖች ጋይተውብናል። አንዱ በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ ሞጆ ከተማ በልምምድ ላይ እያሉ ወድቆ በመጋየቱ ለ10 ሰዎች ሞትና ለ93 ሰዎች የመቁሰል አደጋ ምክንያት የሆነው የጦር ሚግ አውሮፕላን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ይኸው የሰሞኑ በሶስት ጠላፊዎች ምክንያት ኮሞሮስ ደሴት ላይ የወደቀውና ለ123 ሰዎች ሞትና ከ50 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ከባድና ቀላል አደጋ ምክንያት የሆነው ቦይንግ 760 ይጠቀሳሉ። ወዳጄ ይኼ ሁሉ እንግዲህ ከምን የመጣ ነው ትለኛለህ? አሁንስ እግዜሩም ርቆን ነው እንጂ እንዲህ በየዕለቱ የአደጋ ዜና ሰሚ ሆነን አንቀርም ነበር። – እግዚኦ ማህረነ ክርስቶስ! ማለት የሚያስፈልገን ይሄኔ ነው።

ወንድሜ ገብርዬ!

ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? ፕሬዚዳንት ክሊንተንስ እንዴት ናቸው? እስቲ እሳቸው እንኳ በአዲሱ የስልጣን ዘመናቸው ስለአገራችን ኢትዮጵያ ደግ ደጉን እንዲያስቡ አምላክ ልባቸውን ያራራልን።

ገብርዬ! እናንተ አዲስ ፕሬዚዳንት ለመምረጥ ሽርጉድ በምትሉበት ሰሞን እኛ ደግሞ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትራችንና የመከላከያ ሚኒስትር የሆኑትን 'ታጋይ' ታምራት ላይኔን ከስልጣን መውረድ በምሳ ሰዓት ዜና በሬዲዮ ሰማን። በየቢሮአችን "ጉድ ጉድ" ተባባልን። የዛን ዕለት ስራም አልሰራንም ማለት ይቻላል፤ ሁሉም በየስርቻው መገረምም መደነቅም ይዞት ከቢሮ ቢሮ ሲንሾካሾክ አመሸ – የልብን መተንፈስ፣ ሀሳብንና አቋምን በግልፅ መናገርና ማሳወቅ በኢትዮጵያ ምድር እንደማይቻል መቼም ታውቀዋለህ። እኛ ጉድ ስንል ዋልን እንጂ የሚገርመው ግን ሰውየው "ታምራት ላይኔ" ጉድ አላሉም፣ ጫካ አልገቡም፣ ጦርም አልመዘዙም፤ "አበጃችሁ ስመከር ስመከር አልሰማ ብዬ ነው" ብለው እንባቸውን እያፈሰሱ «ሁኔታውን በፀጋ ተቀብየዋለሁ» አሉና አሳረፉን፤ እኛ አገር ተደበላለቀ! ስንል። ገብርዬ ፍርሃታችን ከምን የመነጨ መሰለህ፤ የሁለት አምባገነኖች ጠብ ጥሩ አይደለም፤ ሌላውን ሕዝብ ሊጉዳ ይችላል። "በሁለት ዝሆኖች ጠብ ምክንያት የሚጉዳው ሳሩ ነው" ያሉት ኬኒያታ ትዝ ይበሉህ። እና እኛ እንደዚያ ፈርተን አገር ተደበላለቀች ብለን ብንሰጋም ታጋይ ታምራት እንኳን ዝሆን ጥንቸልም አልሆኑ። ሰውየው በፀጋ ተቀበልኩት ይበሉ እንጂ እዚህ እኛ ዘንድ የሚወራው ብዙ ነው። በሰውየውም ምክንያት ከእሳቸው ጋር የዘርም ሆነ የሥራ ንክኪ ያላቸው ብዙ ሰዎችም ቸብ ቸብ እየተደረጉ ናቸው። ትዝ ይልህ እንደሆን ደርግ መውደቂያው ሲደርስ ግማሹን በሕመም፣ ግማሹን በጡረታ እያሳበበ ማግለል ጀምሮ ነበር። ምናልባት ይሄም የዛ ምልክት ይሆንልን ይሆን?

ገብርዬ ይሄ ሰውዬ እንዲሁ አልነበረም ለካ የሚሽቀረቀረው? የታሰረን ወቃሽ አያድርገኝና ያኔ በደርግ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ፍቅረስላሴም እንዲሁ በሽቅርቅርነቱ ምክንያት የሚታማ ነበር። እነዚህም እንደዚሁ። አንዱ ጓደኛዬ ለመሆኑ እኒህ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ አካባቢ ያሉ ሰዎች (ለጊዜው አቶ መለስን አይመለከትም) ገንዘብ ያትማሉ ወይስ ሜርኩሪ ይነግዳሉ ብሎ ቢጠይቀኝ – ወዳጄ እሱን አብረን እንጠይቃለን በሰላም ልኑርበት ብዬው ነበር ያኔ! ስለእሳቸው ክፉ መናገር በማይቻልበት ጊዜ! አሁን ግን ሁለታችንም ስኳሩን አግኝተነዋል። አንተስ አገኘኸው?

ነፍሳቸውን ይማረውና ያኔ ሻለቃ አድማሴ አቶ ታምራት ለም/ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲሾሙ፤ "አቶ ታምራትን ሕዝቡ ፈጽሞ አይወዳቸውም፣ እንደማይወዳቸውም በስታዲየም የተሰበሰበ ሕዝብ ሁሉ ከስድብ ጋር ነግሯቸዋል፣ ለሕዝብ አይበጁም" ብለው በህገ መንግስት ሸንጐ ላይ በድፍረት ተናግረው እንደነበረና አቶ መለስ ዜናዊ አንጓጠዋቸው እንደነበረ ትዝ ይለኛል – ዛሬ ግን አቶ መለስ «የአቶ ታምራትን ምግባረ ብልሹነት ካወቅኩት ቆይቻለሁ ባስመክር ባስመክር እምቢ አሉኝ» ይላሉ። እሳቸው የሰው ምክር እንደሚሰሙ ሁሉ!

በሌላ ጐን ደግሞ አቶ መለስ እንደሚሉት በስልጣን መባለግ ብቻም አይደለም – የዘር ስልጣን ሽኩቻም ሊሆን ይችላል የሚሉም የፖለቲካ ታዛቢዎች አሉ። እንግዲህ በሥልጣን መባለግ በይፋ የታወቁት የጎንደር አማራ ነኝ የሚሉት የኢህድኑ ታጋይ ታምራት ብቻ ከሆኑና ሌሎቹ የቲፒኤልኤፍ ሹማምንት ንፁህ ከሆኑ የሜጋ ኢንተርፕራይዝ ኃላፊ የወይዘሮ አዜብ ባል ታጋይ መለስ ዜናዊ በታጋይ ታምራት ላይ ያቀረቡትን ክስ እናዳምጣለን። መቼም ለጉድ ጎልቶናል!!

አያ ገብርዬ! ስለምክር ቤቱ ካነሳሁ አይቀር በዚያን ሰሞን ሽንጐው "ስለ ምክር ቤት አባላት ዕድር ማቋቋም አንስቶ ሲወያይ ዋለ" የሚለውን ዜና ሰምተን፤ ስንት አንገብጋቢ የአገር ጉዳዮች እያሉ ይህን ተራ የሆነ የግል ነገር እንዴት እንደ አንድ ትልቅ አጀንዳ አድርገው ይወያዩበታል እያልን ስንወያይ አንድ ቀልደኛ ጓደኛዬ ምን አለን መሰለህ – "እውነታቸውን እኮ ነው የዕድር ድክመት ነው እንጂ ኢሕአዲግ እኮ ከሞተ ቆይቷል!" ብሎ በቅኔያዊ አነጋገር ነገረን። ግን እኮ ገብርዬ ይህን ዕድር ማቋቋም ያለብን እኛው ነበርን። እነዚህን ሰዎች ጊዜ ባንሰጣቸውና በአንድነት ተባብረን የሚሆነውን ብናደርግ አንድ የተስፋ ጭላንጭል ይኖራል ብዬ እገምታለሁ። ከላይ ያለው መናጋት ከታች ላለው መንቀሳቀስ ይረዳልና! እስቲ ሁላችንም በየፊናችን በአንድ ልብ እንምከርበት ባይ ነኝ። አንተስ ምን ትላለህ?

ገብርዬ! ግን እኮ እዚህም እኛ ጋ ሰው የአንድነትና የመተሳሰብ ፍቅር እንዲያጣ ተደርጓል። ሰው ለወንድሙ፣ ለወገኑ ችግር ልድረስ፣ እርዳታ ልስጥ ሲል እንኳ አይሆንም አትችልም፣ እኛው እንበቃለን ማለት ጀምረዋል። በያን ሰሞን በወንጂ ከተማ የውኃ መጥለቅለቅ አደጋ ደረሰና የአካባቢው ሕዝብ በተለይም የናዝሬት ሕዝብ አንድ የዕርዳታ ኮሚቴ ያቋቋምና ገንዘብና ልብስ ማሰባሰብ ይጀምራል። በመሐሉም ካሰባሰቡት ገንዘብ ላይ ለወገኖቻችን እንርዳ ብለው እጃቸውን ቢሰነዝሩ የእርዳታ ማስተባሪያ ኮሚሽን ማን አላችሁና! ምን አገባችሁና! ብሎ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለየሕዝቡ እንዲመልሱ አደረጋቸው። ይኸውልህ እንግዲህ ገብርዬ ልብ በልልኝ እውነት አሁን ይሄ ድርጅት ራሱን ችሎ ዕርዳታ መስጠት የሚችል ይመስልሃል? ለምን ሰው እርስ በርሱ ይረዳዳል? ሰውስ ከአደጋው ለምን ያገግማል? ለምንስ አንድነትና ሕብረት ይኖራል? ከሚል ከክፋትና ከማን አህሎኝነት የመጣ እንጂ! እኔማ ይሄን ስሰማ ግርም ብሎኝ ሰነበትኩኝ። እሺ እንግዲህ እነሱ የሚመጣውን ዕርዳታ ወደ ሰሜን ከጫኑት፤ የመሐል አገሩ ሰው ደግሞ ሁሉን ትቶ ለወገኔ እኔ አለሁ ሲል አይሆንም ካሉት ምን ማድረግ ይበጃል ትላለህ? ወገኔ እንደው መላው ጥፍት ያለ ነገር እኮ ነው። ብቻ ገብርዬ መመዝገብህን እንዳታቋርጥብኝ።

ገብርዬ እስቲ በሰፊው ስለሚወራለት ስለዚህ የዘር ፖለቲካ፤ የንግድ አመሰራረትና አደረጃጀት ገፅታ የማውቀውን ያህል ትንሽ ላስረዳ።

የዘር ፖለቲካ በአገራችን ተንሠራፍቶ፤ ሕዝብ ከሕዝብ በዘርና ጐሣ ተለያይቶ የአገር ሕልውና በሚያሰጋ ሁኔታ እያሽቆለቆለ መሄድ ከጀመረ አምስት ዓመት አለፈው። በዚህ አምስት ዓመት ለሕዝባችን የተረፈው ነገር ቢኖር የኑሮ ማሽቆልቆል፣ የብር ምንዛሪ ኃይል ደብዛው መጥፋት፣ የባህር ወደብ አልባ መሆን፣ ከሥራ መፈናቀል፣ ... በአንፃሩ ደግሞ ከደደቢት በባዶ እግራቸው ተነስተው አዲስ አበባ የገቡት የ"ነፃነት ታጋዮች" የሕወሓት(TPLF) መሪዎችና አባላት እየከበሩ፣ እያማረባቸውና በእብሪት እየተወጠሩ የሚሰሩትን እያሳጣቸው መሆኑንም እያየን ነው። ታጋይ መለስና ታጋይ ታምራት ከሜዳ ሲመጡ ይመስሉ የነበሩትንና አሁን የሚመስሉትን ማየት ብቻ ይበቃል – ጌታዋን የገደለች በቅሎ እንዲሉ። የዛሬ አምስት ዓመት ምንም ያልነበራቸው "ተጋዳላዮች" ዛሬ የ"ትግላቸው" ፍሬ የሆነውን ሀብት በማከማቸት የፖለቲካ የበላይነት ብቻ ሣይሆን በኢኮኖሚውም የበላይነት በመያዝ ላይ ናቸው። እነዚሁ የሕወሓት "የነፃነት ታጋዮች" በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮችን የግላቸው በማድረግ ለ17 ዓመታት በጫካ ሆነው ይከተሉት በነበረው ፍልስፍና መርሆ መሠረት ሲያወግዟቸው የነበሩትን ካፒታሊስቶችን ራሳቸው መሆናቸውን በትዝብት ዓይናችን እያየን ነው። ዛሬ ሹማምንቶቹ በትግራይና በሌሎች ክፍላተ ሀገሮች የኢኮኖሚ ሞኖፖሊስቶች በመሆን ሕወሓትን የማይጋፋት ድርጅት እንዲሆን ሙከራ እያደረጉ ነው።

ቀድሞ ከደርግ ጋር በነበረው ጦርነት ከየቦታው በመዝረፍ ያከማቹትን ገንዘብና በተጨማሪ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ተቋቋመ የተባለው የትግራይ ልማት ማሕበር (ትልማ) ከውጪ አሰባሰብኩት በሚለው ገንዘብና ሐብት፤ ብዛት ያላቸው የትግራይና የኤርትራ ነጋዴዎች የአገሪቷን ሀብት በቁጥጥራቸው ስር ሲያስገቡ ቀሪው ወገን የበይ ተመልካች መሆኑን እየተመለከትን ነው።

የግል ኢኮኖሚን (ፕራይቬታይዜሽን) ማስፋፋት በሚለው የኢኮኖሚ መርህ ሰበብ ዛሬ የብዙ ግል ሀብት ባለቤት መሆን ለሕወሓት

አባላት፣ ቡችሎቻቸውና ለኤርትራውያን የተደነገገ ሁኔታ ነው። የዛሬው የትግራይ አዲሶቹ ካፒታሊስቶች የቀድሞዎቹ የሕወሓት የሚሊቴሪና የፖለቲካ ኃላፊዎች ወይም ሙሉ በሙሉ ታማኝ የሆኑ የትግራይና የኤርትራ ተወላጆች ናቸው። እነኚህን እስቲ በቅርቡ ከአንድ መረጃ ያገኘሁትን በጥቂቱ ልዘርዝርላችሁና የምለው ይገባችሁዋል።

1. (EFORT) - Endowment Fund of Rehabilitation of Tigray የተባለው ድርጅት የሚከተሉትን ኩባንያዎች በውስጡ የያዘ ነው።

ሀ) የመስፍን ኢንዱስትሪያል ምህንድስና ኩባንያ (Mesfin Industrial Engineering) ቀደም ሲል በሞተ የሕወሓት አባል የተመሰረተ

ለ) ብሩህ የኬሚካል ኢንዱስትሪ–(Beruh Chemicals)

ሐ) መሰቦ የሕንፃ መሣሪያዎች–(Mesebo Building Materials)

መ) ትራንስ ኢትዮጵያ–(Trans Ethiopia)

ሠ)ሕይወት አግሪካልቸራል ሜካናይዜሽን – (Hiwot Agricultural Mechanization)

ረ) አልሜዳ ጨርቃ ጨርቅ–(Almeda Textile) የተባሉትን በውስጥ የያዘ ሲሆን

የእነዚህ ማለትም በኤፈርት ስር ያሉት ታላላቅ ኩባንያዎች ዋና ሥራ አስኪያጅ የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትር ስዬ አብርሃ ሲሆኑ፣ የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊው ደግሞ የቀድሞው የሕወሓት ሊቀመንበር የነበረው ስብሃት ነጋ የሚባል ነው።

– የስዬ አብርሃ የቅርብ ዘመድ የሆኑት ፍፁምዘዓብ አስገዶም ደግሞ (The Monitor PLC) የተባለውን የሚዲያ ካምፓኒ ይመራሉ።

– የማዕድንና የኮንስትራክሽን ዘርፎቹን ደግሞ የሚመሩት ቴዎድሮስ ሐጐስና አርከበ ዕቁባይ ምትኩ የተባሉት የሕወሓት የአመራር አባላት ናቸው።

– ብርሃን የሕንፃ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የተባለውን በረከት ማዘንጊያ በሊቀመንበርነት ይመራዋል።

– መስከረም ኢንቬስትመንት የተሰኘው በውስጡ አፍሪካ ኢንሹራንስ የተባለ ኩባንያና ሌሎች ሁለት የትግራይ ኩባንያዎችን የያዘውና ሻላ የማስታወቂያ ድርጅት የተባለው በአሰፋ ማሞ የቀድሞው የሕወሓት የማስታወቂያ ማዕከል አስተባባሪ የሚመራው በሕወሓት መሪዎች ሞኖፖሊነት ከሚመሩት ትላልቅ ኩባንያዎች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

– ሰላም የአውቶቡስ ኩባንያ (Selam Bus Line) የተባለውን ትልቅ የትራንስፖርት ኩባንያ የትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ) ዋናው ባለአክስዮን ነው። ይህ ኩባንያና ሱር ኮንስትራክሽን ሊሚትድ (Sur Construction Ltd.) የተሰኙት የንግድ ኩባንያ በጠቅላላ ኢትዮጵያ ከተሞች የተስፋፉ ድርጅቶች ናቸው።

– ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ የኪራይ ቤቶች ድርጅት የሚተዳደረው በትግራይ ዕድገት ማህበር ነው።

– ቀደም ሲል ኩራዝ የሚባለውን የሕትመት ድርጅት የወረሰው ሜጋ ኔት ኮርፖሬሽን በውስጡ የሕትመት፣ የፕሬስ፣ የማስታወቂያና ሜጋ እስቱዲዮ ኢንተርፕራይዝ የተሰኘ የአውዶ ቪዡዋል ኩባንያዎችን ያካተተ ሲሆን የዚህ ትልቅ ኮርፖሬሽን ኃላፊና ተቆጣጣሪ አንድ ቀን እንኳ በሕዝብ ዓይን ታይተው የማያውቁት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ ናቸው። ገብርዬ ይህ ሜጋ ኔት ኩባንያ ትልቅነቱ እንዲህ እንዳይመስልህ።

–ሶፍካም የተሰኘው በ1986 በዶክተር መሐመድ ዱሪ (የኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ቋሚ ተወካይ ልጅ ሙኒር ዱሪ የተመሠረተው ድርጅት ከኤርትራው ነጋዴ ከበረከት (የሞቢል ኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ) ጋር በ10 ሚሊዮን ዶላር ፓርትነርሽፕ የድሬዳዋንና የአ/አበባን ኮካ ኮላ ኩባንያ በቁጥጥራቸው ሥር ነው። አሉላ አርአያ ገብሩ (የቀድሞ ሕወሓት አባል)፣ ንጉሤ ኃይሌ አበራና ሁሴን አብደላ ቃሲም (ሁሴንና ወንድሙ ዋሲም) ከታምራት ላይኔ ጋር የቅርብ ግኑኝነት አላት የተባለችውና ለእስር የበቃችው የወ/ሮ ሽዲያ ዘመዶች ናቸው። ሶፍካም በአጭር ጊዜ ማለትም በተቋቋመ በሶስት ዓመታት ውስጥ በጣም ያደገ ሲሆን፣ በዚህ ቅርንጫፍ ስር ደግሞ ብቸኛ የሆነ የዓለም አቀፍ ሳተላይትና ሬዲዮ አገልግሎቶች አከፋፋይ ወኪል ነው። ሶፍካምና በረከት የምሥርቅ አፍሪካን በትሊንግ ኩባንያንም አቋቁመዋል።

– ሌላ ባለቤትነቱ የእነዚሁ የትግራይ ታጋዮች የሆነው በጂማ ከተማ ያለው ካሬ ሊሙ የተሰኘው ትልቅ የቡና ድርጅት ነው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በትልቅ የሚታዩና ደረታቸውን ነፍተው በማንአለብኝነት በግልፅ የሚንቀሳቀሱ ሲሆኑ ሌሎች አነስ አነስ ያሉት ደግሞ የትየለሌ ናቸው።

እነዚህ እንግዲህ ቀደም ሲል በደርግም ሥልጣን ጊዜ ሆነ አሁን በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች በትግራይና በኤርትራውያን ተወላጆች

በንብረት የተያዙትን የአገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ማለትም እንደ ቡና ቤት፣ ጅምላ መሸጫ መደብሮች ወዘተ ... ያሉትን ሳይጨምር ነው። እንግዲህ ገብርዬ ይህ ሁሉ የምነግርህ ድርጅት በአንድ ጉሣ (ዘር) የተያዘ በመሆኑ ሌላው ሰው ሸባ ሆኖ የሰራው ሁሉ ውኃ እንዲበላው እየተደረገ ነው – በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት ይሉሃል ይሄ ነው።

እንግዲህ አቶ መለሰና አቶ ታምራት፤ አንዳቸው ከአንዳቸው በዘር ይለያዩ እንደሆን እንጂ እንደምታየው በሐብት ማካበት በኩል ሁለቱም የሚተናነሱ አይመስልም። "የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" ነው ነገሩ። ገብርዬ ዋናው አለመቀደም ነው፤ ዛሬ አቶ ታምራት ተቀድመዋል፤ ተወቃሽ ሆነዋል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንደኛው ሌላውን ይወቅሳል፣ እንደገና ሌላውን . . . "ታሪክ ራሷን ትደግማለች"

ውድ ገብርዬ! በመጨረሻ ማለት የምፈልገው መቼም በአትላንታም ሆነ በአሜሪካ እንዲሁም በመላው አለም ከሚገኝ ኢትዮጵያዊ ውስጥ ለአንድ ገብርዬ ብቻ በማለት ይህን ሁሉ አቤቱታ እንደማልዘግብ ልባችሁ የሚያውቅ ይመስለኛል። እንደ ወዳጄ ገብርዬ ብዕራችሁ አፍ አውጥቶ ባያናግረኝም በሃሳባችሁ፣ በልባችሁ ከእኔው ጋር የምታስቡ፣ ጭንቀቴን አብራችሁ የምትጋሩ የአገራችሁ ጉዳይ በብርቱ የሚያሳስባችሁ ሌሎች ብዙ ገብርዬዎች ትኖራላችሁ ብዬ ተስፋም በማድረግ ነውና አረ ጉበዝ ሲባል እስቲ እናንተም እኸም በሉ! ገብርዬም ቢሆን ለአንድ ወርቃየሁ ሲል ብቻ አይደለም ይህን ወኔ ቀስቃሽና አስተማሪ የሆኑትን በሳል ፅሑፎቹን በየጊዜው የሚፅፈው። በመድረኩ በውስጥም ሆነ በውጪ ያለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን በማለት እንጂ! እና ታዲያ ለወገን ጥሪ ደራሽ ወገን ነውና እስቲ ሁላችንም ከያለንበት አንድ እንበል እላለሁ። አለበለዚያ፦

*እንዲያ እየመከርኩህ አንተ እየተቆጣህ፣*
*እኔም መቀመጫ አንተም መግቢያ አጣህ።*

እንዳይሆን በውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ ያለን የኢትዮጵያ ልጆች በሙሉ ብናስብበት ይሻላል ባይ ነኝ። ወዳጄ ገብርዬ! እረ ለመሆኑ የይግለጡ ነገር እንዴት ሆነ ጃል! በየምናምኑም ብፈልገው ብዕሩን አጣሁት። እረ ቃል ይከበር በልልኝ። ወይስ ወዲህ ሊመጣ አስቦ ጌቶቻችንን ላለማስቀየም ፈርቶ ነው!

ለዛሬ ይሄን ካልኩ እስቲ በቸር ከከረምን ደግሞ ሌላውን ሌላ ጊዜ እላለሁ።

ደህና ሁኑልኝ። ወርቃየሁ ነኝ – ከሸገር

# ሠላምታ ከባህር ማዶ ከገብርዬ — ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል። እኔ እንዳለሁ አለሁ። አንተ ለመሆኑ እንዴት ነህ? ለወፉም ለዛፉም ሰላም በልልኝ። ለፀጋዬ ገብረ መድህን አርአያም። ወርቃየሁ ስለ ፀጋዬ አንድ ነገር እንድል አደራ ባልከኝ ሰሞን የእርሱም ሀሳብ እንደወፍ እየበረረ ብቸኛ አፓርትማዬን በሚያዋስኑ ዛፎች ላይ ሐሳቡ ተንጠላጥሎ የሩቅ ድምፀ–ገሐድ በመሆን በንጋት ከእንቅልፌ እየቀሰቀሰኝ እረፍት ነስቶኝ ከረምኩ።

ውድ ወርቃየሁ!

ንጋት እየመጣ ነው። ጭለማ ለጉሕ ቦታውን መልቀቁ የግድ ነው። ንጋት ንጋት እያለኝ ነው። እንዴት አደርክ (Good Morning) ለማለት ምኞቴ የደረሰ ይመስላል። ግን ጅቦች ያሽካካሉ፣ የሌሊት ወፎች ግን በግርማ ሞገስ ቃና መዝሙራቸውን እየዘመሩ ነው። ጅቦች ቀበሮዎችንም አስተባብረዋል። ልትወድቅ የቃጣትን የላሜ ቦራ ወርች ለመቀራመት ዓይን አውጣ ተራድዖአቸውን ተያይዘውታል። ነጭ ጅብና ጥቁር ቀበሮ ጥርሳቸውን እያፋጩ ላሜ ቦራን ከበዋታል። ወፎችም ይንጫጫሉ። ከእነርሱም ውስጥ ለመዘመር ብቻ ጉራማይሌ የሚዘፍኑ አሉ። ንጋት ሲመጣ ሁሉም በአደባባይ ሊጠያየቁ ነው። የንጋት ሕልም ነው መሰለኝ፤ የፀጋዬ ገብረመድኅን ጩኸት ከደም ምድር ተጣርቶ ቀሰቀሰኝ። የሰመመን እንቅልፍ ነው። ስለ ወፎች ባወራህ ቅር ይልሃል? ደግሞ ገብርዬ ምን አመጣ? እንዳትል። የሊትሬቸር ስሜቴን ከልቤ እንደእሳተ ገሞራ የሚፈነቅለው ይህ የጅቦች፣ የቀበሮዎችና የወፎች አሰላለፍ ነው። ወፎች ብልጦች ናቸው። እንደሀገራቸው ይዘምራሉ።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ታሪክ ፀሐፊዎችም፣ መጣጥፍ አቅራቢዎችም የራሳቸው እምነት አላቸው። አንድ የእንግሊዝ ፈላስፋ ሬ. ጂ. ራይነር የተናገሩት ይታወሰኛል፦ "ታሪክ ፀሐፊ ከሚፅፈው ታሪክ ራሱን ወርውሮ ሊጥል አይችልም። የራሱንም ምናልባት ሌሎች ተዛብቷል የሚሉትን አስተሳስሎ ወደ አንድ ሚዛን የሚያጋድለውን እንኳ ለአንባብያን መግለፅ ይገባዋል። ይህን ካላደረገ ቅራኔ በውስጡ ይቀስፈዋል፤ ፀሐፊም ራሱን መሆን አለበት።" ፀሐፊ ታሪከኛም ነው። ፀሐፊ ለውጥ አምጭም ነው። እንደ መንግሥቱና ፖልፓት የራስን ቅል በየጥሻው እንደብቅል

የሚያሰጣ ነው። እንደ ሶስተኛው ራይክ (የሂትለር መንግሥት)፣ እንደ ቦስንያና ሩዋንዳ የዘርና የጎሳ መዘዝ በማምጣት ሕዝብን አራርቆ የኢሕአዴግ መንግሥት እንዳደረገው ለዘመናት የሚቆይ የቁስል እርሾ በመጠንሰስ ሀገርንና ወገንን ይገነጣጥላል። አማኞችን ይኮረኩራል። የአልቃሾችን የባሰ ሆድ በማሸበር ደረታቸውን እንዲደልቁ ያደርጋል። ይህ ሁሉ የጣፊዎች ሥራ ነው። ለፍትሕም ይታገላል። ለሐቅም ይሟገታል። በብዕሩ የእሳት ትንታግ ለብልቦ ቦዘኔውን ማልኮለም የሕዝብ ቤዛ ያደርገዋል። ሲያሰኘውም እንደ ሲግመንድ ፍሩይድና እንደ ዶክተር ሩዝ ስለወሲብና መዳራት በማተት የሰውን ጭንቅላት በዝሙት ፓለቲካ ይቀይረዋል። ማርክስ ነፍሱን ይማረውና ራሱ ቀስቅሶ ራሱ ጽፎ ይህ የላብአደሩ ትግል ነው ብሎ ነበር። ላብአደሩና አርሶ አደሩ ሳይጠግብ እንደገና ደግሞ በብዕሩ መንጠቆ አፍንጫውን ሰንጐ ይቀለብሰዋል። ማርክስ በእውነትም ዓለምን በሁለት ካምፕ ከፍሎት ነበር። ፀሐፊ እጅግ ኃይለኛ ነው። ወፍ ማለት ነው። እንደ ዘጌ ወፍ አብሮ እየተንጫጫ አገር ያውካል፤ አገር ይበጣጥሳል። መልካም ነገር ሲያመጣም መጥፎውንም ይዞ ይቀርባል።

ውድ ወርቃየሁ! ግን ፀሐፊ ያነጋግራል፤ አእምሮን ይጠርባል። አንዳንዴም አደናጋሪ ጽሑፍ ጥፎ መያዣና መገንዣ ያሳጣል። የጥፋት ወታደር ነህ ሲሉት የኢኢስ ቆጳስ ካባ ደርቦ የለም ጳጳስ ነኝ ይላል። እንደ ጅብ ማለት ነው። ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቆረንጦ አንጥፉልኝ ይላል። ስለ ፍቅር ሳይታገል መዋደድ ከሰማይ እንዲወርድለት ይጠብቃል። እርሱ ሳይነድ ሌሎችን በእሳት ያበራያል። እናንተ ስለተጐሳቆላችሁ እኔም በእርዛታችሁ ተቃጥዬ አብቅቼአለሁ ብሎ ይተርካል። ቀበሮ የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ እንደታገለችው ወዋደድ እያማረው ግን ሰውን እየጠላ ስለፍቅር ይሰብካል፤ እንደ ቀበሮ የበሬውን ታፋ ለመገሽለጥ እየተንኳተተ ውጉዝ ከመአርዮስነቱን በእርግብነት ያምታታዋል። እንደ አባ ጳውሎስ ማለት ነው።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ፀሐፊ ደማሚት ነው። ሲያሰኘው የዓባይን ያህል የስምጥ ሸለቆ በብዕሩ የሀረግ ተቀጣይ ሽቦ አፈንድቶ ሐይቅን ይመሠርታል። ሮበርት ሒል ብሮነር እንደተናገሩት፣ "እናም የሰው ልጅን አእምሮ መት በመት የሚያስልፍ ፀሐፊ ሁሉ ከጐራዴና ከጦር መሣሪያ የላቀ ኃይል አለው። እንደነርሱ ያሉ ሰዎች የዓለምን ቅርፅ በመለወጥ አሽከርክረዋታል። ሆኖም ከእነርሱ መካከል ጥቂቶች ናቸው እንኳን በጦርነት ለመዋጋትና ጣታቸውን ቀስረው እንኳ በመቃጣት ያላነሱት፤ በምሑርነታቸው ብቻ በመሥራት ሳይታዩና ሳይታወቁ ስለእነርሱም ዓለም ምን እንደሚያወራ ደንታ ሳይሰጣቸው በሸምቅ ተዋጊነት የሚያገለግሉት። በእነዚህም የብዕር ባቡሮቻቸው እየተጓዙ ክፍለዓለማትንና አሕጉሮችን አፈንድተዋል፤ መንግሥታትን ከትኩተው ከማሳደጋቸውም በላይ በቀለማቸው ግልምጫ ፈንግለዋቸዋል፤ መደብ ከመደብ ብሔር ከብሔር አቃቅረዋል። ይህንንም የሚያደርጉት በፖለቲካ ሤራና ጉሽ በመጠንሰስ ሳይሆን ባላቸው የላቀ ክፉም ሆነ ጥሩ የሀሳብ ምርት ነው።"

ያገር ልጅ ወርቃየሁ!

ወፎች ያስደንቁኛል። የሚሊዮን ዓመታት የመብረር ዝግመተ ለውጥ (Evolution of Flight) ሳይሰለቻቸው የቅልጥማቸው መቅን እንኳ እንዳይከብድ መጥነው ከተፈጥሮ ጋር ተጓሽመው በአሉሚኒየም ቆርቆሮ ለተሰሩት ዘመናዊ አውሮፕላኖች መንደርደሪያ የፈጠራ መሠረታዊ ስዕል (Blue print) ሆነው ሳይ በፈጣሪ መኖር አልጠራጠርም። ከዚህ በፊት እንደተሞኘሁት እግዜር የለም ብዬ ፈጣሪን አልክድም። የዘጌም፣ የዲማም፣ የአዋሳም፣ የላንጋኖም ወፎች ይደንቁኛል። የወፍ ነፍጠኛ ፣ የወፍ ጭቁን በረሽኛ ብሔር የለም። ወፍ ለየቅሉ እንደሀገሩ ይዘፍናል። እደጋግመዋለሁ። የወፍ መዝሙርና የጢንዚዛ የክንፍ ቅኝት ይለያያል። ሽማኔ መዘራዝሩን እየረገጠ መወርወሪያውን እየሰደደ ሲሰራ ሚስቱ ፈስታ ለማደናገር ብትሞክር "ይኼ ሌላ ያ ሌላ" አለ ይባላል። የብሔር የጥዝጥዝ መፈክር ከኢትዮጵያ የሕዝብ ሙብት መፈክር እጅግ ይለያያል። የአንድነት የእርግቦች ጨኸት በብቾኛ የቁራና የየሎስ የአሞራ ጉርናና ድምፅ መቀየር አይችልም። የገብረ ጉራቻ፣ የወረሒሙኑ፣ አንጉለላ፣ የየረር፣ የጉለሌ፣ የበቾ፣ የአርማጭሆ፣ የአቢይአዲና የከረን አንድ ወጥ ዝርያ ያላቸው (species) ወፎች በእርግጥም አንድ ናቸው። ከዚያም አልፈው የቱርካናን ሐይቅ፣ የሰሐራን የበረሃ ምንጭ፣ የደቡብ አፍሪቃን ሻርፐቪል፣ የሱዳኑን ኡምዱርማን፣ የጅቡቲን፣ የበፅ(ምፅዋን) ... ወዘተ አየር በክንፋቸው የሚሰነጥቁ የአንድ ዝርያ ወፎች በእርግጥም ወፎች ናቸው። ግን ለየቅላቸው እንደአካባቢያቸው ስልጥነዋል። ልዩ ለመሆን ይቃጣቸዋል። ከአስመራ አዲስ አበባ ይበራሉ። ሲያሰኛቸው ከብዙ ስቃይና ጉዞ በኋላ እያረፉ መቀሌን ይጐበኛሉ። በሚኔሶታ፣ በቢ ኤም ደብልዩ ፓራፋንጐ(መጫኛ) ላይ እየተሰቀሉ የአሜሪካ ወፎችም ሆነው የኦሮሚያ በራሪ ነን የሚሉ ይመስላሉ። የባሕላችን ውጤት የሆነውን እንጀራ አብሮ ለጥቅማቸው ከመፈርፈር ይልቅ "ቡዱና" የእኛ ነው በማለት ሌላ መዝገበ ቃላት ለመፍለጥ የሚዘምሩ መስለው ይታያሉ። ሌሎች ወፎችን በላቲን ዘምሩ ሊሉ ይቃጣቸዋል። ወፎች የሚያምፁበት ቀን ቀርቧል። ወፎች በላቲን መዘመሩን የሚቃወሙ ይመስላል። ለምን

ከሲሲሊያ ቋንቋ ይልቅ በለመድነው ቋንቋ አንሮህም ይላሉ። ከማያውቁት "የመልአክ" ቋንቋ የሚያውቁት የሰይጣን ኢስፔራንቶ ይሻላል ያሉም ይመስላል።

ዛሬ በዚህች ጦማር የምገልፅልህ ውስጣዊ ችግራችንን ነው። አንዳንድ ጭውውት ሚስጢረኛነቱን ሳይጠብቅ ሁሉንም እየነካ ነው። በግልፅ ለመነጋገር ፍራቻና ይሉኝታ አለ። አንድ ከዚህ በፊት ጓደኛዬ የሆነ "ኤርትራዊ"ን ቡና ቤት አገኘሁት። አሜሪካ በኃይለስላሴ እስኮላርሽፕ ከመጣ ብዙ ጊዜያት አለፉት፤ ጠጉሩ ተመልጧል። አርጅቷልም። ፈራ ተባ እያለ ጓደኞቹን ካሰናበተ በኋላ ሊያነጋግረኝ ሞከረ። "ወንድሜ ሆይ! የእኛ ነገር ቢነገር ተተርኮ አያልቅም። ወይ ፍትሕን አላመጣን ወይ ከእናንተ አልሆን ... መላም የለው። ልጆቼ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታቸውን ጨርሰው ከኢሳያስ የወታደር የሀገር ጥሪ ለማምለጥ አዲስ አበባ ነው ያሉት ... ያልጠላናችሁን ያህል እየወደድናችሁ ነው ... እባክህን ነገሩ ሁሉ ያሳዝናል" ሲለኝ ክው ብዬ ደነገጥኩ። በዚያ ሰሞን ደግሞ አንዲት የትግራይ ልጅ ሥራ ቦታ "ከአማሮች ጋር ስሆን የሰረቅሁ ይመስል በእፍረት አንገቴን እደፋለሁ፤ ጓደኞቼ ሁሉ ርቀውኛል፣ እኔም ርቄያለሁ ... ታዲያ አማራ ጠላቴ እንዳልሆነ እረዳለሁ .. እነዚህ መሪዎቻችን ጉድ ነው ያመጡብን ... ምን ጊዜ መጣ? ... ምን ዓይነት መዓት መጣብን?" ... በማለት ለአንዲት የጓደኛዬ ዘመድ ያጫወተቻት ትዝ ይለኛል።

ዛሬ ክርክሩ ጦፏል። በክልል፣ "በሬፈረንደም"፣ በየራስን ዕድል በራስ መወሰን ላይ ብዙ ጥያቄ ተነስቷል። አውሎ ነፋሱን ያስነሳው የጉሳ አዙሪት ትንሽ ጋብ ሲል ሁሉም መጠያየቅ ጀምሯል። ግን ሁሉም ለጥያቄው የሚያረካ መልስ ያገኘ አይመስልም። ተፋጧል፣ የጉሪጥም ይተያያል። ምን ሁኔታ ተፈጠረ። የሆነ ሆኖ ይህ የዘርና የጉሳ መርዝ ከመረጨቱ በፊት ሁሉም ከዚህች መሬት ነው የበቀለው። ፀጋዬ ገብረመድህን አርአያ "የሁሉም ዘር ከዚህች ምድር ነው የወጣው" ይላል በጦቢያ መጣጥፉ።

ውድ ወርቃየሁ! ክረምቱ በአሜሪካ እየጀማመረው ነው። በየአፓርትማና ጉዳናዎች አካባቢ የተተከሉ ዛፎችና አበቦች በውርጭ ረግፈዋል። የክረምቱን አስቃቂ ቆፈን በመፍራት ይመስላል በዋግ እንደተመታ የሀገራችን ተክል ጥላ ርቋቸዋል። ወሮችም በየዛፉ መንጫጫታቸውን ትተው በየታዛውና በየበረንዳው ጣሪያ ላይ በመቆናጠጥ የተፈጥሮ መስፈሪያ ዋርካ እንደሌላቸው ሁሉ ከኃጢአተኛው የሰው እንስሳ ለመደበቅ ሲንሺከኩና ሲሽለኩለኩ ይታያሉ። ዝግመተ ለውጥ(Evolution) ሳይወዱ በግድ እየኮረኮመ ስላሰለጠናቸውና የተፈጥሮም ምርጫ (Natural Selection) ጠንካራ ጠባይ የሚለግሳቸውን የዘር ቅመም ስላጐናፀፋቸው ከሞት ለመዳንና ለመኖር የሚያደርጉት ትግል ኢየሱስ ስለወፎችና እፀዋት ከሰጠው ትምህርት ጋር የሚጋጭ ይመስላል። በቀላሉ በሐረግ ሲተመን (Paraphrase ሲደረግ) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከዚህ ጋር ይቀራረባል፦ "በራሪ ወፎችን ተመልከቱ፣ አያርሱም፣ አያጭዱም፣ አይጨነቁም፣ ለነገ አያስቡም። የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሰማዩ አባታቸው ይለግሳቸዋል፤ ይሰጣቸዋልም።" ትንሹም ወፍ፣ ትልቁም ወፍ፣ ድንቢጡም እርግቡም እንኳ ሁሉም ወፎች መሆናቸውን ያወቁ ይመስላሉ። ጠላት ሲመጣ አብረው ይንጫጫሉ። የአዳኝ የረሸ ርችት ሲተኮስ ክንፋቸውን በማጨብጨብ ሌላው እንዳይዘናጋ ያሳስባሉ። ይጨነቃሉ። ካልታገሉ የሰማዩ አባታቸው ዝም ብሎ የግብረሰናይ ዕርዳታ (Welfare Check) እንደማይፅፍላቸው ያወቁ ይመስላል። የጌታንም የበላይነት እየተቀበሉ በኑሮ ውጣ ውረድ እንደቦታውና ሁኔታው ሳይቦዝኑ ከአብራካቸው ለወጡት ጫጩቶች ከተጣለው የሥጋ ቁርቁሮና ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ምግብ ይለቃቅማሉ። በውዲቷ ኢትዮጵያ ማሽላን በወንጭፍ ከሚጠብቀው እረኛ በትግላቸው እጅግ ሰልተው ዘርን በኩምቢያቸው ይዘው ለ"ብላቴናቸው" እንደሚያጉርሱ ሁሉ እዚህም ከቆሻሻ የጭነት ማጠራቀሚያና ማጓጓዣ እንኳ ሳይቀር ፈልፍለው የሚበሩት በየሕንፃዎች ለደበቋቸው ንዑሳን ነፍሳት ነው።

ሁሉም ግን ወፎች ናቸው። ከአንድ ወጥ የመጡ ደመ ነፍሶችና አዝእርት (Species) እንደነዚህ ወፎች ጉሳ ለይተው ቡራ ከረዮ አይሉም። ድንቢጦች ድንቢጥ ወፎች ናቸው። ከአንድ ወጥ ወፎች የአማራ፣ የትግሬና የኦሮሞ ጉሳ ወፎች የሉም። ሁሉም ከአንድ ምድር ነው የወጡት። ነገር ግን በገጠር ከተማዎችና በእሪ በከንቱ ወፎች አለቃቀማቸው ለየቅል ነው። በዚህም ልዩነት ፈጣሪያቸውን ሁልጊዜ የሚያሳጡ ይመስላል። ምግብ ለማግኘት ረፋድ የበረራ ጉዞ ያደርጋሉ፤ ብዙዎችም ከመኪና መስታወትና መስኮት ጋር ተላትመው ይሞታሉ። እጅግ አይቦዝኑም፤ ሁልጊዜ እንደተጣደፉ ናቸው። አንዳንዴም የብዙኃኑ ዴሞክራሲ የሚረዳቸው ይመስላል። በሸርሽር መንደሮችና በሶደሬ መሰል ፓርኮች በሚደረጉት ግብዣዎች ያንዣብባሉ። ቀን የወጣላቸው ይመስል ብዙኃኑ ደንገዝገዝ ሲል ቤቱ እስከሚሄድ በየዛፉ ተሰቅለው የተረፈውን ፍርፋሪ ለመቀራመት ይንጫጫሉ። ብልጥ ናቸው። የቢራ ትራፊ ሳይቀር ከተጣለው ቅዱስ ጊዮርጊስ መሰል የቢራ ጠርሙስ ስባሪና የፕላስቲክ ብርጭቆ አልኮልን ያጣጥማሉ። አልኮለኞችም ናቸው። የአደንዛዥ ዕፅም ትርፍራፊ ካለ ያንንም

መቃ አንገታቸውን ቀና ደፋ በማድረግ ከዝናብ ውኃ ጋር ያጣጥማሉ። እነዚህ የካፒታሊዝም ወፎች ናቸው፡፡ ጉሰኝነት አይሰማቸውም፡፡ የተፈጠረውን ዕድል ሁሉ ቅራኔያቸውን አሻሽለው አብረው ይካፈላሉ። እንደሰው የማሰብ ችሎታ ባይኖራቸውም በሥነ ምግባር ከነጩ፣ ከጥቁሩ፣ ከአማራው፣ ከኦሮሞው፣ ከትግሬው ... ወዘተ ይሻላሉ፡፡ ነፃ አውጪ ድርጅት የላቸውም፡፡ ወገናቸውን አይለዩም፣ ወፎች ናቸው። ነገር ግን ሁኔታው በፈጠረው በአንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ይለያያሉ። ከወሎ፣ ከአሳውርታ፣ ከአሰበ ተፈሪ፣ ከጅማ፣ ከጨለንቆ፣ ከአሊዩ–አምባ፣ ከአክሱምና ከአዲስዓለም ወፎች ይለያሉ። ስለዚህም እዚህም ያሉት የካፒታሊስት ወፎች ይለያሉ፡፡ በአትላንታም፣ በዋሽንግተንም ... በሴንትሉዊስም አሉ። ሲንጫጩ ሁሉም ወፎች እርስ በእርሳቸውም የሚሳለቁ ይመስላሉ፤ ግን በጉሰኝነት መርዝ አልተበከሉም። ስለዚህም እኛን ይበልጣሉ፡፡ ከእኛም ተማሩ ይላሉ፡፡ ወፎች እንደሀገራቸው ይዘምራሉ። የትግሬ፣ የኦሮሞና የአማራ ወፎች ለየብቻቸው ይጮሃሉ። በየረርና በከረዮ ዋርካዎች ላይ ይንጫጫሉ፤ በአጋዴንና በጉባ ቆላማ ግራሮች ላይ ይንጠላጠላሉ። ክረምት ሲሆን በተከዜ በሚቀዝፈው ግንድ ላይ አብረው ብቅ ጥልቅ ይላሉ። በራስ ደጀን ላይ የገብስ እሸት ይጠረጥራሉ። ወፎች ጉሰኞች አይደሉም፤ ከአንድ መሬት ነው የወጡት። ወፎች ሲባሉ ከአንድ የዘር ግንድ (species) የመጡትን ነው። አሞራና ወፍ ለየቅል ነው። ቢዋሰብ (ወሲብ ከሚለው ቃል የመጣ ነው) እንቁላል አይወልድም፡፡ ትግሬና አማራ ቢጋባ ልጅ ይወልዳል። የመጣው ከአንድ የዘር ግንድ ነው። ወሲባዊ ገደብ (Sexual isolation) የለበትም። ኦሮሞውም እንደዚሁ። ሁሉም ተጋብቷል፤ ሁሉም አብሮ በልቷል። የመጣውም ከኢትዮጵያ ምድር ነው። ግን በስም ብቻ ተለይቷል። በአስተሳሰቡ ከወፎች አንሷል። ከትንሿም ድንቢጥ አንሷል። ይህ ሕሊናውን (Conscience) ሊኮረኩረው ይገባል። ሕሊናውን ሲያክ አንድነት ይፈጠራል። ግን ወፍ አንድ በመሆኑና ብቻውን በመዘመሩ የግለሰብ ልዩነቱን ማንም አይቀማውም። ወፍ እንደ ሀገሩ ይዘምራል። ከአንድ ግንድ የወጣ ሁሉ በወፍነቱ የሚያምን ነው፡፡ ወፍ እንኳ ሕዋአቀፍ (ዓለም አቀፍ) ወይም Universalist ነው። እግዚአብሔርም ዛሬ ቢመጣ እንዲህ ይላል፦ “ከአንድ ግንድ የመጣ እንዴት ይለያያል፤ ይህስ ፈጣሪን አያስቀይምምን? ... በርካታስ ቅጣት በኢትዮጵያ ምድር አያመጣምን? ... ምን ነካችሁ ጉበዝ?” ይላል። በሥልጣኔ ወፍ በልጦናል፤ ጥንብ አንሳው ጆፌ አሞራ ሳይቀር በብልህነቱ በልጦናል። ቢያንስ በቀይ ሽብር ያለቀውንና በኤርትራ የረገፈውን የኢትዮጵያ ሠራዊትና ወጣት ዓይን ለጥቅሙ አብሮ ቆርቁሯል። ለክፉም ለደጉም አብሮ ይሰለፋል። በወሎ በረሃብ የተኙትን ብላቴናዎች ጉድን አብሮ ተቀራምቷል። ምን ነካችሁ ጉበዝ ጥንብ አንሳ እንኳ ለጥቅሙ ያብራል! የተክሉን፣ የይዘዘውን፣ የፈይሳን፣ የገሞራን፣ የባብሌን፣ የቱለማን፣ የመኩሪያን፣ የዝማን፣ የሙሉሸዋን፣ የሐይሎምን፣ የቀፀላን ... የሌላም ሌላም ዓይን ጉልጉሏል ... እጅግ ያስለቅሳል።

ፀጋዬ ገብረ መድኅንም አስተማረ። ሁሉም አንድ ወጥ ወፎች ከአንድ ግንድ እንደመጡ የሁሉም ጉሳ የመጣው ከዚህች መሬት ነው አለ። ፀጋዬም አለ፤ ብርሃንንም ገለጠ። እያለቀሰ ባትሪውን አበራ። ብዙ ጉድም አየ። እንደገናም አለቀሰ። እንዳለውም እንደ ሐይሌ እንደኦሎምፒኩ ድለኛ በደስታና በጭንቀት መንታ ጉርፍ አወረደ። የእምባው ጨው አቃጠለው። እንደ ወሰርቢ ጫንጮ ሚጥሚጣ ለበለበው፤ እረፍት አጣ። አንዳንዶቹ ተቹት። አጋራቸው ሆኖ ሳለ ለዩት። እንደገናም እርሱ እንደ ሻማ በሀገሩና በወንዙ እየቀለጠ ለሌሎች ብርሃን ሰጠ። እርሱ እየጨቀየ እጀ ጠባቡን አጠበ። ሰንጥቆም ሊወጣ ሲል እርስ በእርስ ተጠላለፉ፡፡ እንደገናም በጦቢያ መሰናክል ተንገዳግዶ ዘለለ። የሕዝብን የወርቅ ሜዳልያ በአንገቱ ላይ አንጠለጠለ። ፀጋዬ እንደ ኃይሌ ወርቁን ወሰደ። አጀብ! ምሁራንም መረመሩት። የገዛ ወንድሞቹ ወቀሱት፤ ወንድምነቱን ሳይረዱ ወረፉት። በግብ ሳይተናነሱ በጊዜያዊ ፍልሚያ ፈተኑት። በሀገራቸው ፍቅር ሳይበላለጡ በቃል እላፊ ትንሽ ገፋ አደረጉት። በግራው እየሮጠ በቀኝ አደናገሩት፡፡ ጥላሁንም፣ ወርቃየሁም፣ ይግለጡም፣ ፀጋዬም፣ ሀብተጊዮርጊስም፣ ማንዴላም፣ እንደ ወፍ ናቸው። ከአንድ ምንጭ ይጠጣሉ፡፡ ወፎች በኩምቢያቸው ውኃን እንደሚያጣጥሙ እነዚህም ምሁራን ፖለቲካን በአእምሮአቸው ያወጣሉ ያወርዳሉ፡፡ ሁሉም የመጣው ከአንድ መሬት ነው። ጉሽ ወገኖቼ!

ወፍ ኩምቢውን ቆርጦ ወፍ አይሆንም። ይህን ካደረገ ገጣጣ፣ ገጣባና ቁስላም እንስሳ ነው። የሰው ሠራሽ ገጣጣ ወፍ እውነተኛ ወፍን አይወልድም። ኩምቢዋ የተቆረጠች ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ አይደለችም። ዳርዊን እንዳስተማረው በሰው ሰራሽ የሥጋ መቆረጥ (Physical excision) ተፈጥሮአዊ ስኬት አይመጣም። በእኔ አመለካከት የተበላሸው አመራሩ እንጂ ሕዝቡ አይደለም። የትግራይ ሕዝብ ወንድማችን ነው፡፡ ተቆርጦ መጣል ያለበት የወያኔ አስተዳደር ወይም አመራር ነው፤ የኢሳያስ አፈወርቂም ጭምር። “ትግራይና ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለባቸው” የሚለው መፈክር በጠላቶቻችን

ወጥመድ የሚያስገባ ነው።

ይህንን የጐሳ መንግሥት ደግፈው ካቆሙትና ከሚያወናብዱት ካድሬዎችና ሰላዮች በስተቀር የትግራይ ሕዝብ ከወደፊት የታሪክ ተጠያቂነት ለማምለጥ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በማበር አሁኑኑ ሳይውል ሳያድር መፍትሔ መሻት ይኖርበታል። መሐል አገር ተወልዶ ጥምር ዜግነት በማግኘት አማርኛን እንደአፍ መፍቻው የሚጠቀም ኤርትራዊ ምንም እንኳ ውስጣዊ አክራሪነቱ ከእነኢሳያስ ቢበልጥም እርሱም ዘለዓለም በዘር ጥላቻ እየተረገመ ከሚኖር የኢሳያስ የዘረኛና የተገንጣይ መንግሥትን በመፋለም መንግሥታቱን ለማውደም (ወያኔንና ሻዕቢያን)ና ብሎም ሕዝቡን ለማቀራረብ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ያንን የሕዝብ ብርኃዊነት (CONCIENTIZACION) ሁሉም ማቀጣጠል አለበት። ያሉትን ኢትዮጵያዊና ተቃዋሚ ድርጅት እስቴት ዲፓርትመንት፣ ሻዕቢያና ወያኔ የአማሮችና የደርጐች ስብስብ ናቸው ብለው ስላስጠሉ የሚመሰረተው ግምባር ከእነርሱ አልፎ መስፋት አለበት። ከነሌንጮ ለታ፣ መለስ ዜናዊና ኢሳያስ አፈወርቂ ግልገል ፋሺሽቶች፣ ሰላዮች፣ ገንጣዮችና ካድሬዎች በስተቀር የትግራይንና የኦሮሞን ሕዝብ በቀመሩ (EQUATION) ውስጥ ለመጨመር ከባድ ትግል መደረግ አለበት። ለዚህም አመቺ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተፈጠረ ነው። ዛሬ ነገን አይሆንም። ዛሬ የሚፈለግ መፍትሔ ግን ለነገ ይሆናል። ሕዝብንም ከኗሪ ጥላቻ ያነፃል።

ወንድም ወርቃየሁ!

ፀጋዬ ገብረመድኅን አርአያም በሀገሩ እንደወፍ ይጮሃል። የዛፉን መንጠላጠል፣ ፍሬ አለቃቀሙን፣ እየራበው ለመኖር መፋለሙን፣ እንደ ግንደቆርቁር ሁሉን የዛፍ ልባስ ጠልቆ ለማወቅና ምስጢሩንም ለመግፈፍና ገሀድ ለማውጣት እየታገለ ነው። በሰደድ እሳት በዘመናት የዝግመተ ለውጥ ቴክኖሎጂ የሰራችውን ክቡር እንቁላሎችዋን ለመደበቅ የደከመችበት የሳር ቤት ሲቃጠል አምርራ እንደምታለቅሰው ወፍ በሀገሩ ሆኖ ቤቱ ሲቃጠል ሰው ያዝናል፤ የሀገሩ ሕዝብ ሲለያይ ይከፋዋል፤ ሁሉም ጐራውን እየለየ የሰደድ እሳቱን ለማጥፋት በደቦ ሳይተባበር ሲያይና ያች የድሀ ቅልሱ ስትቃጠል ይከፋዋል። እኛም ከሩቅ ከንፈር ከመምጠጥ በስተቀር ለፀጋዬ አልደረስንለትም። አንዳንዴ ግን ፈራ ተባ እያልን ያለችንን እንወረውራለን። ፀጋዬ እውነት አለው። እንደዘጌ ወፍ በዘጌ ይጮሃል። የፍትሕ ያለ እያለ ይማፀናል። ወደ ሰሜን ሲጮህ "አንት ትምክህተኛ ተቃጠል" ይሉታል። ወደ ባሕር ማዶ ሲጣራ ድምፁ ሳይሰማ አጓጉል ይሆንበታል። በፀጌ አትፍረዱበት። ወደ ደቡብ ያገር ያለህ ሲል "አንተ ነፍጠኛ" ይሉታል። ፀጌ ከፍቶታል ወርቃየሁ! ወኔን ሲቀሰቅስ አንተ "ጠበንጃ ነካሽ የጦር አውርድ እኩይ ልጅ" ይሉታል። ሊስትሮዎችም ሳይቀሩ በኪሱ የተቋጠረውን ሳንቲም ይመንችፉታል። ማንም ሹምባሽና አሥር አለቃ ካለፍርድ ቤት ፈቃድ ደሳሳ ጐጆውን ሲበረብሩበት ይናደዳል። የዳኛ ያለህ ብሎ ይጮሃል።

በየስሙላው "ነፃ ፕሬስ" እውነትን ሲዘግብ በአፈላማ እንደታየዘ ከባድ ወንጀለኛ 20,000 ብር ውለዳት ተብሎ ከርቸሌ ይገባል። እንደወፍ ዘርና እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ዶሮ በየአውዳመቱ ከስብሳብ ተጠልፎ ይታነቃል። ሲብስበት ያመራል፤ የገዛ ወገኖቹ ለሐቅ መታገሉን እያወቁ በሆዳምነት ሲያሾፉበት ይሰማዋል። ፀጌ ሰው ነው። ወፍም ወፍ እንደሆነችው እርሱም የሰው ሰው ነው። ቤቱ ሲቃጠል ቀድሞ የሚሸተው ለእርሱ ያፍንጫ ሥር ነው። እኛማ በርቀት የት የለሌ ነው ያለነው።

ግን እኮ ዶክተር ሐብተጊዮርጊስም፣ ዶክተር ጥላሁንም እንደ ዘጌ ወፎች ናቸው። እንደ ፀግዬም ናቸው። ከኢትዮጵያ ነው የበቀሉት። ሌላው ሀገር ወዳድም ከኢትዮጵያ ነው የበቀለው። የታሪክን ፈርጅ የሚመረምሩባት መነፅር ግን ይለያያል። ግን በመጠኑም ቢሆን እንደወፎቹ በጤፍና በሰናፍጭ ጥርጠራቸው ይለያያሉ። ሁሉም ሀገራቸውን ይወዳሉ። ፀግዬ ቅርብ በመሆኑና የኢትዮጵያ ኑሮንም በመኖሩ "ቤቴ ሲቃጠል ቀድሞ ነው የሚሸተኝ" ቢል እውነት አለው። እነጥላሁንና ሐብተጊዮርጊስም በናፍቆት ሩቅ ሆነው በሀገር ፍቅር ቢቃጠሉ አይፈረድባቸውም። በአንድ ቃል ሁሉም ወገን ናቸው። ችግሩ ወገንን በአንድ ላይ ማስተባበር ነው። ይህ በአጭሩ የጋራ ግምባር ይባላል። ወፎች በአንድ ላይ ይበራሉ፤ አንዱ ለአንዱ ኮምፓስ ይሆናል፤ አንዱ የአንዱን ጠረን አሽትቶ ይከተላል። እንደ ጥርኝ ሽቶውን እየረጨ የሚበር ወፍ አለ። ግን እኮ ወገን ነኝ የሚለው ተለያይቷል። መለያየት በእርሱ ብሷል። <u>ጐራ ከለየው ጠላት ይልቅ እርሱ ተለያይቷል።</u> በፍሬ ከርስኪ ተበታትኗል።

ውድ ወርቃየሁ!

በግምባር አፈጣጠር ላይ ማዕከላዊነት ያስፈልጋል። በነፃ አውጭነት ሰከርን እንጂ የሚመሠረተው የደቦ መድረክ ማዕከላዊ ግምባር ቢባል አሰባሳቢነቱን ይገልጣል። ወፍ እንኳ ሳይቀር ይሰባሰባል። ጥሬ የሚጠረጥረው በአንድነት ነው። ምዕራባውያን ማዕከላዊ ፖለቲካ (Centrist Politics) ይሉታል። አንድ የፖለቲካ አሰባሳቢ ድርጅት ሁሉንም ሲያቅፍ ሚዛናዊ ማዕከሉን (Fulcrum) እንደታርዛን ጦጣ አያናጋም፤ አለበለዚያ ሁላችንም ተገልብጠን ገደል እንገባለን።

በሌላም ጐኑ የፖለቲካ ገበናችን ሲገመገም

አንድ ወገን አንድነቱን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ካልገለፀና ከጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ጋር የራሱን ብሶት ካያያዘው እጅግ ያነጋግራል። "ለትግራይ ሕዝብ ከመለስ ዜናዊ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለህም" ይሉታል፤ "መለስ ዜናዊ ከተገለበጠ የትግራይ ሕዝብ ጉድ ፈላበት" ይሉታል፤ "እነዚህ የደርግና የኃይለሥላሴ ትምክህተኛ አማራዎች ትግሬ ለምን ገዛ ብለው ነው" የሚንጫጩት ይሉታል። እርሱም ሳይወድ በግድ ወገን ይለያል። በታሪካዊ አመጣጡና በፖለቲካዊ ፈርጅ ቢለያይም ሁኔታው ጀርመኖች የናዚን ፓርቲ እንደደገፉት ዓይነት ማለት ነው። ስለሆነም ለጊዜውም ቢሆን በምንም ዓይነት ሁኔታ ትግሬው ሕዝባችን በታቃዋሚ የፖለቲካ መድረክ ቢከፋውም እንኳ በውጭም ሆነ በአገር ቤት ሊሰባሰብ አልቻለም። "ትግራይና ኤርትራም ከኢትዮጵያ መገንጠል አለባቸው" የሚለውም አባባል የመጣው ይህንን መንሥዔ በማድረግ ነው። የአንድ ብሔር ብዙኃን ሕዝብ አማራጩን መንገድ ከዘጋ ሌላ መንገድ መኖር አለበት ከሚል ነው። ይህንን ያነሱ ምሑራንም በአንዳንድ ሁኔታ ሲታይ አይፈረድባቸውም፤ ሁሉም በር በመዘጋቱ የአማራጭ በር እያሉ ይጮሃሉ። እንደ ወፍ ማለት ናቸው። የትግራይ ሕዝብ አልደረሰላቸውም። "ትግራይና ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለባቸው" የሚለው መፈክር ሌላም ልሕቀ-ስሌት (Calculus) ያመጣል። በኢዩሮ ኦሮሞ (Euro Oromo) ሚሲዮናዊ ነፃ አውጭዎች አንድነትን ያስመታል፤ ለኦሮሚያ መፈክርና ለእርስ በእርስ ትንቅንቅ በሩን ይከፍታል፤ ማጥም ውስጥ ይዘን ይሰምጣል። ሁሉም ምሑራን የሚያነሱትን (ከአንድነት ጐን እስከተሰለፉ ድረስ) በማዕከላዊነትና በጥንቃቄ (Sensitivity) መመርመር አለብን።

ፀጋዬ ገብረመድህን በሀገር አፍቃሪነቱና በታጋይ ጋዜጠኛነቱ እጅግ ብወደውም እዚህም ያሉ ምሑራንን በሀገር ወዳድነታቸው አደንቃቸዋለሁ። ሁሉንም ምሑር አይደለም። ለማለት የፈለግሁት ገብቶሃል ወርቃየሁ። ስለዚህም ነው ሁሉንም ማሰባሰብ ያለብን። ፀጋዬ ገብረመድህንና የአሜሪካ ሀገር ወዳድ ምሑራንን በጠረጴዛ ዙሪያ በውይይት ለማምጣት ከቻልን የጋራ ግምባር ይሉሃል ይኼ ነው!! አንዱን ደግፈን አንዱን ከመታን "የትሮትስካይትና-የስታሊኒስት" የውይይት ፌዝ ይሆንና የቆምንለት ዓላማ ሁሉ ይቀለበሳል፤ ጠላትም ጉልበት ያገኛል። ስለሆነም አስታራቂ ሀሳብ ላይ ለእናት ሀገራችንና ለሕዝባችን ስንል ማተኮር አለብን። ንድፈ-ሐሳቡን (ቲዎሪውን) በኋላ አንድነት እንደገና ሲፈጠር እናኝከዋለን። ለወገን እንካሠላንቲያ ጊዜ የለም። እናት ሀገራችንን ጉድ ያደረግናት በድርጅት ርዕዮተ-ዓለም በመጣረብ ነው። መኢሶንን፣ ኢሕአፓን፣ ወዝሊግን፣ ኢዲዩን አስታውስ። ደርግን እኛ ምሳ እናደርገዋለን ስንል እርሱ ቁርስ አድርጉን የማታ ማታ የተገንጣዮች ራት ሆነ። በማዕከላዊነት፣ በፍትሕ፣ በመቻቻልና በመደማመጥ ለአንድነት ወደፊት መግፋት ይኖርብናል።

በአንዳንድ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ "የእፎይታንና" "የአዲስ ዘመንን" ጋዜጦችን ለመሸጥ በማይወዱን ወገኖች በኩል የሚደረገውን የርዕስ አንቀፅና የመስተያየት መጣጥፎችን ግርድ ከምርቱ መለየት ይኖርብናል። ጠላት የሚበረታው ወዳጅ ሲቀያየም ነው። ስለሆነም እኛ በእኛ ላይ መረባረብ የለብንም። የኢትዮጵያ ሬጅስተርም፤ ጦቢያም ያላቸው አጠቃላይ አመለካከት የአንድነት መፈክር ነው። "አንዱ በአንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ" እንዳይሆን የእኛ ነገር። ግን ጀምበር እንደገና መውጣቷ አይቀርም፤ አንድነትም እንደገና ይመሠረታል። ተስፋ መቁረጥ የለብንም። "ለተስፋ፣ ሕይወት ዝሩባት" ይላሉ ጂሲ ጃክሰን። (Keep the hope alive!) መቻቻል፣ መደማመጥና የአንድነት ፍልሚያ ከሌለ አሻቅበን የምናያት የፍትሕ የሽልማት ወርቅ ርቃ በሩቁ እንደምትበር ወፍ ዓይናችን እየተከተላት ሳለ ትጠፋናለች። ግን በፍጥነት እየሮጥን ከተከተልናት ከአድማሳችን አትጠፋም፤ ዓይኖቻችንም ከዚህች የአድማስ ሽልማት ጋር እየሮጡ ይይዟታል። ዓይን በሽልማት ላይ (Eye on the Prize) ይሉሃል ይኼ ነው። ግን ይህን ሁሉ መዓት እንወጣለን (We shall overcome)፤ ድሮ በተማሪዎች እንቅስቃሴ "እናቸንፋለን" እንል ነበር። አንዳንዶች አብዮታውያን ደግሞ "እናሸንፋለን" ይሉ ነበር። በጨቅላነታችን ጊዜ በቃል አመራረጣችን እንኳ "የመስመር ልዩነት" ነበር። አንዱ "ላብ አደር" ሲል ሌላው ወገን "ወዝ አደር" ይል ነበር። ያ ጊዜ ዛሬ ተለውጦ አንዳንዴም ሲያስለቅሰን አንዳንዴም ያስቀናል። ወርቃየሁ የአሁኑ ክርክራችን ወደዚያ ሊጠጋ ምንም አልቀረውም፤ ምንም እንኳ አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም። ነጭም ሆነች ጥቁር ድመት አይጧን ከያዘች ግብሯን ተወጥታለች ማለት ነው። ድመት ናት። ፀጋዬም ኢሕአዲግን ለአንድነት ሲል ከተቃወመ፣ አንዳንድ የአሜሪካን ምሑራንም ኢሕአዲግን ለአንድነት ሲሉ ከተቃወሙ ተፋላሚዎች ናቸው ማለት ነው። ሌላው ለአንድነት ሳይሆን ኢሕአዲግን ለሥልጣን የሚቃወምም አለ። እርሱን ግን የጠላቴ ጠላት ስለሆነ ብቻ ወገኔ ነው ልንለው አንችልም-እንደ ሌንጮ ለታ ዓይነቱን ነው። የከረረ ተገንጣይ ነው። ነገር ግን በአንድነት ኃይሎች መካከል የአደባባይ እንካሠላንቲያ አያስፈልግም። በግላዊ

ደብዳቤና በፍቅራዊ የስልክ ነቀፌታ ማስተካከል ይቻላል። ክርክራዊ ጉነጣ ለክርክር ብቻ መደረግ የለበትም። (Polemics for polemics sake is futile) ክርክራችን ከዚህ በላይ አድጐ የሞራል የበላይነቱን መያዝ አለበት። ከወገን ጋር አብረን ማልቀስ፣ አብረን መሳቅ አለብን። እንደ ወፎች አብረን መንጫጫት አለብን።

, አንጀቴ ወርቃየሁ!

ይህን የምለው የማዕረግ ቀሚስ እንደለበሰ ፍርደ ገምድል ዳኛ አንዱን ደግፌ ሌላውን ድባቅ ለመምታት አይደለም። እንዳንተው የሀገሬ ነገር ያቃጥለኛል። እኔም እንደ ፀጋዬ አነባለሁ። ሲብስብኝ ስህተት ውስጥ ለመግባት ይቃጣኛል። በኢሕአዲግ ስም ትግሬውም ላይ ለመቆጣት ደሜ ይፈላል። መልሼም በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እልና ራሴን ወቅሴ የብቸኛ ሕሊናዬን አነፃለሁ። ትግሬም እንደዘኬ ወፍ ከአንድ ምድር እንደበቀለ እረዳለሁ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ አንዳንዱ ከባራተዬሪ አስካሪ ጦር ጋር ቢሰለፍም ይህንን በጅምላ ወስጄ ሁሉንም ትግሬ አልጠላም። ጥቂቶች ኃይል ወዳለው ቢያጋድሉ ሁሉንም አልነቅፍም። መወናበድም አለ። ከጉሳ ፖለቲካ ባሻገር አረጋዊ በርሔ እንዳለው ትግሬውን የሚያወናብዱት በማስፈራራት ነው። መለስ (ለገስ) ዜናዊ ከተገለበጠ የትግራይ ሕዝብ ደህንነት (security) ይጠፋል ብለው ያስፈራሩታል። የፈራ ሕዝብ በቅስቀሳ ስሜተኛ ይሆናል። በቆንጨራና በጩበጣ ውጊያ የሚጨፈጨፍ ይመስለዋል። እዚህ ላይ አረጋዊ በርሔ እንዳለው ፕሮፓጋንዳ(ቡጋንዳ) በሁሉም በኩል ሰርቷል። የፈራ ሕዝብ ሊተባበር አይችልም። ይህንን ፍርሐት ማስወገድ አለብን። ለግንባር ድልድዩን ከአሁኑ መጣል ይኖርብናል። ይህ የአርቀ አሳቢ ዜጋ ሁሉ ምኞት ሊሆን ይገባል። ምኞት ግን ተግባራዊ የሚሆነው በሥራ ሲተረጐም ነው። ወፎች በተፈጥሮ ባሕርይ (instinct) ርቀት ያለው የአየር መንገድ ጉዞ ተጉዘው ግባቸውን ሊመቱ ከቻሉ፤ እኛ እንዴት የእነርሱን ያህል እንኳ አንስለጥንም?

ወፍም አንዳንዴ የሚያሾፍ ይመስላል። የወፍንም ጠባይ ተንተርሰን ምሳሌያዊ ትዕይንትን እንደልብ ወለድ መድረስ እንችላለን። የቀበና ወፍ በእንደባጉና ወፍ ይስቃል። የትግሬው ወፍ በለስ በመቀንጠቡ ከጂማው የቡና ፍሬ መንቻፊ እርግብ የተለየሁ ነኝ ይላል። በጌቶና በባሪዮ ያሳማ ሥጋ ፍርፋሪ የሚለቅመው አሞራ ከካውንቲው የሮማ ሞራ ለቃሚ በራሪ እኔ ልዩ ነኝ ይላል። የጐንደር ወፍ የሰሊጥ ፍሬ በመተምተሟ ከአዲስ አበባ አክናፋት የተሻልኩ ነኝ ትላለች። ወፍ እንደአገሯ ትሞሃለች። የአካባቢው ሁኔታ አይቀየር ኑሮዋን ለግሷታል። የዘኬ ወፍ በጠባይዋ የሱልልታ ወፍ አይደለችም። ወፍም ተለይታለች፤ እንደአገሯ ትሞሃለች፤ የዘኬ ወፍ። ልዩ ነኝ በማለቷም ይሰማታል፤ ትጨነቃለች። ወፍ እንደአገሯ ትሞሃለች። እንዲህም ብላ ታለቅሳለች–

"ጌትዬ የት ልደር፣ ጌትዬ የት ልደር፣
ድንጋይ ላይ ብቀመጥ እባቡ መከራ፣
እዛፍ ላይ ብወጣ አሞራው መከራ፣ ...
ጌትዬ የት ልደር! ጌትዬ የት ልደር!

ከአንድ ወጥ ወይም ዘር(species) የመጣች ወፍ ተጨንቃለች። የካፒታሊዝም፣ የትግሬ፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጥቁር ... የነጭ ወፍ አዝናለች። የት ትሂድ እውቀቱ እስከሚገለፅላት ወፍ እንደ ሀገሯ ትሞሃለች።

ለመሆኑ ያገር ልጅ ወርቃየሁ ይህንን ሁኔታ እንዴት ተረዳህ? እንደወፏም አማራም፣ ትግሬም፣ ጉራጌም፣ ኦሮሞም ተጨንቋል፣ አዝኗል። በአካባቢውና በየጉሳው ይዘምራል። በአንድነቱ ተዘናግቷል። ግን እርሱ ከወፎች ሁሉ የበላይነት አለው። ለምን ማለት ነው። ያስባል፣ ያሰላስላል፣ የፖለቲካ እንስሳ ነው። ከወፎች ይልቅ እርሱ የላቀ ነው። አውቆ እንደ ወፍ ከተባበረ መንግሥትን ይገለብጣል። ከነቃም የመሪውን መቀበሪያ ጉድጓድ ይቆራል። በአንድነት ኢኮኖሚው፣ ፖለቲካውና ሕብረተሰቡ እንደሚሻሻል ያውቃል። እንደተበታተነ ወፍ ብቻውን ስለሚዘምር፣ በቅራኔ ስለተበታተነ፣ በጥላቻ መርዝ ስለተለከፈና ብሎም ወንድሙን ስለጠላ አዝኗል፤ አፍሯል። ምንተ እፍረት ሆኖበት ነው እንጂ ቃሉን መልሶ ቢውጠው በወደደው።

ትግሬው፣ አማራው፣ ኦሮሞው ተጠላልቷል። እንደወፍ እንደየሀገሩ ይዘምራል። ትግሬም አዝኗል። ፀጋዬ ገብረመድኅን እርአያም እንዳለው ሁሉም የተፈጠረው ከአንድ መሬት ነው። ኤርትራዊውም አዝኗል። ወደጠላው አዲስ አበባ ይጓዛል። እጅግ አፍሯል።

አንዳንዱም የገዛ ቤቱን ተጠራጥሯል። ከትግሬና ከኦሮሞ ጋር አብሮ በልቶ ልጆቻቸውን ያገባው አማራም ልቡ ሸፍቷል። ትግሬዋም በጉረቤት የዘር ቅስቀሳ ስለተነካች የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው የእኔው ጉሳ ነው በማለት መለየት ጀምራለች፤ በፖለቲካም ሰልጥናለች። ባል ወጣ ሲል ከወገኗ ጋር መወያየት ያምራታል። ችግሯ ሁሉ የአድጊ አማራ ነፍጠኛነት ሆኖ ስለተነገራት ልጆቿንም ሳይቀር ትቀሰቅሳለች። እንግዲህ በቤተሰብም መካከል መራራቅ መጣ ማለት ነው። ግናም አይምሰልህ እርሷም ውላ ሳታድር ይከፋታል፤ ... የዘር ቁርጥማትና ምዝመዛ ቀላል ስላልሆነ እጅግ ያማታል።

ኦሮሞውም ያመዋል፤ ትግሬውም፣ አማራው ያመዋል። አንዳንዱም አንድነት ይቃጣዋል። የውስጥ ሕሊናው፣ በማንም የሐሳብ

ፖሊስና “በነፃ አውጭ” ፌሮ ያልታሰረው ጥሬ የህሳብ መንፈሱ ለራሱ የውስጥ ደወሉን ያሰማል። ሰው እንደገደለ ሰው ነው። ኃጢአቱ በውስጡ ይጮሃል፤ ስህተቱ ይገለጥበታል። እነርሱ ሲለዩኝ ለምን እለያለሁ ይላል። ከእነርሱ ራሴን ካለየሁ እኔም ተገንጣይ ነኝ ይላል። እንደ ፀግዬ ገብረ መድኅን አርአያ የውስጥ ሕሊናው ይደውላል፤ ደውሎም በራሱ አይወስንም፤ ለሌላውም ያበራል። ፀጋዬ ጉሽ! ግን አንዳንዴ ምሑር ያናድደኛል። “በነፍጠኛ አማራ” ስምና “በጠባብ ትግሬ ስም” አለፍ አለፍ ብሎ ያምታታል። አትፍረዱበት፤ እርሱም መሮታል። ከሁሉም በኩል ብዙኃኑን ሕዝብ የነፃ አውጭዎችና የሥርዓቱ መደብ ደጋፊዎች አድርጎ ያቀርባል። ድሃ ኢትዮጵያዊ ትግሬ አለ። ትግሬም ኢትዮጵያዊ ነው። ትግሬም በስህተቱ በውስጡ ይቃጠላል። ጫማ የሌለው የሸዋ፣ የጉንደርና የጉጃም አማራ እንዳለ ጠንቅቆ ያውቃል። እጅግ ብዙኃኑ አማራ ጭቁን ነው። ረፋድ መንገድ ጌሾ ተጭኖ በቅዳሜ ገበያ በጨው ለመለወጥ የሚገሰግሰው ባለሥንጥቅጥቅ እግረ ቆርማዳ አማራ ብዙ ነው። ለነፃ አውጭዎች ከዚህ በፊትም ለነስባጋድስ ያለውን ግማሽ ጥማድ በሬ ገብሮ ያንን ለዘመናት የተበዘበዘ ጭንጫ መሬት በእጁ እንደ ዝንጀሮ የሚጭረውን ትግሬ ሆድ ይቁጠረው። እነ አቦይ ስብሐትና እነመለስ ዜናዊ ቢያወናብዱትም እያደረ ትግሬም የነቃ ይመስላል።

እነራስ ጉበናን እያወገዘ የኦሮሞያን ክልል ዘላለማዊ ለማድረግ የሚጥረውም የነሌንጮ ለታና የሌሎችም ሚሲዮናውያን ረጋ ሡራሽ ስልጡን መሰል ማርክሲስት የብዙኃኑን ኦሮሞ ቆሽት አሳርሯል። ኦሮሞም ቅራኔው ጉሽሞታል። ይህም በእንግሊዝ፣ በጀርመንና በአሜሪካ በሕዝብ መዋጮ ማርቸዲስና ቢኤም ደብልዩ የሚነዱትን የቤተሰብ ኦሮሞ ዘመናዊ አርሲቶክራሲ አይመለከትም።

ኢትዮጵያዊውም ነዷል። ለአንድነት ታግሏል። ምንም ሳይኖረው በኢትዮጵያ ከሌላው የተለየ ሳያገኝ የሚታገለውና የታገለው አማራው ነው። ሁሉም መንግሥታት ሁሉንም ጨፍጭፈዋል፤ ሁሉንም መተዋል። ቀይ ሽብር የእኩልነት ዕድልን (Equal opportunity) ለሁሉም ሰጥቷል። የአንድነት ኢትዮጵያዊ ኃይልም በድርጅቶቹ አዝኗል። ሁሉም ተርመስምሷል። ሁሉም ቀውሷል። ሁሉም confused ሆኗል። ከሁሉም አቅጣጫ የሚተኮስበት የርዕዮተ አለም የጥይት እሩምታና ዘረኝነት አወናብዶታል። እንደ ሺህ ፍየልና በግ በአራት ማዕዘን ታጥሮ የመትረየስ እሩምታ ሲዘንብበት እንዴት በድንጋጤ እንደሚርመሰመስ ግልፅ ነው። ሁሉም መንገዱ ጠፍቶበት ይጋጫል። ኤርትራዊውም ተለይቻለሁ ብሎ ለአፍታ ቢፈነድቅም ወጣቱ ክፍል ወደ አዲስ አበባ እየጎረፈ ነው። የጠላውን ዘመናዊ የአማራ የባሕል(Culture) እምብርት አዲስ አበባን እንደገና ወዷታል። በቅራኔው ያፈረ ይመስላል። በግልፅ ባይናገርም የመጣው የዘር ጥላቻ እንደጎዳው ያውቃል። ከደም ሀገርና ከጭቅጭቅ የጉሳ ፖለቲካ ባሻገር አንድነትን ለማየት የሚያስችለው ሁኔታ በሚስጢረኛነቱ በውስጡ እሳት እየጫረበት ነው። የተጫረ እሳት ይነዳል፤ መንቦግቦጉ አይቀርም። ግን ጊዜ ይወስዳል። ኢሳያስ፣ መለስና እነ ሌንጮ ለታም ምንተ እፍረታቸውን ነው እንጂ የሚያራምዱት የጉሳ ፖለቲካ እንደማያዋጣቸው ያውቃሉ።

ወንድም ወርቃየሁ!

ለአዲስ ሃሳብና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ልብን የሚማርክ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ-ተገንጣይ፣ ብሔራዊና ሁሉን አቀፍ ግምባር መምጣቱ አይቀርም። ጠንካራ አመራር ሊሰጥ የሚችል አስታራቂ አመራር (Leadership) መፍለቅ ይኖርበታል። ይህ እንዲሳካ ትግሬም በትግሬነቱ፣ ኦሮሞውም በኦሮሞነቱ፣ አማራውም በአማራነቱ መታየት የለበትም። የነንክሩማህንና የነማንዴላን መርህ ይዞ በዘረኞች መቃብር ላይ አዲሲቱን ፍትሐዊና ፌዴራላዊ ኢትዮጵያ የሚመሰርት ግምባር በየቦታው እንዲመሰረት ሁሉም ጥሪ ማድረግ አለበት። የሁሉም ሀዘንና ጥርጣሬ፣ በበጎ ፈቃደኝነትና በፍቅር ይተካል።

ወንድም ፀጋዬ ገብረመድኅን አርአያ እንዳለው ሁሉም የተፈጠረው ከዚህች መሬት ነው። ለዓለምአቀፍ መተባበር(global cooperation) ጎሰኝነት መልስ አይደለም። ጎሰኝነት እንደ ኤይድስና ነቀርሳ ሕዝባችንን የሚጎዳ በሽታ ነው። ሦስተኛ ዓለም በነጩ ዘረኝነት ተጎድቷል። ሁላችንም አዝነናል። የማታ ማታ ጥላቻ ፍቅርን አያሸንፍም። እንደጠላቶቻችን እኛም ከጠላን ተሸንፈናል ማለት ነው። አዲሱ ስትራቴጂ ይህን ማስተዋል አለበት። ሁላችንም ወድቀናል፤ ተላልጠናል፣ ተመልጠናል። በሀገር ላይ ቸነፈር፣ አስረሽ ምቺው ሲደርስና ሁሉም ራስ ወዳድ ሲሆን ኃይማኖተኞች ከእግዚአብሔር ፀጋ ተለይተን ወድቀናል ይላሉ። (We fall short of the Glory of God)

ውድ ወርቃየሁ!

ይህም ሲባል ዘረኞችን፣ ጉሰኞችን፣ ሰላዮቻቸውን፣ ጋሻ ጃግሬዎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን እንቃወም ማለቴ አይደለም። እስከሞት ድረስ መታገል አለብን። አፍራሽን ካልመከትን እኛም ፈራሶቹ ነን። የኢትዮጵያም የአሁን መፈራረስ ቋሚ ይሆናል። ግን ከታሪክ ተጠያቂነት ለማምለጥ ሁሉንም ቀዳዳ መድፈን አለብን። ሕሊናችን መንፃት አለበት። እጅ መስጠት የለብንም። ግን ከጭለማ መሿለኪያ

ባሻገር ብርሃን አለ። (There is light at the end of the tunnell) እዚህ ብርሃን የሚያደርሰው ጉዞ የተራቀቀና በእውነት ላይ የመሰረተ መሆን አለበት። የአንድነት ኃይል የሞራል የበላይነቱን (the moral highground) መያዝ አለበት።

አዎን ዘመንና የኢትዮጵያ ድክመት ከለገሳቸው ጥቂት የመንግሥትን አመራር ከጨበጡትና ሥልጣን ካስከራቸው የጐሳ አይዲዎሎጂ ካድሬዎች በስተቀር ትግሬው ደንግጧል። ከአክሱም አቢይ አዲ፣ ውቁሮና አደዋ ለእነዚሁ ምርጥ መደብ ከተሻሻለው የንግድና አድልዎ ካለበት የበጀት ስልጣኔ በመለስ ብዙኃኑ ያገኘው ነገር የለም። ኦሮሞውም በግልባጩ እንደዚሁ ነው። ጥቂት የአመራር አባላትን ይዞ ለጊዜውም ቢሆን በክልልና በጐሳ ስም እንደጣልያኑ ጄኔራል ባራትዬሪ ከፋፍሎ መግዛት ይቻላል፤ ግን ይህ ዘለዓለማዊ አይደለም። 'ሆዳም' አማራም ሳይቀር ከፍቶታል። ነገ ከሥልጣኑ እንደሚባረር ያውቃል። ታምራት ላይኔም ተሸሯል። እርሱም አዝኗል። ለሚያልፍ ጊዜያዊ ሥልጣን ብዙ ቀጥፏል፤ ብዙ ዋሽቷል።

ሁሉም አዝኗል። ኢሕአፓውም፣ መድህኑም፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አገር ወዳዱም ተክዟል። ኢዲዩም ነዷል። ሁሉም ግን የመጣው ከአንድ መሬት ነው። ስለዚህም ሁሉም ተነክቷል። ያልተዘጋ ቤት፣ ያልተቃጠለ መንደር፣ ያላዘነ ቤተሰብ የለም። ለዚሁም ነው ዐቢይና ትልቅ ግምባር በሕዝብ ብሶት ላይ የተመሠረተ ስብስብ የሚያስፈልገው አፉን አውጥቶ ባይናገርና ቢፈራራም ሁሉም ይፈልገዋል። ሁሉም አፈርኩኝ ብሏል። እንደ ጃኖራ ባለገምባሌ ጉረምሳ አፈርኩኝ ብሎ ሁሉም ጠበንጃ ጉድባ ሥር ደግኗል። ግን የልቡ ትርታ ጨምሯል፤ ደንግጧል፤ ከዚያ ጉድባ አይዞህ ምን ነካህ ብሎ በፍቅር የሚጐትተው መሪ ይፈልጋል። የሁሉንም ብሶት የሚያዳምጥ መሪ መሆን አለበት። አፍሮ ሌላው ላይ ተኩሶ ራሱን እንዲገድል መንደሩንም እንዲያጠፋ ማበረታታት አይገባም።

ልጅ ወርቃየሁ!

መሪውም ግምባሩም ጠንካራ መሆን አለበት። ካስፈለገ በብልሐት ኃይል መጠቀም ይኖርበታል። ለፈራ፣ ላዘነ፣ ለደነገጠና፣ ለተከዘ ሕዝብ ጠንካራ መሪ ያስፈልጋል። በጐሰኞች ላይ የሚያምፅ፣ በአንድነት ፀሮች ላይ ምህረት የሌለው ሀገር አልሚ መሪ፤ አማራም ይሁን ትግሬ፣ ኦሮሞም ይሁን ጉራጌ ... ሌላም ሌላም ይሁን፣ ሕዝባችንን ከድኅነት ከድንቁርና ከዘር ጥላቻ የሚያላቅቅ። አዎን እምባውንና ብሶቱን በእኩልነት የሚያብስና የሚረዳ፣ ድጋፍ ያለው መሪ ያስፈልጋል። ዛሬም የወሎች፣ የእግዜር፣ የአማራ፣ የኦሮሞና የትግሬ ክርክር ቀጥሏል።

ፀጋዬ ገብረመድኅን አርአያ እንዳለው ሁሉም የተፈጠረው ከዚህች መሬት ነው። እንደመሬቱም ወጣ ገብነት የሕዝቡም የባሕል መልክዓ ልባስ የተለያየና ወጣ ገብ ነው። እኛም እንደሀገራችንና እንደወፎች እንዘምራለን። ይህን የሚነሳን ማንም ጉልበተኛ ጂንጂስካን የለም። ብቻችሁን አታልቅሱ፣ ብቻችሁን አትዘምሩ የሚለን የዓለም አቀፍ ጉረኛ ሥርዓት የለም። እኛም እንደገበናችን ብቻችንን እያለቀስንና እየሳቅን መፍትሔያችንን ለራሳችን ጥቅም እንፈልጋለን። መዝሙራችንን ለመዘመር፣ ልቅሶአችንን ለማልቀስ እባካችሁ ተዉን እንላለን! (Please leave us alone to sing our songs)። ወፎችም፣ እግዜርም፣ አማራውም ትግሬውና ኦሮሞውም ዛሬም በየሕሊናቸው ይከራከራሉ። ነገር ግን ለጥፋት እንደሚቃጠል የደማሚት ገመድ ጊዜው እያጠረ ነው። ከመፈንዳቱ በፊት ሁሉም ኢትዮጵያዊ አብሮ ማዘንና መተከዝ አለበት። ለብቻ ማልቀሱ አያዋጣም። አብሮ መፍትሔ መሻቱ አይበጅም ጃል! አብሮ ካሰላሰሉ መፍትሔውም አብሮ ይገኛል። ወፎችን ተመልከቱ።

እንደወፎች ትንሽ ላንጐራጉር መሰለኝ። ወርቃየሁ! ለዚህ ግጥም ወፍ እንዳገሩ ይዘምራል። ክራሩና መሰንቆው በአንተ ያምራል፤ ከባሕር ማዶ አትጠብቅ።

## ዐቢይ ክርክር
## (የወፍ ጉራማይሌ)

ወፍ፦ "ጌትዬ የት ልደር
ጌትዬ የት ልደር
እዛፍ ላይ ብሰቀል አሞራው መከራ
ድንጋይ ላይ ብቀመጥ እባቡ መከራ
ጌትዬ የት ልደር
ጌትዬ የት ልደር"

እግዜር(ያሕዌ)፦ ከዘጌ ሳኖርሽ ከጣና ባሻገር፣
ስርቻ ወትፌ ክንፍሽን ስፈጥር፣
ደግሞ ምን ጉደለኝ ብለሽ ተንጫጭተሻል፣
ፈጣሪን ለመድረስ በጉም ላይ በረሻል፣
ቅጣት ይገባሻል፣
ሰይፌም ይቀስፍሻል።

ወፍ፦ ላቲን ሳልናገር እስፔራንቶ ሳልገጥም፣
በክልል በወሰን በጐሳ ሳልፈርም፣
ለምን ጌታ እኔን ቀልጨ እንድልም፣
ሴት አሞራ ልክህ እንቁላሌን ታውድም።

ትግሬ፦
እባካችሁ ተረዱልኝ እኔም እኮ ተገርፌያለሁ፣
በጀርባዬ ጠበሳ ለዘመናት አልቅሻለሁ።
እኔም ስክር ምንተ—እፍረቴን፣
እናንተም ስትከሩ፣

የፉክክር ቤት ሲሆን፣ በየቡድኑ ሲካረሩ፣
መሪዬ አገር አውድሞ፣ ሞረሽ ሲሆን ቅጥአምባሩ።
ተቆጥቼ ባርባር ቢለኝ በገበናዬ አትዘኑብኝ፣
ለይታችሁ በጣት ጠቅሳችሁ
ትግሬ ትግሬ ነው አትበሉኝ።

ኦሮሞ፦
ቤት ካሉት መቃብር ይሞቃል፣
ግብራችሁ እንዴት ይረሳል፣
ተከድኖ ቢበስል ይሻላል።
ደግማችሁ አታሳዝኑን፣
ቂማችንን በልብ አድርገን፣
በክልል እንለያይ፣
ማዶ ማዶ እንተያይ።

አማራ፦
ሥቃይ ለእናንተ መጥቶ፣ እኛን መቼ ጠቀመን፣
ከእናንተ የሣር ቤት የተሻለ
የቱን ሕንፃ አገኘን፣
ከእናንተ ረሃብ የተለየ
የቱን ሎማ ኬክ ቆረጥን፣
ከእናንተ ልጆች የተለየ
መቼ ቀይ ሽብሩ ማረን፣
ሕዋስ ለይቶ አንጓሎ
መቼ ቱበርኪሎስስ ተዉን
ተስቦ ሽቅብ አይቶ
መቼ እናንተን አልነካም አለን፣
የገገር መደብ እናንተን ጉድቶ
መቼ ለእኛ አጉረስን።
ከስቃይ ምንጭ የምንጠጣ
እንዴት በውሸት እንለያይ፣
እጅግ የሚዘገንን ስቃይ፣
የሚያስለቅስ የደም ብካይ።

እግዜር(ያሕዌ)፦
እኔ ዳኛው አቃቤ ሕግ ጠባችሁን ልገላግላችሁ፣
ከየት እየለሌ ብርሃን ዘመን
የጊዜ ተጓዥ ፈጣሪያችሁ፣
ስፍኒክስ ሳይሠራ፣ የጊዛ ፒራሚድ ሳይቆለል፣
ለዘመናት በሙሴ ጽላት፣ነበርኩ እኔ ያሕዌ —
ጠበኞችን የምገለግል።
ፍጥረትን ሁሉ የፈጠርኩ ጊዜን በጊዜ የምሽር፣
እስቲ በሉ ተወቃቀሱ፣ ስለእውነት እንመስክር፣
እኔ ዋቃ እኔ ጉይታዬ፣ እኔ አላህ እኔ እግዜር።

ትግሬም ከመሆናችሁ በፊት፣
ሰውም አድርጌ ፈጠርኳችሁ፣
አማራም ከመሆናችሁ በፊት፣
ሰውም አድርጌ ፈጠርኳችሁ፣
ኦሮሞም ከመሆናችሁ በፊት፣
ሰውም አድርጌ ፈጠርኳችሁ፣
ቆዳችሁንም አጥቁሬ
በአፍሪቃ ቀንድ በተንኳችሁ፣
ከጉሳችሁ በፊት የነበረ፣
ሰውነታችሁ መች ይናዳል፣
ጥቁርነታችሁ ተፍቆ፣ መቼ ቀለማችሁ ይሻራል።

በሉ ተረዳዱልኝ ሌላውንም አስተምሩ፣
ሁላችሁም ኃጢአተኞች ናችሁ፣
"እኔ እውነተኛ ነኝ" — ብላችሁ አታቅራሩ።
ይቅር ብያችኋለሁ፣ የምትሠሩትን አታውቁትም፣
የበለጠ ሥቃይ ሳይመጣ፣ ውይይቱ ይፈጣጠም፣
አሻፈረኝ ካላችሁ፣ ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፣
ወገናችሁ ሥጋችሁ ሁሉ፣
እንደአፈር ይፈራርሳል፣
በእሳተ ጉመራ ይነዳል፣
በቸነፈር ይወድማል፣
በጦርነት ይማገዳል።


ወፍ፦ ጌትዬ የት ልደር፤ ጌትዬ የት ልደር
ለማን አቤት ልበል፤ ለማን ይግባኝ ላድል!!

ውድ ወርቃየሁ፣ ይህንን ግጥም ስጨርስ ትንሽ ሽለብ አደረገኝ ቅዠት ውስጥም ገባሁ። ፈጣሪንም አየሁት። ያሕዌ! ከእኔ ጀምረህ ይህን መጥፎ የሰው ልጅ በምድር ላይ ለምን ፈጠርክ አልኩት። እርሱም የምትናገረውን አታውቅም አለኝ። አንድ ሰውም ተነስቶ "ጌታ ካንተ ጋር መስማማት ማንም አይችልም። ለምን ከሰይጣን ጋር ተስማምተህ አትሰራም" አለው፤ "ሰይጣኖችን አስቀይመሃል" ብሎ ተቆጣው። ያሕዌም አለ "በዚህ አነጋገርህ አንተ ግብዙ መንግሥተ ሰማያት ከምትገባ ግዙፉ ሰይጣን እንደግመሉ ምሳሌ በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀለዋል" አለው። ጌታም ቀጠለ "አንተ ተንኮለኛ ሌሎችን ከመውቀስ ይልቅ ራስህን አስተካክል። በመጀመሪያ በዓይንህ ላይ ያለውን ጉድፍ አውጥተህ የሌሎችን የዓይን ውስጥ ቆሻሻ ተመልከት" አለው።

ፈጣሪም ወፍን፣ ትግሬን፣ አማራን፣ ኦሮሞን፣ ነጩንም ጥቁሩንም በመፍጠሩ እጅግ ተፀፀተ። መጋረጃውንም ዘግቶ አነባ። እንባውም እንደኖህ ጊዜ ጉርፍ ፍጥረትን አጠፋ። መጀመሪያ ተሳስቼ ነበር አለ። ይህ ትውልድና የአሁኑ ተፈጥሮ ወድሞ እንደ አዲስ ካልተጀመረ ተፈጥሮ አስደሳች አይሆንም አለ። የመጀመሪያ አሪት ዘፈጥረት አብዮትን እንደገና ለወጠው። ሪቮልሽንም አካሄደ። እንደማርክስ አብዮታዊ ሆነ። የሰውን አንጉል አውጥቶ በወፍ አንጉል ተካው። ይህም መልካም ነው አለ። የጉሳ ጥላቻና ጦርነትም እንደሚቆም ተረዳ። ለወፏም እንደተፈጥሮዋ መልካም አንጉል ሰጣት። ወፏም ዘመረች። ፀጋዬም ወፍ ሆኖ እያንጉራጉረ እስክስታውን አቀለጠው። በደስታ እንደወፏም ሊበር ቃጣው። እግዚአብሔርም ይህ መልካም እንደሆነ አየ። ከእንግዲህ ወዲህ የእውነትና የፅድቅ ቃል የቤዛን ግምባር ይመሠርታል አለ። ፍጥረታት ሁሉ አጨበጨቡ። ወይ ጉድ ወርቃየሁ ደግሞ ስለአሪት ዘፍጥረት ልቃዥ! ከእንቅልፌ ስነቃ ገረመኝ።

እስቲ ልብ ሠጥቶን ቸር ይግጠመን!
ገብርዬ፣ አትላንታ/ጆርጂያ

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



## የአየር መንገዳችን የደህንነት ሰቆቃ እስከመቼ?

የዛሬ 50 ዓመት በዲሲ 3 ከአዲስ አበባ ካይሮ የተጀመረውና አንጋፋነቱን የተላበሰው የአየር መንገዳችን የበረራ ደህንነት ቅንጣት ታህል ስንኩል ገፅታዎች ሳያጋጥሙት የዕድሜውን ከግማሽ በላይ ክንዋኔዎች የዓለም አቀፍ አቪየሽንን ትኩረት የሚስቡ የነበሩ መሆናቸውን የጉዞ ሰሌዳው መዝገብ በጥቁር እርሳስ ያልተዘገበ መሆኑን ይናገራል። ዛሬ በጡረታ የተገለሉ አብራሪዎችም የሰማይ ላይ የስንጠቃ ጉዞ ለደቂቃ የማያወላዳ የጥንቀቅ ሰዎች ሥራ በዚህ ላይ ማስመዝገባቸውም የእነርሱንም ታሪክ አፋችንን ሞልተን እንድንናገር መንገድ ከፍቶልናል።

ዛሬ በብዙ ዓይነት መንገድ አድጉአል እየተባለ የሚወራለት አየር መንገዳችን ግን የእንቅስቃሴያችን ዕድገት አጋች በሆነ የበረራ ደህንነት ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ቁጥር አምስት የዓመታት የዲሞክራሲ መንገድ ለዚህ የሰማይ ላይ ደህንነት ያበረከተው አስተዋፅኦ ባይኖርም እስከዛሬ ተደፍሮ በማያውቀው የአየር በራችን መዝጊያ ሽብርተኝነት እያንኳኳ ሲሆን ተከፍቶለት ከገባ በኋላም በቁጥር ስድስት ጊዜ በሚሆን ወቅቶች አውሮፕላናችን ተደፍሯል። ምንም በማያውቁ የዋሃን ተጓዦች ላይ ሽብርተኝነት እየጨፈረባቸው ነው።

በአገር ውስጥ በረራ ድሬዳዋ፣ አሶሳ፣ ጉንደር የተካሄዱት የጠለፋ ድራማዎች የተከናወኑት በፖለቲካ ሽኩቻ በሚመጣ የወኔ ጫና ቢሆንም አየር መንገዱ ላይ ዕምነት የሚያሳጡ የተደጋጋሚ ድርጊቶች በመሆናቸው የበረራ ደህንነቱን ግምት ውስጥ የሚጥሉ፣ የአየር መንገዳችንን የአለም አቀፍ የገበያ ውድድር ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ከፍተኛነቱ ግንዛቤ ውስጥ ያለመግባቱ ሰላሙን የሚያደፈርስበትን መንገደኛም ህይወት አደጋ ላይ መጣል ነው።

ይህንን ሁሉ የዝባዝንኬ፤ ወጥ ያልሆነ አሠራር ያጋለጠው የጠለፋ ድራማ ደግሞ ባለፈው ህዳር 14, 1989 ከአዲስ አበባ–ኬንያ–አቢጃን በበረራ ቁጥር 961 የተመዘገበው ቦይንግ 767 ላይ የደረሰውና ኮሞሮስ ደሴት የተከሰከሰው አውሮፕላን ጉዳይ ነው። በሀገራችን ታሪክ እጅግ አሰቃቂ በተባለለት በዚሁ አደጋ 175 ተሳፋሪዎች የነበሩ ሲሆን 125 አልቀዋል፣ 50 ተርፈዋል። በአሁኑ ሰዓት የበረራ ደህንነት ጭራሽ የለም እስከሚያስብል ድረስ ያደረሰን የሰው ልጅ ጠላቶች በሆኑ አረመኔዎች በተከናወነ የጠለፋ ድርጊት ብዙ ቤተሰቦችን የኃዘን ማቅ ያስለበሰ፣ እንባ ያራጨ፣ ኃዘናችን ከልባችን እንዳይፋቅ፣ ጠባሳው የማይለቅ የዕኩይ ተግባር ምሳሌ ነው። በዚህ ዓይነት የአየር መንገዳችን የደህንነት ሰቆቃ እስከመቼ? በሚለው መጠይቅ ማን ማን በተጠያቂነት ውስጥ ይሽከረከራሉ?

የአየር መንገዳችን ማኔጅመንት በአየር መንገዱ ሠራተኛ ማህበር በፖለቲካ ሁኔታ ሳቢያ የሚፈጥረው ጫና በተከፋፈለ ልብ የሚያዋልለው ሰራተኛ፣ ይሄን የመሰለ አደጋ ደግሞ ተጨምሮበት የብዙ ሀገር መንገደኞችም በአየር መንገዳችን የጉዞ መቅረት (መሰረዝ) ጭላንጭሉንም ሲያሰፋው ዕድገቱ የቱ ላይ ነው ታዲያ? የጠላፊዎቹስ ማንነት በገሃድ እንዳይታወቅ የድብቁ ፋይል ሚስጥራዊነት ለምንድነው? መልሱን የሚቾቹ ቤተሰቦችና መላው የአየር መንገዱ ተጠቃሚ በጉጉት የሚጠብ ቀው ነው። በዚህ አጋጣሚ በዚህ አረመኔያዊ ድርጊት ህይወታቸውን ላጡ ሰዎች ነፍሳቸውን በገነት እንዲያኖርልን ለቤተሰቦቻቸውም መፅናናቱን ይስጣቸው እላለሁ።

አገኘሁ እንግዳ – ከአዲስ አበባ

## ለጠቅላይ ቢሮ ወኪል

ባለፈው ደብዳቤህ ከአሜሪካ ወደ ሀገር ቤት ስለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ጉብኚዎች የተሰማህን እሮሮ አብራርተህ ጽፈህልናል። በእርግጥ የዘገብካቸው ትዝብቶች በድርጊታቸው አልተፈፀሙም አልልም። እዚህም ቆሻታችንን የሚያሳርር ሞልቃቃ አልፎ አልፎ ታያለህ። ከዚህ በፊት ወንድም ይግለጡ ለሀገር ልጅ ወርቃየሁ ደብዳቤ ሲፅፉ እንዳሉት ከደብዳቤ ይልቅ እኔም ስለአንዳንዶቹ ጠባይ በፊልም(ቪዲዮ) ቀርጨ ለእናንተ ባሳይ ምንኛ ደስ ባለኝ። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ የአንጉል ድሐና እንከፍ በቁጥር እጅግ ጥቂት ነው። አብዛኛው በአሜሪካ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ባይሆንለት ነው እንጂ ስለሀገሩ ነጋ ጠባ የሚያለቅስና የሚጨነቅ፣ በዚህም ሀገር ስለ ፍትሕ የሚታገል፣ ከእለት ኑሮውም ቆርሶ ሌት ተቀን ስለኢትዮጵያ የሚፋለም አኩሪ ወገን ነው።

ምንም እንኳ አንተ እውነቱን ብትናገርም ጠላቶቻችን ደግሞ አንዱ ዓላማቸው የውጭውን ትግል በማጣጣል፣ በማስጠላትና በማርከስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠል ስለሆነ ሁሉንም በጅምላ እንዳታይ ሐሳብ ላካፍልህ እወዳለሁ። ደብዳቤህ ግን ሁሉንም ኮርኩሮታል። ስህተታችን

አይጠቆመን ለማለት አልደፍርም። እውነት አለህ። ግን እጅግ ያመረረ ደብዳቤ ነው የፃፍከው ውድ ወንድሜ። ይህንን ሁኔታ ለመቀየር ሁላችንም የሀገር ኃላፊነት ስላለብን እንደዚህ ዓይነቱን አእምሮ የሻገተና ግዴለሽ ግለሰብ(Nihilist) የምንታገለው በማስተማር ነው። ሁኔታውንም ለመለወጥ ይቻላል። አዛለች ካሣዬ /አትላንታ—ጆርጂያ

## ታላቅ የምስራች በሳን ሆዜ

ውድ አንባብያን ይህንን አርዕስት መርጬ ስፅፍ የሚሰማኝ ደስታ በጣም የላቀ ነው። በተለይ ደግሞ በስደት ላይ ላለችው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን የተለየ ደስታ እንደሚሰጥ አምኜ ነው ብዕሬን ያነሳሁት። ወገኖቼ ዳዊት በመዝሙሩ በምዕራፍ (132–133፥1) ጀምሮ እንዲህ ይላል፦ “ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው» ይላል። በእውነት በአንድ ሀገር፣ በአንዲት እምነት ባላቸው ልጆች ላይ ለሰባት ወር ያለመግባባት በሳን ሆዜ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተፈጥሮ ነበር። በዚህም የተነሳ ግማሽ ወገን ወደአንዱ ግማሹ ወገን ደግሞ ወደአንዱ ተለያይቶና ለሰባት ወር ያህል ተከፋፍሎ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። “ግዜ ገቢር ለእግዚአብሔር” እንዳለው መፅሀፉ በእውነት እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራበት ቀን ደርሶ በሁለቱም ምዕመናን መካከል የነበረው ችግር በአንድ ሌሊት ውይይት በሃይማኖት አባቶችና በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በተደረገ ትልቅ ጥረት የነበሩትን ቅሬታዎች ሁሉ ወደ ጐን ጥሎ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብለን በአንድ ላይ ሆነን እግዚአብሔርን ማመስገን ከጀመርን ይኸው አንድ ወር አሳልፈናል። በእውነት ይህንን ለምታነቡ ሁሉ እኛስ ምን እያደረግን ነው? ብላችሁ ራሳችሁን እንድትጠይቁ በእግዚአብሔር ስም አደራ እላለሁ። የእኛን ችግር የፈታነው ራሳችን ስንሆን፤ አሁንም ደግሞ በተለያየ ስቴት ያለውን ያለመግባባት ራሳችሁ ተሰብስባችሁ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብላችሁ በአንድነት ሆናችሁ እግዚአብሔርን ለማመስገን ያብቃችሁ እያልኩ የምሰናበታችሁ ሚኪያስ አለሙ ነኝ – (ከሳን ሆዜ)

## እናንተስ አላጋጠማችሁም?
### (ስንቱን አየሁ በሴትነቴ)

እኔ ያጋጠሙኝን በየጊዜው አንዳንድ ጀባ ከማለት ወደ ኋላ አልልም። ለጊዜው የኢትዮጵያው ገጠመኝን ልተወውና አሜሪካን ከመጣሁ ያጋጠመኝን ላውጋችሁ። የእናንተንም ገጠመኝ ጀባ በሉን። እንወያይበት አምዱን እናስፋው። ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ስመጣ አንዲት አብሮ አደግ ጓደኛዬ ለቦይ ፍሬንዷ(ለወንድ ጓደኛዋ) የፍቅር ደብዳቤና ካሴት ስጪልኝ ብላ ትልከኛለች። እኔም ይገፍ መምጣት። እኔና እሱ የምንኖረው የተለያየ ስቴት ቢሆንም በሰጠችኝ አድራሻ መሠረት በፖስታ ቤት በኩል የተላኩለትን እቃ መላክ። እንግዲህ ድራማው አሁን ይጀምራል። አጅሬውም እቃው እንደደረሰው ወዲያውኑ ፖስታው ላይ ባለው በእኔ አድራሻ መሰረት ደብዳቤ ይፅፍልኛል። በደብዳቤውም እቃው ስለደረሰው ምስጋና እንዲሁም ሊደውልልኝ ብሎ ስልኬ ስለሌለው ለመደወል አለመቻሉ ወዘተ የመሳሰሉትንና በመጨረሻም ፍቃደኛ ከሆንኩኝ ስልኬን እንድፅፍለት ወይንም የምችል ከሆነ የእሱን ስልክ ቁጥር ፅፎ እንድደውልለት ይላል። እኔም በቅን ልቦና ስልኬንና የጓደኛውን ፎቶ ለሸኝት ከእኔ ጋር አብረን የተነሳነውን አንድ ላይ አድርጌ ላኩለት። አጅሬም ስልኬን በማግኘቱ አዘውትሮ መደወል ጀመረ። ስለሴት ጓደኛው አንስቼ ባወራሁት ቁጥር ጨዋታ ቀይሪ ይለኛል። ስለ እስዋ መስማትም ማውራትም አይፈልግም። እኔም በጣም ገረመኝ። እንዲያውም አንድ ቀን ምን አለኝ መሰላችሁ “ስለ እሷ ተይውና እኔና አንቺ ለምን ጓደኛ አንሆንም። ከፈለግሽ ትኬት ልላክልሽና ለአንድ 15 ቀን እኔ ጋ ነይ። ባይገርምሽ እኔ ኢትዮጵያም እያለሁ እሷን ሳይሆን አንቺን ነበር የምመኘው፣ ከአንቺ ነው ፍቅር የያዘኝ” ወዘተ የመሳሰለውን መለፍለፍ በመጀመሩ በነገሩ በጣም አዘንኩኝ። ኢትዮጵያ እያለ አበድኩልሽ ይላት የነበረችውን ጓደኛዬን ዛሬ ሲክዳት መስማቱ አልዋጥልሽ አለኝ። እኔም በትህትና የእኔ ወንድም ኢትዮጵያ እያለህ ምን ያህል ትሰግድላት እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። አንተ ዕድሉን አግኝተህ አሜሪካ መምጣትህን አትይ። እኔም ዕድሉን አግኝቼ እዚህ ብመጣም የሴት ጓደኛዬንና አብሮ አደጌን ለወንድ አልለውጣትም። ምንም እንኳ እዚህ አንዳንድ የማይረቡ ሴቶች የዘመዶቻቸውን ቦይፍሬንድ በጐን እንደሚያወጡ ባውቅም እኔ ግን የጓደኛዬን ቦይፍሬንድ ላወጣው ቀርቶ አላስበውም። እንግዲያውስ የጓደኝነት ትርጉሙ ምኑ ላይ ነው? በጣም አዝናለሁ ሁለተኛ እንደዚህ ዓይነት አስቀያሚ አስተሳሰብ ይዘህ እንዳትደውልልኝ” ብዬ ስልኩን ዘጋሁኝ። ባይገርማችሁ ጓደኛዬ ከአሁን አሁን ይወስደኛል ብላ በተስፋ እንደምትጠብቀው ትፅፍልኛለች። በቅርቡ ዲሲ ለእግር ኳሱ ጨዋታ ሄጄ ልጆች የነገሩኝ ደግሞ የባሰ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኑብኝ። አጅሬው አንዲት ጥቁር አሜሪካዊት አግብቶ እንደሚኖር ነገሩኝ። እንግዲህ ለጓደኛዬ ምን ብዬ ልፃፍላት? አይ የሰው ነገር! በሉ ቸር ይግጠመን –
የሺመቤት ነኝ ከሳንዲያጐ

# እንዲህ ሆነ

## ከዜና ማኅደር

### በተጠለፈው የኢትዮጵያ አውሮፕላን አደጋ 125 ሰዎች ሞቱ 50 ቆሰሉ

በሕዳር 14 ቀን በኮሞሮስ ደሴት አቅራቢያ ሕንድ ውቅያኖስ ውስጥ ለሦስት ተገምሶ በተከሰከሰው ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሆነው በይንግ 767 አውሮፕላን አደጋ የሞቱት መንገደኞች ቁጥር 125 ሲደርስ፣ ቆስለው በሕይወት የተረፉት ደግሞ 50 ናቸው።

ጥልቅ በሆነው ውቅያኖስና በአውሮፕላኑ ስብርባሪ ውስጥ በአደጋ ተከላካይ ሠራተኞች የሞቱትና በሕይወት የተረፉትን ለቃቅሞ የማውጣቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን በዚህ ሥራ ላይ የተሰለፈ አንድ የኮሞሮስ ዋናተኛ በመስጠሙ ሕይወቱ ማለፉም ታውቋል።

በሕይወት ከተረፉት 50 መንገደኞች ውስጥ 16 ሰዎች በኬንያና በሪዮኒዮን ደሴት ሕክምና ከተደረገላቸው በኋላ ከሆስፒታል ወጥተዋል።

የበረራ ቁጥሩ 961 የነበረው አውሮፕላን ከአዲስ አበባ ተነስቶ 163 መንገደኞችንና 12 የአውሮፕላኑን ሠራተኞች በድምሩ 175 ተሳፋሪዎችን ጭኖ በናይሮቢና በሌጎስ አድርጐ አቢጃን ለማምራት ጉዞ በጀመረ ከ25 ደቂቃ በረራ በኋላ ማንነታቸው ባልታወቁ ጠላፊዎች ይጠለፋል። ጠላፊዎቹ አውሮፕላኑ ለአንድ ሰዓት ተኩል ብቻ የሚበቃ ነዳጅ እንዳለው በፓይለቱ እየተነገራቸው የ6 ሰዓት በረራ የሚፈጀውን መንገድ ወደ አውስትራሊያ አቅጣጫውን እንዲያዞር ያስገድዱታል። ጠላፊዎቹ አውሮፕላኑ ናይሮቢ እንዲያርፍ አልፈለጉም። በዚህ ወቅት በተፈጠረው ውዝግብ ጠላፊዎቹ የአውሮፕላኑን ረዳትና ሌሎችንም የአውሮፕላኑን ሠራተኞች በመደብደብ አውሮፕላኑ ግንኙነቱን ከአዲስ አበባ ጋር እንዲያቋርጥ ያደርጋሉ። አውሮፕላኑ ወደ ኮሞሮስ ደሴት መቃረቡን የተረዱት ጠላፊዎች ፓይለቱ አቅጣጫውን እንዲቀይር ያስገድዱታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አውሮፕላኑ ለሦስት ተከፍሎ መከስከሱን የዜና አውታሮች ዘግበዋል።

ጠላፊዎቹ አማርኛ፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ በመናገራቸው ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት ቢኖርም ትክክለኛ ማረጋገጫ ግን እስካሁን አልተገኘም። የጠላፊዎቹ ቁጥር መጀመሪያ 11 በመጨረሻም 3 እንደሆኑ ተነግሮአል።

ከጠላፊዎቹ አንዱ አውሮፕላኑ መጠለፉን ባደረገው ንግግር "እኛ ከእስር ቤት አምልጠን የወጣን የመንግሥት ተቃዋሚዎች ነን" ሲል ·ማድመጡን በሕይወት ተርፎ ናይሮቢ ውስጥ በሕክምና ላይ የሚገኝ አንድ ኢትዮጵያዊ መንገደኛ ለቪኦኤ በሰጠው ቃለመጠይቅ የገለጸ ሲሆን፤ ንግግር ያደረገው ግለሰብ መልኩ ሱማሌ እንደሚመስልና የተቀሩት ሁለቱ ጠላፊዎች ግን ማስክ አድርገው ስለነበር ማንነታቸውን መለየት አልቻልኩም ብሏል። የኢትዮጵያ መንግሥት የአደጋውን ሁኔታ የሚያጣራ ቡድን ወደሥፍራው የላከ ሲሆን ይኸው ቡድን የኮሞሮስ መንግሥት በመንገደኞች ጠቋሚነት የያዛቸውን 2 ግለሰቦች ኢትዮጵያውያን እንዳልሆኑና ከጠለፋው ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸው የጅቡቲና የኬንያ ዜጐች ናቸው ቢልም የኮሞሮስ መንግሥት ግን የኢትዮጵያን መግለጫ አልቀበልም በማለት የተያዙትን ሁለቱን ሰዎች ጉዳያቸው እስኪጣራ ድረስ እንደማይለቅ ገልጾአል።

ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ በአደጋው ዜጎቻቸው ለሞቱባቸው ወደ 26 ለሚሆኑ ሀገሮች የሐዘን መግለጫ ልከዋል። በዚህ አደጋ 27 ኢትዮጵያውያን የሞቱ መሆኑ ታውቋል። በኢትዮጵያ ከኅዳር 16–18 ቀን ለሦስት ቀናት የቆየ ብሔራዊ የሐዘን ቀን ሆኖ የኢትዮጵያ ባንዲራ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ የተደረገ ሲሆን በየአብያተ ክርስቲያናቱና በየመስጊዱ ሕይወታቸው ላለፈው ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ዜጐች ፀሎተ ፍትሐትና ዱአ ተደርጐአል። በኢትዮጵያ የአየር መንገድ 51 ዓመት ታሪክ ውስጥ በጠላፊዎች የተነሳ ይህን የመሰለ እልቂት ሲደርስ ይህ የመጀመሪያው ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና እንደሚያመለክተው ጥቅምት 20 ቀን ከደብረዘይት አየር ኃይል ለበረራ ልምምድ የተነሳ አንድ የጦር አውሮፕላን በሞጆ መሐል ከተማ ላይ ወድቆ በመከስከሱ 8 ሰዎች ሲሞቱ 94 ሰዎች መቁሰላቸው የታወቀ ሲሆን አውሮፕላኑም በእሳቱ ቃጠሎ ሲጋይ አሠልጣኙና አብራሪው ግን በጃንጥላ ወርደው ከአደጋው ማምለጣቸው ታውቋል። የቀድሞ አየር ኃይል ከተበተነ በኋላ በ6 ወር ኮርስ ለብለብ ከተመረቁት 7 ምሩቃን ውስጥ 5ቱ በተለያዩ ጊዜያት ለበረራ ልምምድ እንደተነሱ ወድቀው በመከስከስ ሕይወታቸው ማለፉ አይዘነጋም።

### የአቶ ታምራት ላይኔ ከሥልጣን መባረር

«በምግባረ ብልሹነት» ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ ከመከላከያ ሚኒስትርነት እንዲሁም ከብአዴን ዋና ፀሐፊነታቸውና ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ከጥቅምት 14 ቀን 1989 ዓ.ም. የተወገዱት አቶ ታምራት ላይኔ በቀድሞው አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ በእስር ላይ ናቸው። ከአቶ ታምራት ላይኔ ጉዳይ ጋር በተያያዘ 162 ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትና ነጋዴዎች ታስረዋል።

አቶ መለስ ጥቅምት 14 ቀን የተወካዮች ምክር ቤትን ለአስቸኳይ ስብሰባ አስጠርተው·ታምራትላይኔን ከሥልጣን እንዲወገዱ ባስደረጉበት ጊዜም አቶ ታምራት ከእስር ቤት በቀጥታ ወደ ፓርላማው አዳራሽ እንደተወሰዱና "ምግባረ ብልሹነታቸውን" በራሳቸው አንደበት ተናግረዋል። በአቶ ታምራት ላይኔ ቦታም አቶ ተፈራ ዋልዋ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነቱንና የመከላከያ ሚኒስትርነቱን ሥልጣን እንዲጨብጡ አቶ መለስ ለምክር ቤታቸው አቅርበው ፀድቆላቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና እንደሚያመለክተው አቶ ተፈራ በሁኔታው ተደናግጠው በተቀሰቀሰባቸው ሕመም ሳቢያ ለሕክምና ከኢትዮጵያ ውጪ ሄደዋል።

ከአቶ ታምራት ጋር በተያያዘ ነው በማለት፣ በመንግሥት የኃላፊነት ቦታ የነበሩና አንዳንድ ሀብታም ነጋዴዎች ታስረዋል። ከእነዚህም ውስጥ የታምራት ላይኔ እህትና ባል፣ በአቶ ታምራት የስልጣን ዘመን

ባለሚሊዮን ብር ሆነዋል የተባሉት ወይዘሮ ሽዲያ ናዲምና ልጃቸው አቶ ዋሲም አብደላ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ የሆኑት የዶክተር ዱሪ መሐመድ ልጅ አቶ ሙኒር ዱሪ፣ የትምህርት ሚኒስትሯ የወይዘሮ ገነት ዘውዴ ባል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የአስተዳደርና የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ የነበሩት ዶክተር ከበደ ታደሰ በቁጥጥር ስር ሲውሉ፤ ሌሎች ብዙ ነጋዴዎች በመከላከያ ዕቃዎች ግገር፣ በቡና፣ በስኳርና በመሳሰሉት የጨረታ ውድድሮች ተሳትፈው እንዲያሸንፉ የተደረጉ በሙሉ ወደ ከርቸሌ ለመውረድ እየተፈለጉ መሆናቸው ታውቋል። እንዲሁም ከአቶ ታምራት ላይኔ ጋር ቅርበት አላቸው የተባሉትና የመከላከያ ሚኒስትር የመረጃና ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ መሆናቸው የተነገረላቸው ብርጋዴር ጄኔራል ምናሴ ወልደጊዮርጊስ የተባሉ የጦር መኮንን ለሥራ ግዳጅ ወደ ጅማ ታዘው በሄዱበት በዛው ሳይመለሱ መቅረታቸውን ዘገባዎች ይጠቁማሉ።

ከአቶ ታምራት ላይኔ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይሁን ሌላ የኢህአዲግ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የሆኑት የአቶ ዳዊት ዮሐንስ ባለቤት ወ/ሮ ኃይማኖት በምዝበራ ምክንያት ከሥራ ተባረዋል። ወ/ሮ ኃይማኖት የሕገ መንግሥት ጉባኤ የተካሄደበትና በቅርቡ ወደ ስብሰባ ማዕከልነት የተለወጠው ድርጅት አስተዳዳሪ ነበሩ. ተብሏል።

ሁኔታዎች ይህን ዓይነት መልክ ቢኖራቸውም የፖለቲካ ታዛቢዎች ኢህአዲግ የታጋይ ታምራት ከስልጣን መወገድ ከኢኰኖሚ ምዝበራ ጋር የተያያዘ እንዲሆንለት ቢፈልግም ታዛቢዎች ግን ከዚህ ባሻገር በህወሀትና በአቶ ታምራት ድርጅት በብአዴን መካከል የተከሰተ የፖለቲካ ስንጥቅ መኖሩን ያስምሩበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የአቶ ታምራት ላይኔ ከሥልጣን መባረርን አስመልክቶ የኢትዮጵያ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት አቶ ታምራትም ሆኑ መሰል ግለሰቦች፣ በሕዝብ መብትና ሐብት እንዲሁም በሀገር ሕልውና ሲያዙ የነበሩ በመሆናቸው ጥፋታቸው ሁሉ ሕዝብንና ሀገርን የጐዳ ስለሚሆን ጉዳዩ ለተጐጂው ሕዝብ በይፋ ሊታወቅና በሕግ ፊትም ቀርበው ሊጠየቁ እንደሚገባ አሳስቧል። በመጨረሻም፣ "ሰብዓዊ መብትን የሚረግጡ፣ በርካታ ዜጐችን ያለ ፍርድ የሚገድሉ፣ የሚያስሩ፣ የሚያሰቃዩ፣ የመንግሥት ካዝና በማራገፍና በጉቦ የከበሩ፣ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት ሐብት ያላቸው ኩባንያዎች ባለቤትና መሪ በመሆን ነጋዴውን ኅብረተሰብ አላሰራም ያሉ የፖለቲካ ባለሥልጣናት ብዙ መሆናቸውን" ምክር ቤቱ አመልክቶ፣ "የእነዚህ ከሕግ በላይ የሆኑና የሀብት ምንጫቸው የማይታወቅ በየአካባቢው የተፈጠሩ ባለሥልጣናት ሕዝብ ፊት ሳይጋለጡና በሕግ ሳይጠየቁ፣ አንድን ግለሰብ እንደ መስዋዕት እያቀረቡ ለማደፋፈን የሚደረግ የእርስ በእርስ መበላላት፣ ከስልጣን ሽኩቻ የዘለለ እንደማይሆን" አስገንዝቧል።

## የዋረን ክርስቶፈር ጉብኝት በኢትዮጵያ

የአሜሪካው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ዋረን ክርስቶፈር በቅርቡ በኢትዮጵያና በሌሎች 5 የአፍሪካ ሀገሮች ተመሳሳይ ጉብኝት ማድረጋቸው ይታወቃል። ሚኒስትሩ በግልፅካነጋገሯቸው አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ኢትዮጵያውያን በከፋ የአምባገነንነት ጭቆና ሥር እየወደቁ መሆናቸውንና በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚ ፖሊሲው፣ ከደርግ ጉዳኛ ኢሕአዴግ ንቅንቅ እንዳላለ አስገንዝበዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን ደርግ ከፓርቲው ሥር ያልሆኑ የሲቪክስም ሆነ የሙያ ማህበራት እንዳይቋቋሙ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ እንደነበረው ለዋረን ክርስቶፈር አስታውሰው፣ በአሁኑ ሰዓት የተፈቀደ ቢመስልም፣ ነፃ በሆነ መልክ ለመንቀሳቀስ የማይቻል ለመሆኑ፣ የኢመማ፣ የኢሠማኮና የኢሰመጉ የባንክ ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ መደረጉ፣ የዶክተር ታዬ መታሠር፣ አቶ ዳዊ ኢብራሂም ወደ ውጭ እንዳይንቀሳቀሱ መታገድና የጽሕፈት ቤታቸው መታሸግ፣ ኢሰመጉ ከሁለት ዓመት በላይ ለምዝገባ ያቀረበው ጥያቄ መልስ አለማግኘትና ሌሎች ተዛማጅ ተጽዕኖዎችን ለአብነት ያህል አቅርበዋል። በፖለቲካ ድርጅቶች በኩል፣ የኢድህና የሞዓ አንበሣ አባላት መንቀሳቀስ አለመቻላቸው፣ በኦሮሞ አካባቢ ኢሕአዴግን ያልደገፈ ሁሉ የኦነግ ደጋፊ ነህ በመባል መታሠር፣ መታፈንና መገደል የተለመደ መሆኑንና የመኢሕድ መሪዎችና አባላቱ በእስር ቤት እንዲንገላቱ መደረጋቸውን ፕሮፌሰሩ አስረድተው፣ ባለፉት አምስት ዓመታት በዜጎች ላይ ግፍ የፈፀሙ ባለሥልጣናት ሕግ ፊት ቀርበው አለመጠየቃቸው ሁኔታው እንዲባባስ ያደረገ መሆኑን አጽንዖት በመስጠት አብራርተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ለዋረን ክርስቶፈር አቅዋማቸውን እንዲያስረዱ ዕድል የተሰጣቸው፣ "ታማኝ ተቃዋሚ" በመባል የሚታወቁት የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አባል የሆኑት አቶ ክፍሌ ወዳጆና አቶ ነብዩ ሳሙኤል ሲሆኑ፣ በተለይ አቶ ነብዩ ስለኢሕአዲግ ዲሞክራሲያዊነት በአገሪቱ ሠላም ስለመስፈኑ ያሰሙት ንግግር፣ አሜሪካኖቹን ጭምር ያስገረመና ትዝብት ላይ የጣለቻው እንደሆነ ታውቋል።

አቋማቸውን ለመግለጽ ዕድል ያገኙት ሌላው ተናጋሪ የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር በየነ ጴጥሮስ በበኩላቸው፣ በሕገ መንግሥት ስም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫነው የኢሕአዴግ የፓርቲ ፕሮግራም መሆኑንና ተግባራዊ ለማድረግም ሆነ ለማሻሻል እንዳይቻል ተደርጐ የተቀረፀ፣ ለኢትዮጵያም አደገኛ ሰነድ መሆኑን መሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች መረገጣቸውን፣ የሕግ የበላይነት እንደማይከበር፣ አስተዳደሩም በኢሕአዴግ ጠባብ የጐሣ ዓላማ ላይ የተመሰረተና ጥቂቶችን ለመጥቀም ብቻ የተዘጋጀ መሆኑን አስገንዝበው ምዕራባውያንና ሌሎችም አገሮች "ኢሕአዴግ ከደርግ ይሻላል" በሚል አዘናጊ መመዘኛ አገሪቱ ወደ ከፋ ሁኔታ እንድትወድቅ የሚደረገውን ሩጫ ከመመርመር ወደ ኋላ ማለት እንደሌለባቸው ዶክተር በየነ ለዋረን ክርስቶፈር አሳስበዋል።

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከታዋቂ ግለሰቦች አምባሳደር ዮዲት እምሩን፣ አቶ ጠሐ ሁሴንና አቶ ተሾመ ገብረማርያምን ማነጋገራቸው ታውቋል። ዋረን ክርስቶፈር ዘጠኝ ግለሰቦችን ለማነጋገር ተመድቦላቸው የነበረው ጊዜ ሰላሳ ደቂቃ ብቻ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

ክርስቶፈር ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ የሁለቱ አገሮች ባለሥልጣናት ብቻ በጋራ ጋዜጣዊ

መግለጫ እንዲሰጡ በኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት የወጣውን ፕሮግራም በመቃወም ለብቻቸው በሒልተን ሆቴል የግል፣ የውጭና የመንግሥት ጋዜጠኞችን በማስጠራት መግለጫ በሰጡበት ወቅት በኢትዮጵያ የተሻለ ለውጥ ቢታይም በሰብአዊ መብትና በተለይ በፕሬስ ነፃነት በኩል ብዙ ለውጥ ያስፈልጋል ብለዋል። የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከአዲስ አበባ ቆይታቸው ሲመለሱ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ሲሆን "ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር በተነጋገርንበት ወቅት ስለሰብአዊ መብት መከበር በተለይም ለነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ድጋፍ እንደሚያስፈልግ፤ የጋዜጠኞች መብት እንዲሁም ደህንነት መጠበቅ እንዳለበት አጥብቄ አስረድቻቸዋለሁ።" በማለት ማረጋገጫ ሰጥተዋል።

## ኢትዮጵያ የአፍሪካ አገሮች በቡትሮስ ጋሪ ምትክ ሌላ ፀሐፊ እንዲመርጡ ጠየቀች

የአፍሪካ አገሮች በቡትሮስ ቡትሮስ ጋሪ ምትክ ለተ.መ.ድ. ዋና ፀሐፊነት ሌላ እጩ እንዲመርጡ የኢህአዲግ መንግሥት ጠየቀ።

አሜሪካ ብቻ ድምፅን በድምፅ መሻር መብቷን በመጠቀም ለሚቀጥለው ምርጫ እንዳይወዳደሩ ባገደቻቸው ቡትሮስ ጋሊ ምትክ ሌላ እጩ እንዲቀርብ ድጋፍ በመስጠት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ መንግሥት የመጀመሪያው ሆኖአል። የአፍሪካ መሪዎች ለተባበሩት መንግሥት ድርጅት ፀሐፊነት ሌሎች ብቁ ፀሐፊዎች ማቅረብ የሚችሉበት መልካም አጋጣሚ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው ሲል የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ጥሪውን አቅርቧል። ይህ ከዓለም የተለየው አቋም በተለይ በአፍሪካ ሀገሮች ዘንድ የኢህአዲግ መንግሥት ሙሉ በሙሉ የአሜሪካ መንግሥት መሣሪያ አድርጐ አጋልጦታ ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይተቻሉ።

## የነጋዴው አቤቱታ ሰሚ አላገኘም

የክልል 14 (አዲስ አበባ) የነጋዴው ሕብረተሰብ ክፍል "ክልሉ በቤት ኪራይ ጭማሪ ላይ የወሰደው እርምጃ ሰብዓዊነት የጐደለው፣ በቂ ጥናት ያልተደረገበት፣ ደሐን ከአገር ለማባረር የተወሰደ የኢሕአዴግ ሴራ ነው" በማለት ለሁለተኛ ጊዜ ሰላማዊ ሠልፍ ወጥተው ለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አቶ ዳዊት ዮሐንስ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አቶ ዳዊት ዮሐንስ የነጋዴውን ክፍል ተወካዮች አቤቱታ በፅሕፈት ቤታቸው ውስጥ ሆነው ካዳመጡ በኋላ በሰጡት መልስ "ክልሉ የወሰደው እርምጃ የሚደገፍና እርምት የማያስፈልገው ትክክለኛ ውሳኔ ሆኖ መገኘቱን ምክር ቤቱ ስላመነበት ትክክለኛ ውሳኔ ነው ከማለት በስተቀር ሌላ መልስ አንሰጥም" የሚል መልስ ሰጥተው አሰናብተዋቸዋል።

እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ በቅርቡ ለመንግሥት ዜና ወኪሎችና ለፖርቲያቸው መገናኛ ብዙኃን ወኪሎች ብቻ በጠሩት ጋዜጣዊ ጉባዔ፣ ክልል 14 ያደረገውን የንግድ ቤቶች የኪራይ ጭማሪ መንግሥታቸው ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ የሚያውቀው መሆኑንና በቂ ጥናት የተደረገበት መሆኑና ድርጊቱም የሚደነቅ መሆኑን ተናግረዋል። አቶ መለስ በሰጡት መግለጫ በውሳኔው ነጋዴው ሊኖረው የሚችለው አማራጭ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከቦታ ቦታ የሚችለውን አማርጦ መነገድ፣ ካልቻለም ለቆ ወደ ሌላው የአገሪቱ ክፍሎች መሄድ ብቻ መሆኑን በማስታወቅ በዚሁ አጋጣሚም ኢሕአዴግ አንድን እርምጃ ያለ በቂ ጥናት እንደማይወስድና ከውሳኔ ላይ ከደረሰም ተግባራዊ ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይል እስካሁን የተጓዘባቸው መንገዶች እንደሚያረጋግጡ አቶ መለስ በድፍረት ተናግረዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ክልል 14 በንግድ ሱቆች ላይ ያደረገውን ጭማሪ በጽኑዕ ተቃውሞ፣ የተላለፈውን ውሳኔ ነጋዴው እንዳይቀበል የጠየቀ ሲሆን፤ የአገሪቱ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ማዕከል በሆነችው አዲስ አበባ የሚካሄደውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማዳከም የተወደሰው እርምጃ መላውን የአገሪቱን ዜጋ ኑሮ የሚያናጋና ማህበራዊ አለመረጋጋትን የሚፈጥር አደገኛ እርምጃ እንደሆነ መግለጫው አስገንዝቦ፣ ጭማሪው የንግዱን ኅብረተሰብ የመክፈል አቅም ያላገናዘበ፣ ገቢ በማግኘት ላይ ብቻ ያተኮረና ሕዝቡን በማስጨነቅ፣ በማስበርገግና በመቅጣት ለመግዛት ከመፈለግ የመነጨ የአምባገነኖች እርምጃ መሆኑን በመጥቀስ አብራርቷል።

ከዚሁ ጋር የደረሰው ዜና እንደሚያስረዳው የአዲስ አበባ ነጋዴዎች የተደረገባቸውን የኪራይ ጭማሪ ሕገ ወጥነት በፍርድ ቤት አቅርበው ለመከራከር እንደወሰኑ ታውቋል።

## ኢሠመጉ በሰብአዊ መብት ረገጣ 24 ሰዎች መገደላቸውን አጋለጠ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ሰሞኑን ባወጣው 10ኛው የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ዘገባ በ1988 የደረሱትን የ2927 ሰዎችን አቤቱታዎች መቀበሉን አስታወቀ።

ባለፈው 1988 ዓ.ም. በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ቢያንስ ሃያ አራት ሰዎች ያለ ፍርድ መገደላቸውን ኢሠመጉ በዚሁ መግለጫው አስታውቆ ገዳዮቹ የመንግሥት የፀጥታ ኃይል ሠራተኞች በየትኛውም ደረጃ ለፍርድ ያለመቅረባቸውን አስረድቷል። ያለ ፍርድ የተገደሉ በሚለው ዘገባ ስር ከከፋች ዞን 3 ሰዎች፣ ከአዲስ አበባና ከሐረር 6 ሰዎች፣ ከቦረና 8 ሰዎች፣ ከምዕራብ ሸዋ 1 ሰው፣ በደሴ ካራጉቱ በተባለ ቀበሌ ገበሬ ማህበር 5 ሰዎች ያለአግባብ የተገደሉ መሆናቸውን በማስረጃነት ጠቅሶ፤ ከግድያው በተጨማሪ በጠቅላላው 18 ሰዎች በድብደባ ብዛት ምክንያት አካለ ጉዶሉ መሆናቸውን፣ 5 ሰዎችም ያለ አግባብ ንብረታቸው እንደተወሰደባቸው የኢሠመጉ መግለጫ አብራርቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሆላንድ የልማት ትብብር ማኅበር የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤን ለመርዳት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ገቢ አድርጐት የነበረውን ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ብር ባንኩ ለኢሰመጉ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይኸንኑ ገንዘብ የማይሰጠው ከሆነ ወደ ሆላንድ ተመላሽ እንዲሆን መጠየቁም ታውቋል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኢሰመጉ ከግንቦት ወር 1987 ጀምሮ በባንክ ያስቀመጠውን ከ676 ሺህ ብር በላይ እንዳያንቀሳቅስ ማገዱ የሚታወስ ነው።

## የኤርትራና የኢትዮጵያ የውህደት ጥያቄ እያነጋገረ ነው

በኢትዮጵያ የኤርትራ አምባሳደር አቶ ኃይሌ መንቆርዮስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እየታተመ ለሚወጣ ለአንድ የአገር ውስጥ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃዷ የማይቀር ክስተት መሆኑን አስታውቁ። እንደ አምባሳደሩ አስተያየት የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሥታትና የሁለቱ ሕዝቦች መረዳዳትና ግኑኝነት ለውህደቱ መንገድ ከፋች ሊሆን ይችላል።

የረጅሙ የኤርትራ ትግል ዓላማ ነፃ አገር መመሥረት እንዳልነበረ አምባሳደር ኃይሌ ገልፀው ከኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ከሌሎች ጎረቤቶቻቸው ተለይተው የመኖር ፍላጐት እንዳልነበራቸውም አስረድተዋል። ኤርትራ የውህደቱን ፍላጐት ማንፀባረቅ የጀመረችው በቅርቡ ያለመሆኑንም አቶ ኃይሌ አውስተው፣ የውህደቱ ምክንያትም የኢኮኖሚ ችግሮች አለመሆኑንም ለማስረዳት ሞክረዋል። ኤርትራ ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ አመራሩ፣ ከአካባቢው አገሮች ጋር የመዋሃድን አስፈላጊነት ሲያስብ እንደነበረ አቶ ኃይሌ ገልፀው፣ ሆኖም የጋራ ታሪክና ባህል ከነበሩትና ለተወሰነ ጊዜም በጋራ የፖለቲካ ሥርዓት ስር ከነበሩት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ ቀላል እንደሚሆን አስገንዝበዋል።

ቀደም ባለው ጊዜ፣ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መለያየትና ነፃነትዋን መቀዳጀት መብቷና ሰላሳ ዓመት የታገለችለት ዓላማ መሆኑን ሲገልጡ ቆይተው፣ ትንሽም ሳይቆዩ፣ በቅድም ተከተል የኮንፌዴሬሬሽን ግኑኝነት፣ ቀጥሎም የፌዴሬሽንና በመጨረሻም የውህደት ቀመር ማቅረባቸው አይዘነጋም። አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ስለ ኤርትራና ኢትዮጵያ ውህደት ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከደርግ ውድቀት በኋላ ባለፉት አምስት ዓመታት፣ በኢኮኖሚውም፣ በፖለቲካውም፣ በማህበራዊውም ዘርፍ ተጠቂ ሆነን ስለቆየን፣ የውህደቱ ጥያቄ በዚህ ወቅት መነሣቱ ቂምንና ቁርሾን ሊቀሰቅስ ይችላል ብለው ጉዳዩን ዛሬ ማንሳቱ ወቅቱ እንዳይደለ አስገንዝበዋል። አንዳንዶቹም የውህደቱ ጥያቄ ገፍቶ ከመጣ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተያየቱን በሪፈረንደም መጠየቅ እንዳለበት አስምረውበታል።

## ዶክተር ታዬና ፕሮፌሰር አሥራት ፍርድ ቤት ቀረቡ

በወህኒ ቤት የሚገኙት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ዶክተር ታዬ ወልደሰማያትና ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ጥቅምት 4 ቀን 1989 ዓ.ም. ፍርድ ቤት ቀርበው ነበር። የኢመማው ፕሬዚዳንት ከሌሎች 6 ሰዎች ጋር የጦር መሣሪያ በመያዝ ሕገወጥ እንቅስቃሴ አድርጋችኋል በማለት መከሰሳቸው የሚታወስ ነው። ዶክተር ታዬ እስር ቤት ሲመጡ እጆቻቸው በካቴና ታስረው ሲሆን ለችሎቱ ባሰሙት አቤቱታ ወህኒ ቤት ውስጥ እንዳሉ የተለያዩ ሰዎች እየመጡ ቃላቸውን እንዲሰጡ እንደሚያስገድዷቸውና ይህም አድራጐት እንዲገታላቸው የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጥያቄያቸውን አግባብ ባለው አካል እንደሚያስተላልፍላቸው ገልጾላቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የ5 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸው ላለፉት ሁለት ዓመታት በእስር ላይ የሚገኙት የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በሌላ ክስ በዚሁ ዕለት ፍርድ ቤት ቀርበው ነበር። ፕሮፌሰር አሥራት ከዚህ ጋር ለ150ኛ ጊዜ ችሎት ፊት መቅረባቸው ታውቋል። ጥቅምት 4 ቀን የዋለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት እንደገና ለሌላ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ወስኖ ተነስቶአል።

## ፖሊስ በዶክተር አብዱል መጂድና በሆቴሎች ላይ አደጋ አድርሰዋል ያላቸውን ወንጀለኞች መያዙን አስታወቀ።

በመገናኛና ትራንስፖርት ሚኒስትሩ በዶክተር አብዱል መጂድ ሁሴን ላይ የግድያ ሙከራ ያካሄዱ፣ የመንግሥት ንብረት በሆኑት፣ አዲስ አበባ በሚገኘው በግዮን ሆቴልና ዋቢ ሸበሌ ሆቴል፣ ድሬዳዋ ባለው ራስ ሆቴል ፈንጂ አጥምደው በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል ያላቸውን 11 አሸባሪዎች መያዙን ፖሊስ አስታወቀ።

እነዚህ በቁጥጥር ሥር የዋሉት 11 ሰዎች ሱማሊኛ ተናጋሪዎችና ሙስሊሞች ናቸው። ሽብርተኛ መሆናቸው የተገለጹትና የተያዙት ሰዎች፣ ለሌላ ዳግም ጥፋት ዝግጅት ላይ እንዳሉ ከያዙት መሣሪያዎች ጋር በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን መግለጫው አስረድቷል።

## የምክር ቤት አባል የሆኑ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ቤተመንግሥት ውስጥ ሞተው ተገኙ።

የኦሕዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዓባልና የኦሮሚያ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ፣ በብሔራዊ ቤተመንግሥት ቅጽር ግቢ ሞተው መገኘታቸው ታውቋል። አቶ ዓለማየሁ ደሣለኝ የተባሉት እኚህ የክልሉ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሞተው የተገኙት፣ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት ግምገማ ያደርጉበት ከነበረው አዳራሽ ለምሳ ከወጡ በኋላ ነው።

አቶ ዓለማየሁ ሞተው የተገኙት መኪናቸው ውስጥ ሲሆን የቀብራቸውን ሥነ ሥርዓት የገለጹት የኢትዮጵያ መገናኛ ዘዴዎች የአሟሟታቸውን ሁኔታ ሳያብራሩ በአደጋ መሞታቸውን ለሕዝብ አሳውቀዋል።

## የደብረ ዳሞ ገዳም ግምጃ ቤት ነደደ ተባለ

በትግራይ ክልል በአዲግራት አውራጃ የሚገኘው ታሪካዊው የደብረ ዳሞ ገዳም ግምጃ ቤት መንደዱ ተገለፀ። ይህ የተገለፀው፣ ጥቅምት 9 ቀን 1989 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ በቀረበ ሪፖርት ላይ ነው።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ እንደተመሠረተ የሚነገርለት የደብረ ዳሞ ገዳም፣ ነደደ የተባለው በክረምቱ ማብቂያ ላይ ተፈጥሮ ነበር በተባለ የመብረቅ አደጋ ነው። እያሌ ቅርሳ ቅርሶች የተከማቹበትና

(ወደ ገጽ 35 ይዞራል)

# ማሩ ግሮሰሪ Maru Grocery

## በቅድሚያ እንኳን ለገና በዓል በሰላም አደረሳችሁ እንላለን!

ባሁኑ ጊዜ ከዳላስና ከሂውስተን ከተማ ክልል ውጪና እንዲሁም በሌሎች ከተሞች የምትገኙ ወገኖቻችን እንዳንድ የሚያስፈልጋችሁን፣

**ቅመማ ቅመሞች፣ ጥራ ጥሬዎች፣ የጤፍ ዱቄት፣ እንዲሁም እንጀራ**

የዕቃ ዝርዝርና ዋጋ ለማወቅ ከፈለጉ በዳላስ አድራሻ ይጠይቁን። ባሁን ጊዜ በተጨማሪ፦

1ኛ አስቴር አወቀ በለንደን-ቪዲዮ፣ ሲዲና ካሴት፤
2ኛ AFRICA ARK ስለ ኢትዮጵያ ስእላዊ መግለጫ መፅሀፍ፤
3ኛ The Sign and the Seal--The quest for the lost ark of the covenent, መፅሀፍ፤
4ኛ Long Walk to Freedom--Nelson Mandela, መፅሀፍ፤
5ኛ ዋሸራ 2.0፣ የኢትዮጵያ ሶፍትዌር እናቀርባለን።

Maru Grocery
8353 Park Ln
Dallas, TX 75231
(214)373-6278

Maru Grocery
6065 Bissonnet
Houston, TX 77081
(713)665-6662 (713)665-6608

## EthiO Systems

PO Box 36921
Houston, TX 77236
(713)995-4360
ethiosys@neosoft.com
http://www.neosoft.com/~ethiosys/ethiosys.html

**$115**

ዋሸራ 2.0
for Windows 3.1x Windows 95

**Supported Software**

Word Processing: MS Word, WordPerfect, WordPro, AmiPro,...

Spreadsheets: Lotus 1-2-3, MS Excel, Quattro Pro,...

Database: MS Access, Lotus Approach,...

Publishing: PageMaker, QuarkXPress, Corel Ventura,...

Illustration: CorelDRAW, Adobe Photoshop, Photoworks, ...

Internet: Eudora, Internet Explorer, Netscape Navigator, Exchange,...

Windows 3.1x and Windows 95 resident programs

**በኢትዮጵያ ቋንቋና ፊደል**

መፅሔት፣ መፅሀፍና ልዩ ልዩ ሰነዶችን፤
ስፕሬድሽቶች፤
ዳታቤዝ፤
ንግግር ማቅረቢያ ዝግጅት፤
ኤሌክትሮኒክ መልክት፤
ዌብ ገፅ፤
ልዩ ልዩ ስዕላዊ ፊደላትና የመሳሰሉትን
ከታወቁ ሶፍትዌሮች ጋር ለማዘጋጀት
የሚያስችል ሲስተም።

ዋሸራ 2.0
በሚከተሉ መደብሮች ይገኛል

Maru Grocery
Houston, TX (713)665-6608
Dallas, TX (214)373-6278

Ethio Sound
Washington, DC (202)232-0076

Addisu Gebeya
Washington, DC (202)986-6013

Queen of Sheeba
Falls Church, VA (703)998-0180

# ደበበ በችሎት ላይ

(ከስም የለሽ–Anonymous)
ውርስና አፍታች ትርጉም
(ልሳኑ ስምረት)

በአፈርሳታ ቤት በችሎቱ፣
በሐዘን ታምቆ እንደበቱ።
ሳይሰማው መገፍተሩ፣
መንገላታት መታሠሩ።
ሁሉም እያየው በየግሉ፣
እየተመኘው በበኩሉ፤
ተጠየቀ ስለ"ጥፋቱ"፣
ፍንከች ሳይል ከእምነቱ፣
ሳያጋድል ከፅናቱ፣
ደቤ ጉልማሳው ወጣቱ፣
ሽማግሌው ባልቴቱ
ደቤ የደበበች የሴቱ፣
የብርኃን ምሰሶ ብርቱ።
ጨምዳዳ ፊቱን ቋጥሮ
የዘመናት ሽብሽብ ብሶቱን፣
የእሥር ቤት ዥርጋጋ ሪዙን።
በግማሽ ፈገግታ አብስሮ፣
እልሁን በሕግ ዘርዝሮ።

የድንጋይ ዘመን ዘመነኞች፣
ወንጭፍ አጓኝ የሞኝ ብልጦች።
በመስታወት ቤት ተቀምጠው፣
ጥቀርሻቸውን አንጥተህ –
መርዘኞችን የታገልከው፣
የክብር ኩታ የደረብከው፣
እንደጉርዶን ፓሻ ሳያድልህ –
ለምስለኔ ወርቅ ያልበቃኸው፣
ግን በልብህ ርካት ሽልማት –
የሕሊና ካባ የለበስከው።

ለጥላሼት ቀለማቸው፣
ለስም አጥፊ ስብቅና –
ያልተበገርክ ባለጉራው!!
ለብቸኞች የቆምክ ጥብቅና፣
ደብዩ የሀገር ናሙና፣
የትግል ከመዘና።

ጨምዳዳ ፊቱን ቋጥሮ፣
አገጩን እንደተራራ ደምሮ፣
የሕዝብን ብሶት ቀምሮ፤

ራሱን በራሱ አሸጋሽጉ፣
አቶም ለአቶም አፈጋፍጉ።
በባትሪ ሐቁን መርምሮ፣
እንደ ወፍጮ ራሱን ወቃቅሮ፣
ያውም በውሸት ተከሶ..ባላጠፋበት ተወግሮ፤
በርጋታ ሳያንቀላፋ፣
ሳያቀረቅር አንገት ሳይደፋ።
በጀግንነቱ አስመስክሮ፣
እንደወፍጮ ራሱን ወቃቅሮ።

ካመረረው የከሳሽ ሁከት፣
የእርሱ ፀጥታ የገነነበት፣
በዚያ የፍርደ–ገምድል ችሎት፣
እንባው ተናንቆት የዋጠበት ...
ደብዩ የተለካበት፤
ይባስ ብሎ
ተጣጥሎ
እግሩም ቢታሰር በካቴና...
ሕሊናው ሮጠ ተፈታና፣
ደብዩ የስቃይ አንፋሮ...
የድኃ ሀገር ጉተና፣
የሦስተኛ ዓለም ኮምፓኜሮ...
የብሶታቸው ሁሉ በገና፣
የነፒካሶ የነሚሮ...
የብርኃዊነታቸው ፈተና።
ተናገረም ሳያለቅስ፣
በማንም "እምነተ–ቢስ" ክስ፣
ለነራስ ኒኬል ጉርሻ ምስ።

እምነቱም የእውነት ነበር፣
ወንድምነት መከባበር፣
መተራረቅ መፈቃቀር፣
ለብዙኃን መተባበር።
ባለዐቢይ ነፍስ ደበበ...
ገብረሀቅ የእውነት ባሪያ
ወደ ኮከቦች የሚያሻቅብ...
ተስፋው ብርሃን መተያያ
ከጭቅቅት ፖለቲካ ባሻገር...
መስመሩ የጥራት መለኪያ።
በችሎቱም ተከሶ...
ተንጋጦበት ተስቆበት፣
ለምን ብለው ቢጠይቁም...
ባላንጣዎች ያልረኩበት፤
ግን ጦርነትን ተቃውሞ...
መራራቅን ተፋልሞ
ሰውን በመውደድ ነዶ
በጥላቻ ገሞራ ውስጥ
በዐመድ እሳት ረመጥ፣
እንዳይገቡ እርሱ ተማግዶ፣
ሁሉንም እርሱ ወስዶ።
ስለእነርሱ እርሱ ተገዶ።

ደብዩ ወንጀልም የለው
ፅድቀ–ልፋፋ ፍትሕ ነው
የለም
በፍጹም አልተገዛም!
ያልገባቸውም ይማራሉ
በሠፈሩት ይሰፈራሉ
በሕዝብ ዳኝነት ሕሊና ...
በሰውነት ስብዕና
የጉናቸውን ያገኛሉ
በደብዩ የእምነት ከሰሉ
በፍትሕ ሕዝብ ይዳኛሉ
የለም!
በፍፁም አልተገዛም
ያልገባቸውም ይማራሉ

በደብዬ የእምነት ክስሉ
በፍትሕ ሕዝብ ይዳኛሉ።

ፈሪ ነህ ሲሉት ሳይፈራ
ሳይኮላሽ ሳይገራ
በማንም ዋልጌ ገራራ
በቀጣፊ ነዳፊ ኮብራ
በሞላጫ የባሕል ቦራ
በስብቅና ቴረሪስት ገታራ፤

ባሕላችንን ለሚንቁ
በድኀነታችን ለሚሳለቁ
አፍራሽ ጦራቸውን ለሚሰብቁ፣
እንደቀያፋ ለሚናጡ
በክርስትና ተጠልለው –
የአምላክን ስም ለሚድጡ
ለሚሰድቡን ለሚያንጓጥጡ
ክሬዲትን ለሚያሳጡ
ገንቢ ሒስን በስም ማጥፋት
ለጥቅማቸው ለሚሸጡ
"ባገር ወዳድ" ስም ተጠልለው –
ድርጅትን ለሚመልጡ
እንደአሲድ ለሚልጡ።
አንተ ለእነርሱ የምትዋስ
እነርሱ ሳይበሉ የማትጉርስ

ደብዬ የስዋሰው ግስ
ጡፍህ ያልሆነ ግሳንግስ
ሥራህ የሚመሰክር ሕያው –
አንድነትን የሚለግስ።

ሲጨፈልቁህ የምትነሳ
የዋሕ ደብዬ ከነስህተትህ –
የኅብረተሰብ እንስሳ
በሕዝብህ ልብ የታቀፍክ –
አንጻርጌ ፍቱን ፈይሳ
የኅብረተሰብ እንስሳ!!

ማስታወሻ፦ አደራ ይህ ግጥም (ትርጉሙ) ለሕሊና–እሥረኞች (Prisoners of Conscience) መታሰቢያ ይሁንልኝ። ትርጉሙ አፍታችና ውርስ ነው። ታሪኩ የዴብስ ታሪክ ቢሆንም ለሕሊና–እሥረኞች ሁሉ ጥብቅና የቆመ ነው። ርዕሱ "ዴብስ በክስ ፍርድ ቤት" የሚል ነው። የተፃፈውም ክስም የለሽ (Anonymous) ፀሐፊ ነው። ዩጂን ዴብስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ለአሜሪካ ሠርቶ አደሮች የታገለ፤ በግፍም ለብዙ ዓመታት በእሥራት የማቀቀ የሕዝቦች መሪ ነው። ጽሑፉ ዴብስና ገጣሚዎች ከሚል መጽሐፍ በውርስና በአፍታችነት የተወሰደ ነው።

*[Ruth Le Prade, Debs And The Poets, Upton Sinclair Company, 1920 page 32]*


R T S

RAPID TAX SERVICE
ፈጣንና ቀልጣፋ
የታክስ
ሥራ አገልግሎት
PROFESSIONAL
TAX PREPARATION
INDIVIDUAL & BUSINESS
ELECTRONIC
TAX FILING

OFFICE HOURS
*Monday - Friday 8:00am to 7pm*
*Saturday 9am to 5 pm*
CALL (RTS) LEAKE MALEDE
PHONE: (404)296-3088
FAX: (404)296-7413
E-Mail: rapidtax@aol.com
*Accepted the past two years by the IRS to participate In the electronic filing Program*

ASAP  COPIES

BEST PRICE IN TOWN!
*High-Speed Duplicating*

Business Cards
Flyers
Typesetting
Resumes
Fax Services

ካብኛ!!

Photo ID
Passport Photos
Laminations
Greeting Cards

Letterheads
Envelopes
Rubber Stamps
Copy Service
Self-Serve Copies

Conveniently located in Campus plaza Shopping Next to Dekalb Book Store

# የዶ/ር ዮሐንስ መላኩ
# አጭር የሕይወት ታሪክ

ዶ/ር ዮሐንስ ከእናታቸው ከወ/ሮ አስካለ ኃይሌና ከአባታቸው ከአቶ መላኩ ተገኝ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር መስከረም 11 ቀን 1950 ዓ.ም. አዲስ አበባ ውስጥ ተወለዱ።

ዶ/ር ዮሐንስ የአንደኛና የመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በኢሊባቡር ዋና ከተማ በጐሬ አጠናቅቀው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው አዲስ አበባ በሚገኘው የሽመልስ ሐብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፈጽመዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአንድ ዓመት ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ወደ አሜሪካ መጥተው ትምህርታቸውን በመቀጠል ከ1974–1976 ዓ.ም. የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን (B.A.) ከኖትሪጅ ካሊፎርኒያ ዩንቨርስቲ፣ የማስትረስ ዲግሪያቸውን ከካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ አገኙ። ቀጥለውም በኢንዲያና ዩኒቨርስቲ ሌላ የማስተረስ ዲግሪ (M.S.) አግኝተዋል።

ዶ/ር ዮሐንስ መላኩ የገበዩትን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል ወደ እናት ሀገራቸው በመመለስ በንግድ ምክር ቤት ውስጥ የሕዝብ ግንኙነትና የህትመት መምሪያ ዲሬክተር በመሆን ከ1979–81 ዓ.ም. ድረስ አገልግለዋል።

ከዚያም ወደ አሜሪካን አገር በመመለስ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ማዕከል (ECC) ውስጥ ከ1982–83 የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል። ከዚያም አርሊንግተን በሚገኘው የጋራ የመረዳጃ ማህበር (MAA) ውስጥ በፕሮጀክት ዲሬክተርነት በመስራት ላይ እያሉ በጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል በ1988 ዓ.ም. በትምህርት የዶክተርነት ዲግሪ አግኝተዋል።

ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ እስከእለተ ሞታቸው ድረስ በዋሽንግተን ዲሲ የትምህርት ዘርፍ ውስጥ የፕሮግራም አስተባባሪ በመሆን ሠርተዋል።

ዶ/ር ዮሐንስ መላኩ ትንሽና ትልቅ ሳይሉ ሰውን አክባሪና ደጋፊ በመሆናቸው በትርፍ ጊዜያቸው ልዩ ልዩ ኮሚኒቲ ድርጅቶችን አገልግለዋል። ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩ ድረስ ነፃ አገልግሎት ለህብረተሰቡ አበርክተዋል። በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ ትናንሽ የኢኮኖሚ ድርጅቶች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ በግላቸው ጥናት በመካሄድ ላይ ነበሩ። ይህንኑ ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒቲ ዲቨሎፕመንት ካውንስል በዋሽንግተን አካባቢ በሚያካሂደው የትናንሽ የንግድ ድርጅቶች ማቋቋምና ማስፋፋት ፕሮግራም አማካሪ በመሆን ነፃ አገልግሎት ሲያበረክቱ ቆይተዋል።

ዶ/ር ዮሐንስ በጓደኞቻቸውና በሚያውቋቸው ሁሉ በፈገግታቸው፣ በሰው አክባሪነታቸውና በበጎ ምግባራቸው የተከበሩ፣ የተወደዱ ሰው ነበሩ።

ዶ/ር ዮሐንስ መላኩ በጣም የሚወዱት የ5 ዓመት ዕድሜ ያለው ልጃቸው ሚካኤልንና ቤተሰባቸውን ትተው November 6 ቀን 1996 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም November 13 ቀን 1996 ዓ.ም በአርሊንግተን ከተማ በኮሎምቢያ ጋርደን ሲምትሪ ተካሂዷል።

አዲስ አበባ ለሚገኙት አባቱና እህቱ፣ ቨርጂኒያ ለሚገኙት የቀድሞዋ ባለቤቱና ለልጁ (ሚካኤል)፣ ለወንድሞቹና ለቅርብ ወገኖቹ በሙሉ እግዜር ያጥናችሁ እንላለን።

የቀድሞ የጎሬ ተማሪዎች (ልጆች)

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሯችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሯችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## ክፍል 9

## እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!!

እሷ ወደምትኖርበት እስቴት የተጓዝኩት በአይሮፕላን ነበር። ከመነሳቴ በፊት በነበረው ምሽት አይሮፕላን ማረፊያ የምትጠብቀኝን ቦታና ሰዓት ተነጋግረን ነበር። ታዲያ ጉዞው የአንድ ሰዓት ተኩል ነበርና በዚሁ ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር በአዕምሮዬ ይመላለስ ነበር። እግዚአብሔር በመጨረሻ ያሰብኩትን ሊያሳካልኝ ነው በማለት በለመለመ ተስፋ ነበር የተጓዝኩበት። በተባለው ሰዓት አይሮፕላኑም ካለችበት ከተማ አረፈ። ልቤም ትንሽ መታ ማድረግ ጀመረ። በስልክ ብቻ ድምጿን፣ በፎቶ ብቻ መልኳን የተዋወቅሁዋትን፣ የኑሮ ጓደኛ ትሆነኛለች ብዬ ያሰብኳትን ልጅ ለማየት ቀናት ወደ ሰዓታት ተቀይረው ይኸው ደቂቃዎች ይቆጠሩ ጀመር። ትዝታ በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ (መጋቢት 1986 – March 94 እትም) እንደገለፀችውና "ይህ ሰው እንዳሰብኩት ባይሆንሳ" ብላ እንዳለመችው እኔ አላሰብኩም። ቀና ቀናውን ብቻ ነበር አስብ የነበረው። ከ3 ወራት በላይ ለብዙ ሰዓታት ያነጋገርኳትና ስለእሷም ማወቅ የሚገባኝን ያህል ያወቅሁ ነኝና ምንም ቢሆን ምንም በመቻቻል ልንግባባና ልንጋባ እንችላለን የሚል ቀና ሃሳብ ነበር በአዕምሮዬ የሚመላለሰው።

የተቃጠርነው ዕቃ መረከቢያው (Baggage Claim) አካባቢ ነበርና ወደዚያው እንደሄድኩ ከሩቁ አየሁዋት። እንደነገረችኝ ራንግለር ሱሪ ለብሳ ጠቆር ያለ ኮት ብጤ ደርባለች። ፊቷን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙራ ኖሮ መጀመሪያ ከጉን በኩል አይቼአት እሷ መሆኗን አረጋግጬ ከኋላዋ ትከሻዋን ነካ አደረግሁት።

"ታዲያስ ትዝታ" አልኳትና በፈገግታ ተመለከትኳት።

"ምን ፈለግህ?" አለች፣ ድንጋጤ አይሉት ቁጣ፣

ግራ በተጋባ መልክ ጨበጥኳትና ጉንጯን ሳም አደረግሁ። እጇ ይንቀጠቀጥ ነበር። ቆማ ዝም ብላ አንዴ እኔን አንዴ ወደሌላ አቅጣጫ ትመለከት ጀመር። እሷ ጋ የመጣሁ መሆኔን የዘነጋችም መሰለኝ። ዝም ብላ መቆሟን ሳይ ሌላ የምትጠብቀው ነገር ያለም መሰለኝ።

"ዕቃዬን ተረክቤያለሁ" አልኳት።

ከእንቅልፍ እንደባነነች ሰው ዓይነት ሆነችብኝና "ተረከብክ እንዴ?" አለችና እንድንሄድ ጋበዘችኝ።

መኪናዋ ከቆመበት ቦታ ድረስ ሄድን። ማውራት የለም፤ ምንም የለም። ብቻ ገልመጥ ገልመጥ እያለች ታያለች ከኋላዋ የረሳችው ነገር ያለ ይመስል! ዕቃዬን መኪናዋ ውስጥ ከተትንና እሷ እየነዳች ሄድን። አነዳዷ በጣም አደገኛ ዓይነት ነበር። ፓሊስ የሚያባርረው ወንጀለኛ ዓይነት መስሎ ታየኝ። መንገዱ ከሚፈቅደው ፍጥነት በላይ መንዳቷን ስመለከት።

"ትንሽ አልፈጠንሽም" አልኳት እየፈራሁ እየተባሁ።

"እ! እእ! ይቅርታ" አለችና ፍጥነቷን ቀነሰች። ምንም ማውራት የሚባል ነገር አለመኖሩን ስረዳ ትንሽ ሃሣብ ገባኝ። "ምን ሆና ይሆን?" አልኩ በሆዴ።

"ታዲያስ አገራችሁ እንዴት ነው?" አልኳት።

"ደህና ነው" ብላ በአጭር መልስ ተገላገለች። በዝርክርክና ፈጣን አነዳዷ ከአሁን አሁን ተጋጨን እያልኩ ባስብም ምንም ሳንሆን ከቤቷ ደረስን። ከዚያ በኋላ የሆነውን እሷ በተከታታይ በግንቦትና ሐምሌ 1986 ላንዳፍታ እትሞች ላይ ገልፃዋለች።

እቤት ከገባሁ በኋላ በእሷ ላይ ያየሁትን ሁኔታ ሁሉ ለመግለፅ ቃላት ያጥረኛል። የሚገርማችሁ ነገር ቀደም ብዬ ተዋውቄያት ሳነጋግራት የነበረችው ትዝታ በፍፁም ልትሆንልኝ አልቻለችም። ረጋ ባለ መንፈስ ቀስ እያልኩ ሁኔታዋንም ሳጤነው ኢትዮጵያዊም አልመስል አለችኝ። እዚህ አሜሪካ በመኖር ያወቅሁዋቸው ፈረንጆችንም አልመስል አለችኝ። በአጠቃላይ ዕረፍት የነሳት፤ በምታደርገውና በምትናገረው ነገር ሁሉ ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና አለመተማመን ያለባት ነገር ነው ሆና የታየችኝ። ከአለሁበት ከተማ እሷን ብዬ መምጣቴን የዘነጋችም ትመስላለች። ቤቷ ድረስ የመጣሁ፣ ከሆነም የትዳር ጓደኛዋ ልሆን የምችለውን ሰው እንዴት እንደምታስተናግድ ግራ የገባትም ሆና ታየችኝ። እቤት ገብተን ራት ቀርቦ እስከበላንበት ጊዜ ድረስ

ይታይባት የነበረው መቅበዝበዝ ይህ ነው አይባልም። አንዴ መኝታ ቤት፣ ከዚያ ወጥታ ወደ ወጥ ቤት፣ ደግሞ ሽንት ቤት፣ ስትመላለስ አካሄዷ፣ አረማመዷና ጠቅላላ ሁኔታዋ የፊልም እንጅ በውን የሚታይ አይመስልም ነበር። ሰው ይታዘበኛል የሚል ግምት አልነበራትም።

ሁኔታዋ እያሳሰበኝ አልፎ አልፎ ለማቀርብላት ጥያቄ የምትሰጠኝ መልሶች አጫጭር መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ዓይኗን እንደማፍጠጥ አድርጋ ስታወራው የምትቆጣ መምሰልዋ ነው።

ራት ቀርቦ፣ ተበልቶ አንድ ጠርሙስ የወይን ጠጅ ቀርቦ መጠጣት እስከጀመርንበት ጊዜ ድረስ በመካከላችን የተደረጉት የቃላት ልውውጥ በጣም የተወሰኑ ነበር። በአዕምሮዬ የሚንከላወሰውን የጥርጣሬ መንፈስ ለመሸፈን ስል በእብዛኛው ለወሬያችን ርዕስ የማመጣው እኔ ነበርኩ። በሷው ቤት። የወይን ጠጅ መጠጣት ስንጀምር ሁኔታዋ መለዋወጥ ጀመረ። ወይን ጠጅ አጠጣጧ ትንሽ ጠንከር ያለ ሆኖ ታየኝ። ብርጭቆውን ብድግ አድርጋ ፉት ባለች ቁጥር የፈገግታዋና የደስተኛነት መጠን እያደገ መጣ። ቀልቧ ሰብሰብ እያለ መምጣቱ ሲሰማኝ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ በሆዴ ሳቅሁ። እንዲህ ከሆነማ እሷን ካገባሁ የወር አስቤዛችን በቪኖ ማለቁ ነው የሚል። አንደኛውን ብርጭቆ ጭልጥ አድርጋ ሁለተኛውን እንዳጋመሰችው ትንሽ እንደመቁነጥነጥ አለችና እሷ ጐን ካለው መቀመጫ ጋበዘችኝ። ኮቴንም ባወልቀው ጥሩ እንደሚሆን ምክሯን ለገሠችኝ። ቀደም ሲል የወሬ ርዕስ የጠፋት አሁን እኔን አላስወራ ማለት ጀመረች። እሷ በዚያ ወቅት ይሰማት የነበረውን ሁኔታ በግንቦት 1986 (May 1994) ላንዳፍታ እትም ላይ ገልፃዋለች ። የነበረውን ሁኔታ ለእሷ እንዳለችው ይሁን እንጂ እኔ ይሰማኝ ከነበረው ሁኔታ ጋር እንድታገናዝቡት የዚያን ዕለት ምሽት የሆነውን ብነግራችሁ ደስ ይለኛል።

አጠገቧ ካለው መቀመጫ እንድቀመጥ ከጋበዘችኝ በኋላ ምናልባት "በረዶውን ለመስበር" (Breaking the ice) ይረዳንና የበለጠ ተግባብተን ለማውራት እንችላን በሚል ጠጋ ብዬ ሰውነቷን እያሻሸሁ ለበለጠ የፍቅር ጨዋታ እጋብዛት ጀመር። ሰውነቷን ነካ አድርጌ ማሻሸት ስጀምር መቅለጥ ጀመረች። የጠጣችው ቪኖ የሚያደርገው ግፊትም ይሁን የእሷ የራሷ የጋለ የወሲብ ስሜት ጠጋ ባልኳት ቁጥርና ነካ ባደረግሁዋት ቁጥር የበለጠ ጠጋ፣ የበለጠ መነካት ትፈልጋለች።

መቼም የወሲብ ፍላጐት አንዴ መጋጋል ከጀመረ ወደ ኋላ መመለስ እንምይችል አሳምሬ አውቅ ነበርና ፍላጐቷን ከማሟላት ወደ ኋላ አላልኩም። ጉረኛ እንዳትሉኝ እንጂ እንዲህ ነዶ ተቃጥሎ ለመጣ ለጋለ ስሜት መድኃኒት እንደሆንኩ ብዙ የተወራልኝ ስለነበርኩ አውቀዋለሁ። ደግነቱ የምትኖረው በራሷ ቤት ሆነ እንጂ አፓርታማ ቢሆን ኖሮ ትዝታ ባሰማችው የወሲብ እርካታ ሲቃ ጐረቤት ጉድ ባለ ነበር። ጉረኛ እንዳትሉኝ አደራ ብያለሁ።

መኝታ አልጋ ሳያደርሰን እዚያው ራት ከተበላበት ቦታ ያካሄድነው የፍቅር ጨዋታ እንዳበቃ ትዝታ ጠባይዋ ቅይርይር አለ። እየተንጫነጨች ተነስታ ወደ ንፅህና ክፍል ገባችና እዚያው ቅርቅር ብላ ቀረች። እኔ በላብ ተጠምቄ ከአሁን አሁን ትወጣልኛለች ብዬ ብጠብቅ አልወጣ አለች። ቢቸግረኝ ተነሳሁና እሷ ያላሳየችኝ ሌላ የንጽሕና ክፍል እንዳለ ብዬ ፍለጋ ገባሁ። ቤቱ ባለ አንድ ፎቅ በመሆኑና እኔ እስካሁን ያለሁት በምድር ቤቱ ውስጥ በመሆኑ ፍለጋዬም እዚሁ አካባቢ ነበር። በዚሁ በምድር ቤቱ ባለው ንፅህና ክፍል እሷ ገብታበታለች። ሌላኛው ያለው እንግዲህ (ካለ ማለቴ ነው) ላይኛው ፎቅ ላይ ነው፡፡ ላይ ደግሞ ለመውጣት ገና መብቱ አልተሰጠኝምና ተመልሼ መቀመጫዬ ላይ ቁጭ አልኩ። ቆይታ ቆይታ ከመታጠቢያ ቤቱ ወጣች። ገላመጠችኝና ወደ መኝታ ቤቷ ለመሄድ ደረጃውን መውጣት ጀመረች። ተነስቼ ተራዬን ንፅህና ክፍል ገባሁ። ተጣጠብኩና መቼም ሌላ መኝታ ቤት አልተነገረኝምና ፎጣውን ደርቤ ያው መቼም ሌላ መኝታ ክፍል ካልሰጠችኝ እዚያው ና ማለቷ ነው ብዬ በመገመት እሷ ወዳለችበት ክፍል አዘገምኩ። መኝታ ክፍሏ ስገባ አልጋው ዳር ቁጭ ብላ ፀጉሯን ታስተካክላለች። ስገባ ፊቷን ዞር አደረገች። እንዳልገባው መስዬ ሄድኩና ጐኗ ቁጭ አልኩ።

«ትንሽ አታፍርም?» አለችኝ

«ምነው ምን ሆነ?» አልኳት

«ያደረግኽውንማ ታውቃለህ፤ እንዲያው በመጣህ በመጀመሪያ ቀን sex ላይ ስትሮጥ» አለችኝ። የምለው ጠፋኝ። ለዚህ ሁኔታውን አመቻችታ የጋበዘችኝ እሷው ሆና እኔን ይህን ማለቷ ትንሽ አናደደኝ።

«ወንዶች ስትባሉ ይኸው ናችሁ። በሴቶች ላይ advantage መምታት ትፈልጋላችሁ። በዚህ ላይ ደግሞ እኔ ልጅት እንዲያው ሜዳ ላይ እንዳገኘኻት ሴት ተራ አልምሰልህ ቢገባህ» አለች። ድምጿ እየከረረ፣ ቁጣዋ እየጋለ መሄዱ ሲሰማኝ ከአጠገቧ ተነሳሁና ቆምኩ።

«የእኔ እህት አንቺ እንዳልሽው እኔ በአንቺ advantage ለመምታት አልሞከርኩም።» አልኳት። የእኔም ውስጤ እየጋለ መሄዱ ተሰማኝ።

«ነው እንጂ፤» አለች።

«ካልሽስ you asked for it አንቺው ነሽ ለዚህ የጋበዝሽኝ። እኔ በሃሣቤም አልነበረ» አልኳት።

«you asked for it ??» አለች ጥያቄም፣ ቁጣም፣ ጩኸትም ባዘለ አነጋገር፣ «ወይኔ እኔ ልጅት» አለችና ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሳች። ተፋጠጥን።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# አዲሱ የግብረ ሠናይ አዋጅ (ዌልፌር ሪፎርም) በፍልሳውያንና (ኢሚግራንትስ) በስደተኞች (ሬፊውጅ) ላይ ስለሚያስከተለው ተፅዕኖ

## (IMPACT OF WELFARE REFORM ON IMMIGRANTS AND REFUGEES)

ከስደተኛ ዘገባዎች አለፍ አለፍ ብሎ የተቀነጨበ።
Exerpts from REFUGEE REPORTS, NOV. 19, 1996)

ኦገስት 22, 1996 ርዕሰ ብሔር ክሊንተን የግብረሠናዩን አዋጅ በሕግ እንዲፀድቅ ፈርመውታል። የአዋጁ ስም «የግላዊ ኃላፊነትና የሥራ ዕድል የ1996 አስታራቂ ድንጋጌ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። በእንግሊዝኛው "PERSONAL RESPONSIBILITY AND WORK OPPORTUNITY RECONCILATION ACT OF 1996" ይባላል። የአዋጁ መሠረታዊ ዓላማ በግብረሠናይ ላይ ሕይወታቸውን የመሠረቱትን ሕዝቦች ራሳቸውን ይችሉ ዘንድ ወደ ሥራ መስክ ማሰማራት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አዋጁ ሕጋዊ ፍልሳውያን (Legal immigrants) በማዕከላዊ መንግሥት የሚደጐሙ ዕርዳታዎችን (Federally funded benefits) እንዳያገኙ ወይም የማግኘትም ዕድላቸው እንዲጠብ በማድረግና የመንግሥት ወጭን በመቀነስ የበጀቱ ጉደሎነት (Budget deficit) እንዲስተካከል ይረዳል ተብሎ ታምኖበታል።

ይህ የግብረሠናይ (Welfare) አዋጅ የሪፖብሊካኖችና የክሊንተን መስተዳድር ዐቢይ የፖለቲካ ቁምነገር ነው።

በመጀመሪያ ሕጉ የሚያብራራው ቤተሰቦች የግብረሠናይ ዕርዳታ የሚያገኙት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን ነው። ጊዜን ይወስናል። ማንኛውም ለመሥራት የሚችል ዜጋ በሁለት ዓመት ውስጥ በሥራ መሠማራት አለበት። ነቃፊዎች ወይም ሒሳውያን(critics) ሕጉ የግብረሠናይ ተረጅዎችን ደጉሞ ራሳቸውን እንዲችሉ ካለማድረጉም በላይ በርካታ ሕዝቦችንና ሕፃናትን ወደባሰ የድህነት መቀመቅ እንደሚያስገባ ይናገራሉ። እንደ <u>የበጀትና የፖሊሲ ቅደም ተከተል ማዕከል</u> (CENTER ON BUDGET AND POLICY PRIORITIES) አባባል ከሆነ «የአዋጁ መሠረታዊ ተፅዕኖ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ላይ በመሆኑ ድህነትን ከመጨመሩም በላይ በተለይም ሕፃናትንና ሕጋዊ ፍልሳውያንን በመጉዳት ድኃው የበለጠ ድኃ እንዲሆን ያደርጋል።»

የአዋጁም ደጋፊዎች ግብረሠናይ የምፅዋት ወይም የችሮታን ባሕል ለማሳደግና ሕዝቦችም በዚህ መንጠላጥል ላይ በመመካት የሥራ አፍላቂነትና አምራችነት እንደተለያቸው በማተት ዳግመኛም ይህ እጅን ዓይቶ የመኖር ሁኔታ የሕዝቦችን ስሜት በማዳሸቅ የሚጎዳ በመሆኑ ግብረሰናይ ሲጠፋ ወይም ሲቀየር ሕዝቦች ሥራ ይይዛሉ ወይም ይፈልጋሉ ይላሉ። ይህም የራስን በራስ መቻል መርሆ በማስረፅ ሕዝብ ታታሪና አምራች እንዲሆን ይረዳል ይላሉ። በዚህም ክርክር ላይ ለምሳሌ የቴክሳሱ ሪፖብሊካን ላማር ስሚዝ «ግብረሠናይ ልጆቻችንን፣ ቤተሰቦቻችንንና ግብር ከፋዩን ሕዝብ (Tax payers) በመጉዳት እንደዚሁም ለተሻለ ሕይወት የሥራ አነሳሽነትን በመንፈግ ሕዝቡን ወደ እጅ አይቶ የመኖር ተጠዋሪነትና መመካት እንዲሁም የባሕል መዳሸቅ ውስጥ ከቶታል» በማለት በቅርቡ ሐሳባቸውን ሰጥተዋል።

የፍትሕ ተሟጋች ድርጅቶችና ግለሰቦች አዋጁ ሚዛናዊነት የጐደለው ነው ይላሉ። ሕጉ ሕጋዊ ፍልሳውያንና ስደተኞች ላይ በአድልዎ አነጣጥሯል በማለት ይከራከራሉ። የብሔራዊ ፍልሳውያን (የፍልሰት) የሕግ ማዕከል (The National Immigration Law Center) «በዚህ ሕግ ከተገፉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ከፍተኛ በደል የሚደርስባቸው ፍልሳውያን ናቸው» ይላል።

በመጨረሻው የሴኔቱ የግብረሠናይ አዋጅ ውይይት የኬኔክቲኬቱ ተወካይ ሴንተር ክሪስቶፎር ዶድ «ለሕጋዊ ፍልሳውያን በምርጫ ውስጥ ስለማይሳተፉ ብቻና እነርሱንም ማጥቃት ቀላል ስለሆነ ዋስትና አንሰጣችሁም ማለት ትልቅ ስህተት ነው፤ ... እንደዚህ ዓይነቱ እነርሱ ላይ ያነጣጠረው የአዋጁ ዒላማ ጉጂና ከፋትንም ያዘለ ነው» ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል።

፩) <u>የመብት ተከራካሪዎች በሀገሪቱ ስላለው አንዳንድ ቀውስ ፍልሳውያን ማማኻኛያና ቁጣን መወጫያ ሆነዋል ይላሉ።</u>

የሕብረተሰብ መብት ተከራካሪዎች ይህ አዋጅ ሚዛናዊ ባልሆነ መንገድ የሀገሪቱን ኅብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምክንያት ለማምታታት ፍልሳውያንን እንደመነሻ አድርጐ የሚያቀርብ ነው በማለት ይከራከራሉ። ርዕሰ ብሔሩም አዋጁን በፊርማቸው ቢያፀድቁትም አንዳንድ የድንጋጌው አንቀፆች ሕጋዊ ፍልሳውያንን እንደሚጐዱ አልደበቁም። በመቀጠልም «ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ ሌት ተቀን የሚባዝኑትን ይጐዳል፤ ታክስ ከፋይና በጦር ሠራዊቶቻችንም ውስጥ የሚሳተፉትን

ፍልሳውያን ይማናቸዋል ብለዋል። እርሳቸውም አንዳንድ ግልፅ የሆኑትን ጉዳይ ፀረ–ፍልሰት ዕቀባዎችን(restrictions) እንደሚቀለብሱ በአደባባይ ተናግረዋል። የአሜሪካ የእርሻ ልማት መንግሥታዊን አካል (Department of Agriculture) የምግብ ፕሮግራምን ለሕጋዊ ፍልሳውያን አዋጁ በግብር (ከአገስት 22, 1997 ጀምሮ) እስከሚተረጉም ድረስ እንዳይቆርጥ ወይም እንዳያቆም ትዕዛዝ አስተላልፈዋል።

፪) <u>ያልተመዘገቡ ፍልሳውያን (Undocumented Immigrants) ምንም ዓይነት የረባ ዕርዳታ እንዳይሰጣቸው ተደርጓል</u>። ሆኖም የሚከተሉትን ያገኛሉ፦

- በሚዴኬይድ (Medicaid) በጀት በኩል ለአስቸኳይና ድንገተኛ የሕክምና ዕርዳታ ብቻ፣
- ገንዘብ ነክ ያልሆነና በቁስ የሚተመን (Non-cash, inkind) በሠው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋ (Disaster) ለተጎዱ የሚሰጥ ችሮታ፣
- ለሕፃናት ክትባትና ተላላፊ በሽታዎችን ለመግታት ለሚደረጉ ምርመራዎች። (Immunization & Testing to curb communicable diseases)

፫) <u>ሕጉ በአብዛኛው መልኩ ካልተመዘገቡ ፍልሳውያን ይልቅ ሕጋዊ ነዋሪዎችን ይጎዳል።</u>

አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ያልተመዘገቡ ፍልሳውያን ለመንግሥት ዕርዳታ ብቃት የላቸውም፤ ዕርዳታም አይሰጣቸውም።

- ሕጉ በአካል ጉዳት ለሚመጣ ወይም በአእምሮ መዛባት ለሚከሰት የኑሮ ችግር መንግሥታዊ ደጓሚ ገቢን (SSI, Supplemental Social Security Inocme) ይከለክላል። የምግብ ዕርዳታም አይሰጥም። እነዚህን ሁለት ዕርዳታዎች ለማግኘት ፍልሳውያን የዜግነት ወረቀት ማግኘት አለባቸው። ወደፊት የሚመጡ ሕጋዊ ፍልሳውያን ከሚከተሉት ዕርዳታዎች ይከለከላሉ። ይህም ለመጀመሪያ 5 ዓመት ይሆናል።
- ለድኃ ቤተሰቦች የሚሰጥ ጊዜያዊ ዕርዳታ (TANF-Temporary Assistance To Needy Families)
- ሕፃናትን ለሚያሳድጉ የሚሰጥ ዕርዳታ (AFDC-Aids to Families with dependent children)
- ለድንገተኛ በሽታ ብቻ ያልሆነ የሕክምና ዕርዳታ (Nonemergency Medicaid)

፬) <u>አዲሱ ሕግ ስደተኞችን (REFUGEES) ለ5 ዓመት ይረዳል</u>።

እነዚህም በፖለቲካ ምክንያት ወደ አሜሪካ የመጡትን ጥጋውያንን (Asylees) እና የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄያቸው አሳማኝ ወይም ተገቢ በመሆኑ ለጊዜውም ቢሆን ወደሀገራቸው እንዳይመለሱ ፈቃድ የተሰጣቸውን ያጠቃልላል። ከ5 ዓመት በኋላ ዕርዳታ አያገኙም። በሌላ በኩል ደግሞ በአሜሪካ ጦር ሠራዊት ውስጥ የሚያገለግሉትን፣ በጦርነት የተሳተፉትንና ሳያቋርጡ 10 ዓመት የሰሩትን (እየሰሩ ታክስ የከፈሉትን) ሕጉ አይመለከትም። የምግብ ዕርዳታ የዋስትና መደጎሚያ ገቢ ያገኛሉ። (Food stamps and Suplemental Social Security Income) ሌሎችንም ዕርዳታዎች ያገኛሉ። (TANF, AFDC, TITLE XX funded Services)

፭) ፍልሳዊ (Immigrant) ጓደኛዎ ወይም ዘመድዎ እዚህ ከመጣ በኋላ ዕርዳታ ለማግኘት መንግሥትን ከጠየቀ፣ ዕርዳታውንም ሕጉ የሚፈቅድለት ከሆነ የአስመጭው ገቢ ተደምሮ ከታየ በኋላ ነው የዕርዳታ ብቁነት የሚታወቀው። (ለምሳሌ እኔ እህቴን በሕጋዊ መንገድ ከኢትዮጵያ ባስመጣና እዚህ ሥራ ብትጀምር የምታገኘው በቂ ባይሆንና ኑሮ ባይሳካላት ዕርዳታም ብትጠይቅ የሁለታችንም ገቢ (Income) መደመር አለበት፤ ምንም እንኳ ከእኔ ጋር ባትኖርም። ይህም የኃላፊነት ስሌት (FIGHTING BACK)(DEEMING PROVISION) ይባላል።

፮) <u>ይህን አዋጅ ለመቀልበስ በሕገ መንግሥቱ መሠረት በፍርድ ቤት መታገል</u>

በርካታ ለፍልሳውያን ጥብቅና የቆሙ ድርጅቶች አንዳንድ የአዋጁን አንቀፆች ለማሻር ፍርድ ቤት መዝገብ ለመክፈት እያቀዱ ነው። ክሱንም መመስረት አስፈላጊ ነው የሚሉት የሕገ መንግሥቱን የተሻሻለውን 14ኛ አንቀፅ(14th Ammendment) በመጥቀስ ነው። የአሜሪካ የተሻሻለው 14ኛው የሕገ መንግሥት አንቀፅ ከዚህ ጋር ሲዘረዘር በትውልድ ወይም በዜግነት ወይም በብሔር ወይም በፆታ ... ወዘተ አድልዎ ክልክል እንደሆነ እነዚህ ተከራካሪዎች ያስረዳሉ። (* ለምሳሌ ስደተኞችን ወይም ፍልሳውያንን የሚጎዳው የካሊፎርኒያው አንቀፅ 187 (Proposition 187) አሁን ፍርድ ቤት ቀርቧል። ለዚህም የላቲኖ ፍልሳውያን ያደረጉት ትግልና ፍልሚያ ሁላችንንም የሚያኮራ ነው።)

ትርጉም፦ከኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማህበር
የጥናትና የምርምር የዝግጅት ክፍል
Ethiopian Community Association of Missouri
(ECAM)
2336 Tennessee Ave, St. Louis, MO 63104
Phone: (314) 776-7464
Fax: (314) 776-0401

# የአባትና የእናት አደራ ለልጅ፤ የሐቀኛ ኢትዮጵያውያን የሕዝብ ልጆች ትብብር በሴንት ሉዊስ

አባትና እናት ለልጆቻቸው ከሚሰጡት ትልቁና ክቡር ምክር ተባብራችሁ ስሩ፤ ችግራችሁን በጋራ ተወጡ የሚለው ነው። እኛም የዚህ አደራ ጠባቂዎች ነን። በታሪካችን ሕዝባችን በትብብርና በአንድነት የተወጣቸው ችግሮች ብዙ ናቸው።

በስደት ላይ እንኳን ድርጅት መስርቶ ግልጋሎትን መስጠት ይቅርና ራስንም ማስተዳደር ቀላል አይደለም። ይልቁንም እናት ሀገራችንን እንደመርዝ የበከላት የጐሳ በሽታ በስደትም ላይ ስለሚንፀባረቅ ይህንንም ጠንክሮ በመታገል ለሁሉም ወገን በእኩልነት ግልጋሎት መስጠት ማኅበራችንን አጠናክሮታል። የዛሬ 13 ዓመት April 13, 1983 ይህንን ማኅበር መሰረትን። በሒደቱ ወቅት ያላጋጠመን ችግር፣ ያልተወጣነው ወጥመድ አልነበረም። ሁሉንም ችግር በእርጋታና በአስተዋይነት እንደዚሁም በብልሀት በመወጣታችን ዛሬ እንኳን ለኢትዮጵያውያን ቀርቶ ለማንኛውም ግልጋሎት ለጠየቀ የአፍሪቃ ዜጋና የመካከለኛው ምሥራቅ ተወላጅ ሰብዓዊ ዕርዳታ እንሰጣለን። ባለፉት 3 ዓመታት ከተገልጋዮቻችን ውስጥ ኤርትራውያን፣ ሱዳናውያን፣ ሱማሌዎች፣ ዐረቦች፣ የዛየር ተወላጆች፣ የሩማንያ ዜጋ፣ የብሩንዲ ዜጋ፣ የናይጄሪያ ዜጋ፣ አሜሪካውያን፣ ታይላንዶችና ሌሎችም ይገኙባቸዋል። የሀገራችንን ባሕልና ታሪክ ቅርሳችን በመሆናቸው ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ለሕዝብ አስተዋውቀናል።

ከታሪካችን ማኅደር ለጥቁር ሕዝቦች አኩሪ ክብርን ያጐናፀፈውን የአድዋ መቶኛ ዓመት በዝነኛው የትምህርት ተቋም በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ አክብረናል፤ በጋዜጦችና በሬዲዮ ጣቢያዎች ለአድማጮች አስተምረናል። በድንገተኛ አደጋ ለተጐዱ ወገኖቻችንና ጊዜያዊ ችግር ለሚደርስባቸው የኮሚኒቲ አባላት ቀድመን በመድረስ ችግራቸውን ፈትተናል፤ የባሕል መደንገጥ (Cultural shock) የመታቸውን መልሰን አቋቁመናል። ቤተሰብን ከቤተሰብ ከባሕር ማዶ ሳይቀር አገናኝተናል። በዘረኛ አሠሪዎች ለተገፉ ጥብቅና ቆመናል፤ በአደባባይና በሆስፒታሎች ቋንቋ ለሚያስቸግራቸው ተርጉመናል ... ብዙም ብዙም ቁም ነገር ሠርተናል። ራስን ማመስገን አይሁን እንጂ ጠንክሮ አብሮ በመስራትና «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» የሚለውን መርህ በግብር በመተርጐም በአንድ እግሩ የቆመውን ማኅበራችንን ዛሬ ተዝናንቶ በሁለት እግሩ እንዲቆም አድርገናል። ሥራችን እየመሰከረና እየተናገረም ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ በተዓምር የመጣ አይደለም። የማፈራረስ ሸርን፣ ማንቋሸሽን፣ ጥላቻ መዝራትን፣ ክፍፍል መፍጠርን፣ ስድብን፣ አሉባልታንና ማጣጣልን ታግለናል። አሸንፈናልም። ከሌሎች ማኅበራትና ድርጅቶች ትምህርት በመውሰድና ለውኸንብር ክብር ሳንሰጥ (Dignify ሳናደርገው) በአልሚ ዕቅዶች ላይ ብቻ በማተኮር እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል። የዲሞክራሲን ጐን በማሳደግ የሚመጣውን ነቀፌታ ሁሉ ከመብት አንፃር በማየት ሁሉም እንዲሳተፍ አድርገናል። «አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማምና» አልሰማሁም እያለ የተሰሩ በጐ ተግባሮችን የሚያንቋሽሸውንም ሳይቀር ከእኛ እንዳይቀር ቀስቅሰነዋል። በአንድ አጋጣሚ ምክትል ሊቀመንበሩ ሲናገሩ "እኛ የሁሉም ኃላፊነት አለብን፣ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አመራር ነን፣ ስለሆነም ሁሉም ወገናችን ነው፣ ሥራችን ልክ እንደ አሜሪካ ፕሬዚዳንት ሥራ ነው። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለመረጧቸውም ላልመረጧቸውም በተጠየቁበት ሁሉ ግልጋሎትን ይሰጣሉ። ማኅበርን በበጐ ፈቃደኛነት ጠንካራ አመራር በመስጠት መገንባት አለብን፤ ጐጂ ነገሮችን (Negativism) አንቀበልም፤ ግን ገንቢ ነቀፌታን አንፈራም። ለሀገራችን የሚበጅ ዲሞክራሲ እዚሁ መመስረት አለብን። ራሳችንን ነፃ ሳናወጣ ለሌሎች መታገል አንችልም» ብለዋል። በመቀጠልም ሁልጊዜ የሚጠቅሱትን ጥቅስ ለግሰዋል «ትናንሽ ግለሰቦች ስለሰው ያወራሉ፤ ትልቅ ጭንቅላት ያላቸው አሳቢ ግለሰቦች ስለዐቢይ ቁምነገር በጐ ተግባር ሌት ተቀን ይሰራሉ፤ ትላልቅ ሰዎች ስለበኩር ጉዳይ ይወያያሉ፤ ትናንሽ ሰዎች ስለሰው አሉባልታ ያስራጫሉ» ብለዋል።

ከደም ምድር ኢትዮጵያ በመለስ ምንም እንኳ ደም ባይፋሰስም ለሴንት ሉዊስ የኢትዮጵያውያን ማኅበር ለ13 ዓመታት ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎበታል። ሌላው ቀርቶ ግለሰቦች ለበርካታ ወራት ክፍያ ሳይጠይቁ ድርጅቱን ገንብተዋል። የልጆቻቸውን ወተት መግዣ፣ ጊዜያቸውን፣ የቤት ኪራያቸውንና ምግባቸውን ሰውተው ለድርጅታቸው ዕድገት በመቆርቆር የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። የስደት ሐቀኛና የፍትሕ ታማኝ አርበኞች ናቸው። ነገ ታሪክ ይመዘግባቸዋል። እንደጂዊሽ ኮሚኒቲ፣ እንደአይሪሽ ኮሚኒቲ ለ50 እና 100 ዓመት በኢትዮጵያዊነታችን የጥንካሬ ታሪካችንን ማስመዝገብ አለብን ይላሉ። ይህንን ለበጐ ተግባር የተሰለፈ ጠንካራ ሕዝብ ማንም ሊፈታተነው አይችልም። ይህ ሁሉ የአመራር ብስለት ነው።ከዚህ በፊትም የነበረው ቦርድ ይህ ነው የማይባል አኩሪ ታሪክ ፅፎ አልፏል። አሁንም በ11/30/96 የተመረጠው ቦርድ ትልቅ ቁምነገር ሠርቶ ለልጆቻችን ለማሳለፍ ቃል ገብቷል። ስብሰባውን የመሩት የኮሚኒቲው ሊቀመንበርም "ለሐቀኛና የአንድነት ወገኖች የምናሳስበው ለታሪካችን፣ ለአብሮ በመቻቻል መኖር ብሎም ለፍትሕና ለሰብዓዊነት ጠንክረን መታገል አለብን፤ ልጆቻችን የሚኮሩበትን በጐ ተግባር በአወንታዊ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር ታሪክን ሠርተን ማለፍ

አለ-ብን። መጭው የሕይወት ዘመናችን ከኖርንበት አይበልጥም። ቁም ነገር ሰርተን ለመጭው ትውልድ አርማችንን ማስረከብ ይኖርብናል» በማለት በሳል አነጋገራቸውን ከቀልዳቸው ጋር በትምህርታዊነት ለግሰዋል። የዚህን ትውልድ ኃላፊነት በማስተማር ሕሊናችንን ኮርኩረዋል።
ትልቁ ትኩረታችን የኮሚኒቲ ማዕከል (Community Center)፣ የኢትዮጵያ ቤተመፃሕፍትና ቅርሳ ቅርስ ወመዘክር መገንባት ነው። አባቶቻችንና እናቶቻችን ያወረሱን አደራ ስላለ አሁንም ታሪካችንንና ባሕላችንን በአሜሪካ እንገነባለን። ከሌላውም የአሜሪካ ዜጋ በመማማር አሜሪካንንም እናለማለን። እኛም እየሰጠን ከእነርሱ እንወስዳለን። በመንገዳችን ላይ የሚደነቀረውን ከመጤፍ ሳንቆጥር ለልማት፣ ለአንድነት፣ ለፍትሕና ለብልፅግና ወደፊት እንገሰግሳለን። እናንተም ለCommunity Center ግንባታ ለመርዳት ከፈለጋችሁ በአድራሻችን ተገናኙን እንላለን። ከእኛም ተመክሮ ተማሩ። ታሪክ ያላት ሀገራችን የሚታይ ትንሽ ወመዘክር እንኳ በአሜሪካ የላትም። ዛሬም ነገም ተነገ ወዲያም ለባሕላችን፣ ለታሪካችን፣ ለፍትሕ፣ ለአንድነታችንና ለሰብዓዊ ዕርዳታችን ወደ ኋላ አንልም። በጐ ነገር ለሚያቅዱ ሁሉ፣ ሰላምንና ፍትሕን ለሚፈልጉ ሁሉ ከጐናችሁ ሆነን እንታገላለን።

እባካችሁ ፎቶግራፎችን ባለመላካችን ይቅርታ አድርጉልን። በሚቀጥለው ጽሑፋችን እንከሳችኋለን። ለተጠናከሩ አብያተ ክርስቲያናት፣ በመጀመር ላይ ላሉ የኮሚኒቲ ማኅበራት፣ ለሚውተረተሩ ሰብዓዊ ድርጅቶች ለሚታገሉ ኮሚቴዎች፣ ለተጠናከሩ ኢትዮጵያውያን ማኅበራት፣ ለፍትሕና ለአንድነት ለሚሟገቱ ተቋሞችና የሕዝብ ፍቅር ላላቸው ወገኖች አይዟችሁ! በርቱ! ከጐናችሁ ነን እንላለን። «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» የሚለውን መርህ አትርሱ። የእኛም የሚዙሪ መንግሥት መርኅ "UNITED WE STAND, DIVIDED WE FALL" ይላል። ምሥጋናና ክብር ለሴንት ሉዊስ ኢትዮጵያውያን!!

የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማኅበር
2336 Tennessee Ave, St. Louis, MO 63104
Phone: (314) 776-7464
Fax: (314) 776-0401

**Allstate**
You're in good hands.

**4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4**
**Clarkston, GA 30021**
**Phone: (404)508-8978 FAX: (404)299-6266**

AUTO
HOME OWNER'S
RENTER'S
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO



THEODROS
HAILEGIORGIS
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

You're in good hands.

# አጭር ልቦለድ ታሪክ

## የመታጠቢያዋ ሳህን

ከጌታቸው ገ. ወልድ

ቀኑ ቅዳሜ ስለነበር የሰፈራችን ጠጅ ቤቶች በመሸተኞች ተሞልተዋል። በማግሥቱ ሥራ ስለሌለው አጉቴም ተደባለቃቸው። እኩለ ሌሊት ላይ እቤት ሲመጣ ጢምቢራው ወጥቷል።

ልክ የቤቱን በር በርግዶ እንደገባ "ዘውዱ..ዘውዱ..አትሰማም እንዴ...?" እያለ ተጣራ። እንደሰከረ ስለገባኝ ጭጭ አልኩ። "ዘውዱ ...አንተን... አይደለም...እንዴ...የምጠራው" በማለት በድጋሚ ተጣራ። አያይዞም እንደገና በቁጣ "ዘውዱ!" ብሎ ጮኸ።

ከእንቅልፌ እንደባነንኩ ለማስመሰል እየተንጠራራሁና እያዛጋሁ ከብርድልብሴ ከተገለጥኩ በኋላ "አ..አ..ቤት" አልኩ።

"ሳህኗን አቅርብልኝ!" አለ በተዳከመ ድምፅ። ነገሩ ገባኝ። ሊያስመልሰው ነው። አልፎ አልፎ ከልክ ያለፈ መጠጥ ሲጠጣ እንደዚያ ያደርገዋል። "የዛሬው ጠጅ አልተስማማኝም" በማለት አከለ።

"አይ እዳዬ" ለራሴ ካልኩ በኋላ ከአልጋዬ ተነስቼ በመሄድ ሳህኗን አቀረብኩ።

አጠገቡ አልቆየሁም ልክ ጣቱን አፉ ውስጥ ሲዶል ወደ አልጋዬ በፍጥነት ተመልሼ ያስመለሰውን እንዳላይ ወይም እንዳይሸተኝ ፊቴን በብርድ ልብስ ሸፈንኩ። አስገድዶ እንደተያዘ ለግቶ ለግቶ የነበረውን መጠጥ ጉልጉሎ ለማውጣት ሲወራጭ ይሰማል፡፡ አያይዞም አስመለሰው፣ ሆዱን ያስጨነቀው ተንዶልዱሎ ወጥቶ በሳህኗ ላይ ተዘፈዘፈ። እንደገና ጣቱን በማስገባት የቱረፈውን ለማስወጣት ተንገታገተ። ከበፊቱ ይበልጥ አስጨነቀው በመጨረሻ የቀረው እየተንጠባጠበ ወጥቶ በመታጠቢያው ላይ ተጠራቀመ።

"እፎይ! እንዲህ ግልግል እያለ ሰው ሆዱን ያስጨንቃል'' ካለ በኋላ "ዘውዱ ለአፌ መጉመጥመጫ ውሃ ስጠኝ" አለ።

እንደገና ከአልጋዬ ለመውረድ ብርድልብስ ስገልጥ የትውከቱ ሽታ አፍንጫዬን አጠነው። ሊያስመልሰኝ ቃጣኝ፣ ከአልጋዬ በመውረድ በጣሳ ተዘጋጅቶ የተቀመጠውን ውሃ አቀረብኩለት። አፉን ተጉመጥምጦ ሳህኗ ላይ ተፋ።

ሳህኗ እስከጥንቹ ድረስ ድረስ ሞልታለች፣ ለመንካት ያስጠይፋል፣ "ምንአለበት ውጭ ተፍቶ ቢመጣ" አልኩ በልቤ።

"ምን ዝም ብለህ ተገትረህ ሳህኗን ትመለከታለህ! እውጭ አውጥተህ እጠብ!" በማለት ትዕዛዝ ሰጠ። ወዲያው በፍጥነት ሳህኗን በማንሳትና ወደውጪ በመውሰድ አጥሩ አካባቢ ትውከቱን ደፋሁት።

አብዛኛውን ጊዜ "ሳህኗን አጽዳ!" የሚል ትዕዛዝ ይሰጠኛል። ግን ተፈጻሚ አይሆንም። ለስሙ ታጠበች እንዲባል ብቻ ውሃ ሳህኗ ላይ በመጨመር ከአንቀረቀብኩ በኋላ ልቅላቂውን መድፋት ነው። የሳህኗን የውስጥ አካል መንካት በጣም ይቀፈኛል።

ማለዳ ከእንቅልፌ ነቅቼ ፊቴን ለመታጠብ ከቤት ውጭ በሚገኘው ብቸኛ የቧንቧ ውሃ ተጠቀምኩ። በቧንቧው ስር ሆኖ መታጠብ ያስደስተኛል። አያቴ ካዩኝ ግን የዕለት ጉርሴን ይነሱኛል።

"ቧንቧው ሥር እንዳትታጠብ ሺ ጊዜ ነው የነገርኩህ ምን ያህል ገንዘብ እንደምከፍል የሚገባህ አይመስለኝም።" እያሉ አቧሬአቸውን ከለቀቁብኝ በኋላ የሞቢል ዘይት ጣሳ እንድጠቀምበት ሰጡኝ።

ፊቴን እየታጠብኩ ሳለ አጉቴ ከመኝታው ተነስቶ ውሃ እስካቀርብለት ይጠብቀኝ ነበር። ልክ እንዳየኝ በተዳከመ ድምፅ "ዘውዱ...የፊት ውሃ... አምጣልኝ" አለ። የሞቢሉን ጣሳ ውሃ ሞልቼ አቀረብኩለት። መታጠብ ሊጀምር ሲል ሳህኗ እንዳልታጠበች ሲመለከት "ማታ ነግሬህ አልነበረም እንዴ ሳህኗን እንድታጥብ" በማለት በቁጣ ተናገረ።

"እንቅልፍ ተጫጭኖኝ ነበር" በማለት በትህትና መልስ ሰጠሁ። ቁጣው በረደ "በል ውሃውን ራሴ ላይ ብቻ ጨምር" አለ። ማታ በመጠጥ ግሎ ያደረውን ጭንቅላቱን ለማቀዝቀዝ። ሳህኗ ወዲያው ሞላች፣ "አውጣና አፍስ!" በማለት አዘዘ። ጨምላቃዋን ሳህን አግቼ አጥሩ አቅራቢያ በመውሰድ ውሃውን ረጨሁ። "ውጭ ወጥቶ ቧንቧውን ቢጠቀም ምን ይጎዳዋል" አልኩ ለራሴ፣ ሳህኗን ሳላጥብ ወደትምህርት ቤት አፈተለኩ።

ቤቱ ውስጥ አብሬአቸው ከምኖረው ጋር ከአንዳቸውም ስምምነት አልነበረኝም። እዚያ የምኖረው ለመኝታው ስል ነበር። ከትምህርቴ ውጭ በሲኒማ ቤት ስለምሠራ ለእንጀራቸው ደንታ የለኝም። አያቴ ቀብቃባ ሴት ነበሩ። እዚያ መብላት እንዳቋርጥ ያስገደደኝ የመጨረሻ ንግግራቸው ምንግዜም ከአእምሮዬ አይጠፋም። ዘወትር ጥዋት

ትምህርት ቤት ለመሄድ ስዘጋጅ ለቁርስና ለምሳዬ ሃያ አምስት ሳንቲም ይሰጡኝ ነበር። አንድ ማለዳ የተለመደውን ድርጐዬን ለመቀበል ወደ አያቴ ተጠጋሁ።

"እስቲ ሌሎች የሰፈሩን ልጆች ተመልከት፣ ለቤተሰቦቻቸው ሸክም አይደሉም። ሊስትሮነት፣ ኩሊነት ሌላም ሌላም ሥራ እየሰሩ ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ሲያመጡ አንተ ግን እኛን ትበዘብዛለህ። ትምህርት ቤት ስትመላለስ ይኼው ስምንት ዓመት አልፎአል። እስካሁን ያየሁት ነገር ቢኖር፣ 'ሁለተኛ ክፍል ገባሁ' በዓመቱ ደግሞ 'ሶስተኛ ክፍል ገባሁ' በተከታዩ ደግሞ 'አራተኛ ክፍል ገባሁ' የምትለው ፈሊጥ ነው። ያንተ ክፍል እንጀራ ሆኖ አንበላው ... በማለት ተንጣጡብኝ። ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ጥያቸው ሄድኩ። ከዚያ ቀን ወዲህ ለአምስት ሳንቲም እንኳን አጠገባቸው ድርሽ ብዬ አላውቅም።

አካባቢው ለሥራዬ ቅርበት ስላለው እንጂ ለመኝታ ሌሎች ቦታዎች አይጠፉም ነበር። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እስካጠናቅቅም መሐይሞችን መቻል ነበረብኝ። አጐቴና እኔ የምንተኛው በአንድ አነስተኛ ክፍል ውስጥ ነበር። ክፍሉ በተለያዩ ቁሳቁሶች ተጨናንቋል። የአጐቴ አልጋ በስተቀኝ የእኔ በስተግራ፣ በሁለቱ አልጋ መሃል አንድ ብጥሌ ጠረጴዛ ተቀምጣለች። ከእኔ አልጋ በስተግርጌ ሌላ ጠረጴዛ ላይ የተለያዩ መጠን ያላቸው ሳጥኖች ተደራርበው ተቀምጠዋል። የአልጋዎቻችን ሥር በሌሎች የካርቶን ሳጥኖችና ትርኪምርኪ ዕቃዎች ታምቀዋል። ግርግዳው በተለያዩ ጊዜያቸው ባለፉ የቀን መቁጠሪያዎችና የሲኒማ ቤት ፖስተሮች ተሸፍኗል። ግርግዳውን ከሸፈኑት ወረቀቶች ስር ትኋንና ሌሎች ተባዮች ይርመሰመሱባቸዋል። ከመግቢያው በር አጠገብ ከአጐቴ አልጋ ግርጌ ሌላ አነስተኛ ጠረጴዛ ትገኛለች፣ በእሷ ላይ ያቺ አርጂታዋ ሳህን ተጐልታለች።

አንድ ሌላ ቀን በጧት ተነስቼ ከመሄዴ በፊት ማታ የተቀመጠለትን ውሃ ለመቀየር ጣሳውን ለማንሳት ስጠጋ ሳህኗ በብጣ ውሃ ተሞልታ ተመለከትኩ። ሽታው አያስጠጋም፣ የአጐቴ ሽንት ነበር። "በስመ አብ" ብዬ ሁሉንም ነገር ለአክስቴ ትቼ ከቤቱ ሹልክ ብዬ ልወጣ ስል አጐቴ ከእንቅልፉ ነቅቶ "ሳህኗን ማጽዳት እንዳትዘነጋ!" በማለት የተለመደ ትዕዛዙን ሰጠ። የሳህኗን ጫፍ ከመንካቴ በፊት ለጥቂት ሲኮንድ ደንዝዤ ቆምኩ። በመጨረሻም በቀስታ አንስቼ አጥሩ ጋ ወስጄ ሽንቱን ረጨኹ። ከዚያም እሳህኗ ላይ ውሃ ጨምሬ ጥቂት አንቀርቅቤ ውሃውን ደፋሁ።

ምንም እንኳን አጐቴ የወጣትነት ጊዜው ያለፈ ቢሆንም አድራጐቱ እንደጐረምሳ ነው። ለአጭር ጊዜ ባለትዳር ሆኖ ሚስቱን ከፈታ በኋላ የሴቶች ዓይነት ቤቱን ጐብኝተዋል።

አንድ ምሽት በሰፈራችን የምትገኝ አንዲት ሴት ጐትቶ መጣ። ሞቅ ያለው ይመስላል። እቤት ውስጥ እንደገቡ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው መነጋገር ጀመሩ። ጆሮዬን ወደነሱ አቀናሁ።

"ተኝቷል?" በማለት ሴትዮዋ ጠየቀች።

"እባክሽ ስለእሱ አትጨነቂ እሱ ሲተኛ እንደሬሳ ነው" በማለት አጐቴ አስረዳ።

"አይ ጣጣዬ! እንደሬሳ ነው የሚተኛው ካለ እንደሬሳ መተኛት አለብኝ" አልኩ ለራሴ። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አልችልም። ተባዮቹ ግን ሰላም ነሱኝ። ድፍን የተባይ ዘር እኔ ን ለማጥቃት በደቦ የወጡ ይመስላል። ሰውነቴን እንዲመጠምጡት ተውኩላቸው።

በዚያው ጊዜ አጐቴና ሴትየዋ ልብሳቸውን ሲያወልቁ በብርድ ልብስ ቀዳዳዎች በኩል አሾልቄ ተመለከትኩ። ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸው። ወዲያው መብራቱ ጠፋ። በአልጋው ላይ ለመተኛት ሰውነታቸውን ሲያመቻቹ ይሰማል። ብዙም ሳይቆይ "ሲጥ...ሲጥ...ሲጥ..." በሚል ድምፅ ተተካ። ከአልጋው የሚመነጭ ድምፅ ነበር። የሲጥ ሲጡ ድምፅ ለአኩል ሰዓት ያህል ሳያቋርጥ ቀጥሎ በመጨረሻ ፀጥ አለ።

መብራቱ እንደገና በራ። አጐቴ እርቃነ ሥጋውን ከአልጋው ወርዶ በወለሉ ላይ ተሰናድቶ በሚጠብቀው ሳህንና ጣሳ ውሃ ብልቱን ታጠበ። ሴትየዋም የእሱን አርአያ ተከተለች። ከዚያም ወደአልጋው ተመልሰው ተኙ። "አይ ፍርጃ ይችን ብክል ሳህን ጥዋት ንክች ባደርግ" አልኩ በሀሳቤ።

አጐቴና ወዳጁ እንቅልፍ እንደወሰዳቸው በቀስታ ላመል ተንቀሳቀስኩ። ሰውነቴንም በጥፍሮቹ አከክ አከክ አደረግሁ። የተመለከትኩት በጣም ስላበሸቀኝ ዕንቅልፍ ነሳኝ።

እንዴት እንቅልፍ እንደወሰደኝ አላውቅም ጧት ግን በሰዓቱ ተነሳሁ። የሽቶ ሽታ በክፍሉ ቢኖርም ሴትየዋ ግን የለችም። ቀስ ብዬ አጐቴን ሳልቀሰቅሰው ከአልጋዬ ወርጄ ሹልክ ብዬ ፊቴን ሳልታጠብ ትምህርት ቤት ለመሄድ ሀሳብ ነበረኝ። ከክፍሉ ልወጣ ስል አጐቴ ከብርድ ልብሱ ውስጥ ብቅ ብሎ "አንድ ሰዓት ሞሸ?" ብሎ ጠየቀ።

"ገና አልሞሸም" አልኩት።

"መታጠቢያዋን አጽድተህ እንድትሄድ!" የዘወትር ትዕዛዙን ሰጠ።

ሳህኗን ከነበረችበት ስፍራ እየተፀየፍኩ አንስቼ ውጭ በማውጣት አጥሩ አጠገብ አሳረፍኳት። ከዚያም እግሬን በመጠቀም በውስጧ የሚገኘውን እጣቢ ደፋሁ። ለካ አክስቴ ታየኝ ነበርና "ስንጥር ውጠሃል ወይስ ሁለት እጆችህን አጥተሃል!" እያለች ተንጣጣችብኝ።

መልስ ሳልሰጣት ሳህኗን ወደቤት ካስገባሁ በኋላ እጆቼን ተለቃልቄ ወደ ትምህርት ቤት በጥድፊያ አመራሁ።

እዚያ ቤት ለመኖር ተባዩንና የሰውን ግልምጫ መቻል አያዳግተኝም። ለሳህኗ ስል ግን በረህ ጥፉ በረህ ጥፉ ያሰኘኛል።

በአንድ ሌሊት ቀን ሌላ ሸገኔ አምጥቶ ያሳድራል። ያቺን ቁሻሻ ሳህን ሳልነካ ትምህርት ቤት ለመሄድ እስኪነጋ ትዕግስቴን አጣሁ። ልክ እንደነጋ ድምፅ ሳላሰማ ተነስቼ ልብሴን ለብሼ በሩን ከፈትኩ። ወጥቼ ከመሄዴ በፊት ዓይኔን ከሳህኗ ላይ ጣል አደረግሁ። ይግረምህ ብሎ ውስጧ ባዶ ሆኖ አገኘሁት። ሸገኔዋ እጣቢውን ደፍታ ሄዳለች። "ባለሙያ ሴት መሆን አለባት" አልኩ በልቤ። የዛንለት ጥዋት አጉቴ ሳይዘኝ አፈተለኩ።

ምሽት ላይ ስንገናኝ "በለሊት እየጋለብክ የምትሄደው የት ነው?" በማለት በቁጣ ጠየቀ።

"ትምህርት ቤት" በማለት መልስ ሰጠሁ።

በአልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጦ እግሩን እንዳጥበው ጠየቀ።

ጣሳ ውሃና ሳህኗን አዘጋጀሁ። ሳህኗን ውሃ ሞላሁና እግሩን ውስጧ ላይ በማሳረፍ እያጠብኩ ሳለ በሳህኗ ውስጥ የሚገኘው ውሃ መጠኑ ስላነሰብኝ ተጨማሪ ውሃ አከልኩ።

"ምን ዝም ብለህ ውሃ ትሞጅራለህ? እግሬን በስርዓቱ በቶሎ አጥበህ ጨርስ" አለኝ አጉቴ።

አሁንም በሳህኗ ውስጥ የሚገኘው የውሃ መጠን ዝቅ አለ። በመጀመሪያ ነገሩ ግራ አጋባኝ በመጨረሻ ግን ተገለጠልኝ ውሃው ከሳህኗ ሾልኮ እየወጣ በሳንቃው ወለል ስንጥቅ ውስጥ ሲገባ ተመለከትኩ።

"ግልግል፣ የሳህኗና የእኔ ግኑኝነት አከተመ" አልኩ በልቤ። ከዚያን ቀን ጀምሮ አጉቴም በውጭ በሚገኘው ቧንቧ መጠቀም ጀመረ። ለአዲስ ዕቃ መግዣ እጁ አይፈታም።

---

## . . . እንዲህ ሆነ

(ከገጽ 22 የዞረ)

በታሪካዊነት የሚታወቀው የዚህ ገዳም መንደድ፣ ቀደም ብሎ በመንግሥት አካላት ጭምር ባለመገለጹ፣ የነደደው በመብረቅ ሳቢያ ነው የሚለውን አባባል ለመቀበል የተቸገሩ የሲኖዶስ ጉባዔ አባላት እንዳሉም ታውቋል። ዕውነተኛነቱን አጣርቶ የሚያቀርብ ኮሚቴ እንዲሰየምም ጠቅላይ ቤተክህነት ተጠይቋል።

በሲኖዶሱ ጉባዔ ላይ በቀረበው ሪፖርት ያልተወሳ ቢሆንም፣ በገዳሙ ግምጃ ቤት የነበሩ ስድስት ሺህ ያህል የብራና መጻሕፍት ተቃጥለዋል የሚሉ ምንጮችም ተገኝተዋል።

## የጦቢያ ጋዜጣ መጽሔት አዘጋጆች ታሰሩ

የጦቢያ ጋዜጣና መጽሔት ዋና አዘጋጅ አቶ ታዬ በላቸውና ምክትል አዘጋጁ አቶ አንተነህ መርዕድ በተከታታይ ቀናት መታሰራቸው ታውቋል። የጦቢያ ጋዜጣና መጽሔት በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታዎች ከማንም የፖለቲካ ኃይል ጋር ሳይወግኑ ነፃ አስተያየትና ዜና በማቅረብ በሀገር ውስጥና በውጭ ጭምር ታዋቂነትን፣ በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነትንና ተነባቢነትን አትርፈዋል። የጦቢያ ጋዜጣና መጽሔት አዘጋጆች በተለያዩ ጊዜያት ፍርድ ቤት ቀርበው ብዙ ሺህ ብር የተቀጡ፣ በየጊዜው የታሰሩና ከ300 ሺህ ብር በላይ ዋስ የጠሩ ቢሆንም አዘጋጆቹ የሀገር ፍቅርንና የሕዝቡን አመኔታ ተላብሰው በመጠናከር ቆመዋል።

## ሶስት ዲፕሎማቶች ኮበለሉ

በስዊድን ኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ የሚሰሩ 3 ከፍተኛ ዲፕሎማቶች ኢህአዲግ የሚያራምደውን አምባገነን አገዛዝ በመቃወም ሰሞኑን ኮበለሉ። ከኮበለሉት ዲፕሎማቶች ውስጥ አቶ አድነው ዋቅጅራ የኤምባሲው ሁለተኛ ሰው ይገኙበታል። ኢህአዲግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ አገዛዙን በመቃወም ከኤርትራ ከግብፅና ከኢጣልያ ጭምር በርካታ ዲፕሎማቶች መኮብለላቸው አይዘነጋም።

A TO Z
ELECTRONICS
& GIFTS
220V/110 Volt Appliances
*Audio-Video-Toys-Cameras-Phones-Stereos-Luggage-*
*Fax Machines-Watches-Gift Items* - Etc.
ኤ ቱ ዚ ኤልክትሮኒክስ
We do Digital Vedeo Coversion
From PAL to NTSC & Vice Versa
ከፖል ሴካም ወደ ኤንቲሲና
ከኤንቲሲ ወደ ፖል ሴካም
ቪዲዮ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መስራት የሚችሉ
ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ
1713 CHURCH ST., SUIT A-1
DECATUR, GA 30033
*Jayendra Patel & Dipa Patel*
Tel/Fax: (404)299-9196

# እምነት ወይስ ክህደት?

(ከእያዩ በልልኝ)

ዘመናችን በርካታ የጥናት፣ የምርምርና የእምነት ዓይነቶች በመጠንና በቁጥር የፈለቁበት ዘመን ነው። ይሁን እንጂ የተገኙት ጥናቶች፣ ምርምሮችና እምነቶች ከታች ወደ ላይ ከቀላል ወደ ከባድ በመጓዝ አዳዲስ ግኝቶችን በመፍጠር የተሻለ ዓለምአቀፋዊ ጠቀሜታን የሚያመጣ ሳይሆን በዓይነት ወደ ጐን እየተፈለፈለ ለመከፋፈል፣ ለመለያየትና ለመናናቅ እንድንበቃ አድርጐናል። የዚህ የዘመኑ የፖለቲካ ሂደትና መዋቅር በአንክሮ ለሚያጠናው ለመሆኑ መንግሥት ምንድነው ሳያሰኘው አይቀርም። በተመሳሳይ መልኩ በእምነት ዘርፍም የሚታየው ጉድ እጅግ አሳሳቢና አጠያያቂ ደረጃ ላይ ደርሷል። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን፣ ክብሩንና ሕልውናውን ያጣው በጉሳ ፖለቲካ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ሰበብ ከመጣው የእምነት ፍልስፍናም ጭምር ነው። ስለሆነም ይህ ትውልድ መዋጋት ያለበት ከፖለቲካው ሂደት መዋቅር ጋር ብቻ ሳይሆን በየመንደሩ እንደ ዶሮ ማጩት ከሚፈለፈለው የእምነት ዘርፎችም ጭምር ነው። ጠያቂና መካሪ ሳያገኝ እንደአመፀኛ አውሎነፋስ ሁሉንም እያቦካ የሚቀልድ ነገር ቢኖር አንዱ የሃይማኖት ጉዳይ ነው። እምነት የነፍስ ጉዳይና የመኖር ሕልውና ያረፈበት ከመሆኑም በላይ የዕለት ተግባራት፣ የሞራል ጥበብና እውቀት ሁሉ የሚፈልቅበት ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ ሳለ የገንዘብ ጥማት ያሰከራቸውና ፈፅሞ ሊረኩ የማይችሉ የበረሃ ዘንዶዎችና ጅቦች መቀለጃና መጫወቻ ሆኗል። ከሁሉም በላይ ገንዘብ ትልቁን ሥፍራ የመያዙ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሰዎቹ ራሳቸውን እንደእግዚአብሔር መቁጠራቸው ነው። ስለዘመኑ የእምነት ጉዳዮችን በሚመለከት ባለፈው የጥቅምት ወር እትም ላይ "እኔም አንቺም አንድ ነን" በሚል ርዕስ ስለአንድ ጴንጤ ቤተክርስቲያን መንደርደሪያ በማድረግ መጠነኛ መንፈሳዊ ግርግር ለመመልከት ተሞክሮ ነበር። ዳሩ ግን ጉዳዩ በአንዴ ተወርቶ የሚያልቅ ነገር ስላልሆነ ሰው ሁኔታውን በአንክሮ ለመመልከት ይችል ዘንድ ትግሉ ይቀጥላል።

በትክክል ዕለቱ ትዝ ባይለኝም በ1995 አጋማሽ አካባቢ ነዋሪነቱ በናይጄሪያ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ እንዲያገለግል በወደ አንድ የጴንጤ ቤተክርስቲያን ይጋበዛል። በዚህም ምክንያት እኔም መንፈሳዊውን ጉባኤ እንድካፈል ጥሪ ይደርሰኝና ወደ ሥፍራው አመራለሁ። አገልግሎቱ የሚካሄደው በተከታታይ ለአምስት ቀናት ነበር። የዝግጅቱ ተባባሪ የሆኑ ስለመንፈሳዊው ጠቀሜታ በደንብ ስላስረዱኝ ሁሉንም ቀናት ለመካፈል በመወሰኔ ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ያለውን ትርኢት በጥሞና ተከታተልኩኝ። የመጀመሪያው ቀን ዝግጅት የተጀመረው ሰይጣንን "በቃ" በሉት የሚል ነበር። ዛሬ ለጠላታችን ልክ ልኩን እንነግረዋለን ተብሎ ቁርጥ ውሳኔ ተደረገ። ከዳር እስከዳር ቤቱ በጩኸት ተሞላ። ሁሉም እጁን እያወጣ በቃ፣ በቃ፣ በቃ ... እያለ ለሰዓታት ጩኸቱን ቀጠለ። ሰይጣን መፈክርን ያውቃል ወይስ አዋጅን ይፈራል? የሚል ጥያቄ ተፈጠረብኝ። ለመሆኑ ክርስትና አልገባኝም ወይስ ይህ ጉድ ምንድነው እያልኩ ግራ ተጋባሁ። ጥዬም ለመውጣት ልቤ ፈልጐ ነበር። ነገር ግን ይህንን ተአምር እስከመጨረሻው መከታተል አለብኝ ብዬ ቁርጥ ውሳኔ አደረኩኝ። በዚህ ዓይነት የዕለቱ አምልኮና የስብከት ፕሮግራም ይጠናቀቅና ወደ ቤት ይኬዳል። ቀናት መፈራረቃቸው አይቀርምና የሁለኛውም የሦስተኛውም ቀኖች ዝግጅት ተካሄዱ። በተለይም የሁለተኛውና የሦስተኛው ቀን መልዕክት በረከትን የመውረስ የሚል ሲሆን በሁለት ዋና አቢይ ክፍል ይከፈላል። የመጀመሪያው ሰማያዊ በረከት ሲሆን ሁለተኛው ምድራዊ በረከት ነበር። ይሁን እንጂ ማንኛውም ዓይነት መልዕክት ከመቅረቡ በፊት የመጀመሪያ የአምልኮ ሥነሥርዓት የሚካሄድ ሲሆን ዓላማው ለዕለቱ የተዘጋጁትን መልዕክቶች ካለምንም ጥርጣሬ በእምነት ለመቀበል የሚያስችል መንፈሳዊ ወኔ ቅስቀሳና የልብ መሞረድ ዝግጅት በደንብ መከናወን ነበረበት። በዚህ ዓይነት ሰማያዊ በረከትን እንዴት እንደምንወርስና በምድር ላይ ደግሞ ባለፀጋ ወይም የታወቀ ሀብታም እንዴት እንደምንሆን ተማርን። ይሁን እንጂ ዋና ምስጢሩ የሰማይ መስኮቶች እና የሰማይ ደጆች መከፈታቸው ሲሆን ለዚህ ክንውን እኛ ምን መሆን እንዳለብን አያይዘን ተማርን። በተለይ እኛ ማድረግ የሚገቡን ሀሳቦች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚመደቡ ሲሆን የመጀመሪያው በሕሊናችን የምናውቃቸውንና የሰማናቸውን ሁሉ አግኝቻለሁ ብሎ በእምነት መናገር መቻል፣ የሁለተኛው ለመንፈሳዊ መሪዎቻችን ሙሉ በሙሉ ታዛዥ መሆን ሲሆን የሦስተኛው ያለንን ነገር በሙሉ መልሰን ለእግዚአብሔር መስጠት ናቸው። ይህንን ቲያትር ስሰማ ትንሽ ነቃ ማለት ጀመርኩኝ። ለመሆኑ የት ነው ያለሁት እንደማለት አልኩኝ። ለመሆኑ የቤተክርስቲያን ዓላማና ተልዕኮ ይህ ነው? ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ይህንን ለመማር ነውን? ድምጼን ከፍ አድርጌ ብሞህ ደስ ባለኝ ነበር። ጥንቆላ ይመስል በአፌ ስለተናገርኩ የሰማይ መስኮት መከፈቱ! ለእኔ የሚያስፈልገኝን እግዚአብሔር ሲሰጠኝ ነው ወይስ የአፌን ቃል እየሰማ የጉዳዮቼ ሥራ አስፈፃሚ መሆኑ ነውን? በእርግጥ ይህ ለመሆኑ እምነትን ወይስ ክህደትን ለመማር ነው እዚህ የተቀመጥኩት እያልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩኝ። ደግሞ መፅሐፍ ቅዱስ "ስለመስጠት" በደንብ የሚያስተምረው እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል በምድር ሁሉ ለሰዎች እንዲደርስና የእግዚአብሔር ምህረትና በረከት በክርስቶስ በኩል በመስቀል ሥራ ያለቀ መሆኑን፣

እንዲሁም በእጦት የሚሰቃዩትን ድሆች ከመርዳት እንጂ በአፀፋ መልክ ተመልሶ ራሴን ሀብታም እንዲያረገኝ በማሰብ አይደለም።

“ዛሬ ማታ ኪሳችሁ ተሞልቶ ወደ ቤት ለመመለስ የምትፈልጉ ሁሉ ከእኔ ጋር ቁርጥ ውሳኔ አድርጉ። በዚህ ዕለት ድህነትን አስወግደን ከዚህ ቤት መውጣት አለብን።” ተባለ። ደግሞ መስኮት ወይም የሰማይ ደጅ የሚከፈተው እንደልባችሁ መሻትና እናንተም ለእግዚአብሔር ምን ያክል እንደምትሰጡ መጠን ነው ተባለ። በጣም የሚገርም ነገር ሆነ። በዚህ ዓይነት ልባችን ሲናወጥ፣ አንዳንዱ ሲያመሰግን፣ ሌላው ግራ ተጋብቶ በትኩረት ሲመለከት የቲያትር ትርኢት ቀጠለ። መቼም ሳስበው አንዳንዱ እንደ እኔ ጥያቄ በጥያቄ ሳይሆን አይቀርም። በመሃከልም የመዝሙር ግብዣና የምስጋና ጊዜ ተደረገ። ይሰማ የነበረው የቋንቋ ዓይነት መጠኑና ዓይነቱ አይታወቅም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በፃፈው መልዕክቱ ላይ እንዲህ ይላል። “የእግዚአብሔር ቤት የሠላም ቤት ነው እንጂ የሁከት ቤት አይደለም” በማለት የቤተክርስቲያንን የአምልኮ ሥርዓት በተለይም በልሳን የሚደረገውን ፀሎት ሲያግድ ይታያል። ይህንንም ለምን እንዳላስተዋሉ አይገባኝም። ነገር ግን የቁሳቁስ ትርፍ የሚገኝበትን ትርክምርኪ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህንንም ለሚያምኑና ሀብታም ወይም ድሃ የግል ምርጫ መሆኑ ሲነገር አንዳንዱ ሲፈነድቅ ይታያል። የዚያኑ ዕለት ማታ ብር በብር ሆኖ ወደቤቱ ሲመለስ። ጉድ ነው በደንብ የጥንቆላ ሥራ መሰለኝ። ሌላው ተአምር የታየው የመባ አሰባሰብ ሁኔታ ነበር። አዲስ መንገድ እንጀምራለን ተባለ። እግዚአብሔር ለማኝ አይደለምና በልግሥና የምንሰጠውን ሁሉ ይዘን ወደፊት ለፊት እያሸበሸብን መሥጠት አለብን የሚል መመሪያ ተሰጠን። ትልቁ ጉድ ግን ወደፊት ሄዶ የመስጠት ያለመስጠት ብቻ አይደለም። ነገር ግን መጠነኛ ገንዘብ ወይም ምንም ይዘው ላልመጡ ሰዎች የተሰጠው መመሪያ ነው በጣም ያሳቀኝ። ይኸውም እንዲህ ተባለ “ዛሬ ትንሽ ገንዘብ ወይም በደንብ ሳታስቡበት የመጣችሁ ሁሉ ስማችሁን ፃፉና ሌላ ጊዜ ማምጣት የምትችሉትን ፅፋችሁ አምጡ” የሚል ትዕዛዝ ሲሰጥ አንዳንዱ እስኪርቢቶ አንዳንዱ ወረቀት መዋዋስ ጀመረ። በሥፍራው ሆኖ ለሚመለከት ጉዳዩ ቀላል አይደለም። የስንቱን የዋህ ሕዝብ ሕልውና ሙጥጥ በማድረግ የሰውን ላብና ደም የሚመጡ መዥገሮች አሉ አልኩኝ። እርግጠኛ ነኝ አንድ ቀን ይጠየቃሉ።

— ለመሆኑ እግዚአብሔር ይሰጥ ዘንድ ጉቦ ፈላጊ ከሆነ እንደሰው ሆኗል ማለት ነው?

— እነ ሐዋርያው ጳውሎስና ሌሎችም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ይህ ዘዴ ጠፍቷቸው ነዋ ድንኳን እየሰፉ የራሳቸውን ጥቅምና ሕይወት እየሰዉ ወንጌልን ያሰራጩ?

— ክርስትና አይመስለኝም፤ ነገር ግን ሆኖ ከሆነ ታዲያ የክርስቶስን ሕይወት ለምን አላስተዋሉም?

— የእግዚአብሔር ፍቅር ጥልቀቱና ስፋቱ፣ የኃይሉም ሙላትና ብዛት፣ የክብሩም ግርማና ሞገስ በሰው አእምሮ የማይገመት ሆኖ ሳለ እንዴት ከምድራዊ ቁሳቁስ ጋር ተቀላቀለ?

መቼም የወንጀሉንና የሚሠራውን ሥራ በትክክል ዘርዝሮ ለማስቀመጥ ጊዜም ወረቀትም አይበቃም። ሌላው በጣም አሳሳቢ ሆኖ ያገኘሁት አንድ ተአምር አለ። ይኸውም የትንቢት ቃል ይመስል በመንፈሳዊው መሪ በኩል ብዙ የሚነገሩ ነገሮች ነበሩ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሳለን አንድ ነገር ሆነ። ስሟን በትክክል አላወኩም ነገር ግን የቤተክርስቲያኑ አለቃ ነች የተባለች ሴት ነበረች። ልክ የትንቢት ቃል ነው ተብሎ ሲነገር መንቀጥቀጥ ጀመረች። ወዲያው ወንበር ሥር ወደቀችና ቀሚሷ ተገልብጦ አካሏ እስኪገላለጥ ሆነች። ከዚያም ብድግ አለችና በእግርና በእጇ እየተንከረባበተች ማዳነቅ ሳይሆን በትክክል የጅብን ጩኸት የሚመስል ድምፅ እየጮኸች ወደ ሌላኛው ረድፍ ሄዳ ተደፋች። ክርስትና ይሉታል ጉድ ነው። ለመሆኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራው ምንድነው? ወደ እውነት ሁሉ ይመራል። ያስተምራል። የክርስቶስን ሥራ ይገልፃል። ታዲያ ይህ መንፈስ ከወዴት መጣ? ለመሆኑ ሕዝቡስ ለምን ሁኔታውን በቃሉ አይመራመርም? ሁሉም ሲጠፋ ለምን ዝም ተባለ? ጥፋት! የጠወለገ፣ ሕይወት የሌለው የቁሳቁስ ረሃብተኛ። ከሁሉም በላይ ተስፋ ያስቆረጠኝ ሌላ አቢይ ጉድ ተከናወነ። ይኸውም ስብከት ካለቀ በኋላ ሌላ ቲያትር ተጀመረ። ይህ ከናይጄሪያ የመጣው ሰው ይነሳና የቤተክርስቲያኑን መንፈሳዊ መሪ የነበሩትን ወደ ጉባኤ ፊት ይጋብዛቸዋል። እንደመቆጣትና እንደሀዘንተኛ በመምሰል፤ ለመሆኑ ይህንን ሰው በሚገባ ታውቁታላችሁን? ይህ ሰው እኮ ነቢይ ነው። ለእናንተ ፈፅሞ አይገባም ሲል ቅሬታውን ዘረጋገፈው። አሁንስ በጣም አዘንኩኝ።

ምንስ ቢሆን ሥጋ ለባሽ ቀርቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጐ ደሙን ያፈሰሰለት ጉባኤ እኮ ነው ይህ ሕዝብ። ደግሞስ ሰው ቢያስተምር የሰማዩን ምስጢራት ሁሉ ቢገልጥ አንዳች ነገር ከራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ተሰጥቶት ነውና ሰው የሚመካበትና የሚዝናናበት ምን ሊኖረው ይችላል? ይህ የክብርናን የሙገሳ ጥማት በእነ አዳምና ሔዋን ውስጥ የተጠነሰሰው ያ እንደእግዚአብሔር ለመሆን በመመኘት የዛፉን ፍሬ ለመብላት የተዳፈሩትን የሚመስል ጉዳይ ነው። ሸክላ ተሠርቶ ለጠቃሚነት ቢውል ክብርና ምስጋናው ለሸክላ ሠሪው እንጂ ለሸክላው መሆን የለበትም።

በየዘመናት የነበሩ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ታላቅነታቸው በዝቅተኝነት ውስጥ እንጂ ራሳቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ አይደለም። ከኢዮብ ታሪክ እንደምንማረው፤ “ድሮስ ጆሮዬ ሰምታ ነበር፣ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ራሴን እንቃለሁ። እጄንም በአፌ ላይ አደርጋለሁ” አለ። ምን ዓይነት ጉልምስና፣ ምን ዓይነት የመረዳት ሙላት ውስጥ ሆኖ ነው ቃልን ልተነፍስ አይገባኝምና አፌ ይከደን የሚለው? የዚህን ዓይነት መረዳት ያላቸው የሰውን ከንቱነት የተረዱና

የእግዚአብሔርን ታላቅነት ያዩ ብቻ ፈቃዱንም ሊያስተምሩ ይችላሉ። ደግሞስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ፀሎት በኋላ ጌታ የተናገረውን ማስተዋል የምንችለው ሌላ ሃሳብ አለ። ጳውሎስ ወደ ሦስተኛ ሰማይ በመንፈስ ተነጥቆ ከተመለሰ በኋላ ለበለጠ መገለጥና ለበለጠ ኃይል ሲፀልይ የተሰጠው መልስ ሌላ ነበር። "ኃይሌ በድካም ይገለፃልና ፀጋዬ ብቻ ይበቃሃል" የሚል መልስ ነበር የተሰጠው። ሰው እግዚአብሔርን ምን እንደሆነ በመጠኑ ቢያውቅ ራሱን መናቅ ይጀምራል። የሰው ኃያልነት ኃያል መሆን አለመቻሉን በማወቅ ውስጥ ነው። የሰው ብርታት ብርቱ መሆን እንደማይችል ተረድቶ ወደ ብቸኛና ብርቱ ወደሆነው ወደ እግዚያብሔር በመጠጋት ነው። እንኳንስ የመንፈሳዊ ጥበብ ያላቸው ቀርቶ በምድራዊ ጥበብም ሰፋ ያለ አእምሮ ያላቸው በመጨረሻቸው ሰው ምንም እንዳልሆነ በመረዳት ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ። ለምሳሌ ፓስካል (PASCAL) የተባለው ፈላስፋ ስለ ሰው ታላቅነት ሲናገር "<u>የራስን ከንቱነት መረዳት ነው</u>" ይላል። "Man's greatness lies in his capacity to recognize his wretchedness." እንግዲህ ዛሬ ጣታቸውን ወደ ራሳቸው ያደረጉ በግል ዝናና ክብር የቆሙ የየትኛው መንፈስ አገልጋዮች እንደሆኑ ለመረዳት አያስቸግርም።

ክርስትና ራስን በመካድ ከእግዚአብሔር፣ ለእግዚአብሔር፣ በእግዚአብሔር በሆነው ላይ ተስፋ መጣል ማለት ነው። በራሳችን ሀሳብ፣ በአዋጅና በስብሰባ ግርግር የሚሆን ጉዳይ አይደለም። ክርስትና ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ሕይወት ነው። ክርስትና ብልጣብልጥ ሳይሆን አዋቂ ያደርጋል። ክርስትና አስተዋይ ያደርጋል። ክርስትና ዛሬ ሲጀራንና ቢራን በመተው የምንፈጥረውና የምንሰራው ሳይሆን በክርስቶስ ተሠርቶ ያለቀውን በእምነት መቀበል ነው። ክርስትና ድካምን ቆጥሮ በየቀኑ በመሻሻል ለጥረት ዋጋ የምናገኝ ሳይሆን ምንም ዓይነት ጥረታችን የትም እንደማያደርሰን መረዳት ነው። ክርስትና ማለት ጥበብና እውቀት ማለት ነው። ክርስትና ከዕዳ ነፃ የወጣ በነፃነት የመኖር ሕይወት ማለት ነው። "እውነት ነፃ ያወጣል።" ክርስትና በስሜት፣ በህልምና በምክንያት የሚታይ ወይም የሚመዘን ሳይሆን ብናውቅም ባናውቀውም እውነት ሆኖ የሚኖር ማለት ነው። ክርስትና መንገዱና ምንነቱ፡ ቢገባኝም ባይገባኝም ወደ መንገዱ የሚወስደኝ ታማኝና መሃሪ አለኝ ብሎ ነፃና ከፍርሃት ውጪ በደስታ መኖር ነው። አይ ከዚህ በቀር ሌላ መንገድ አላውቅምና ስለዚህ አንተ የምታወራው አይጠቅመኝም በመባባል የፈጠርናቸው መከፋፈል የከንቱነታችን የሞት ሞታችን እንጂ የማወቃችን ምልክቶች አይደሉም። እግዚአብሔር አንድ ነው፣ ክርስቶስም አንድ ነው፣ ቤተክርስቲያንም አንድ ነው፣ ሰውም አንድ ነው። አንዱ ከአንዱ የማይሻል ደካማ ነው።

ዋና ጉዳይ እግዚአብሔር ታላቅ ነው። እሱን ማወቅ አይቻልም። እሱ ለራሱ የመረጣቸውን ያድናል። የፈለገውን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው። ስለእግዚአብሔር ማንነት ማንም ሊያውቅ አይችልም ራሱ ካልገለጠለት በቀር። ዛሬ ስለ እግዚአብሔር እናውቃለንና እናስተምራችሁ በማለት እንደቀለዱ ጓደኞቻቸው ያደረጉና በሻንጣቸው ውስጥ አስቀምጠው በሳንቲም ስሙን ለመቸርቸር ለሚፈልጉ ወዮላቸው። መልዕክት ከእግዚአብሔር ተሰጠኝ እያሉ ለሆዳቸው የሚኖሩ የራሳቸውን ዕዳ ያከማቻሉና። በምድር ላይ ሊታዘንላቸው ከሚገባቸው አንዱ ናቸውና ንሥኃ እንዲገቡ ቢመከሩ በተሻለ ነበር። የሥነፅሑፍም ዓላማ እነዚህን ጅቦች ለመጉዳት ሳይሆን ከክፉ ሀሳባቸው እንዲመለሱና የፈዘዘውም አጨብጫቢ ሁሉ ረጋ እንዲል ለማድረግ ነው። በዚህ መንገድ የትም አይደረስምና። ዳሩ ግን እኔስ ፀሐፊው ማን ነኝ ለማለት ያልቻልኩ አይምሰላችሁ። የሰውን ስንጥር ስቆፍር የራሴም ግንድ እንዳያደናቅፈኝ የምፈራ ሰው ነኝ። ነገር ግን ስንጥሬም ሆነ የተሸከምኩት ግንድ ካለ ፈፅሞውኑ ምንም ላደርገው አልችልም። አለኝታዬና ብርታቴም ድካሜን በመረዳት ሊታመን በሚችለው በእግዚአብሔር ምህረት አምናለሁና ብርቱዎች ነን ከሚሉት እሻላለሁ። የዋሁን ሕዝብ ይዘው የሚጠፉትን ለመታገል፣ ለመመለስና ለመምከር የማይቋረጥ ዓላማ አለኝ። ከሁሉም በላይ ለመተው የምፈልገው ከእኔም ሆነ ከማንም አገልጋይ ይልቅ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይጠነቀቃል። ነገር ግን በእውነት ደግሜ እላለሁ ይህ የማወራው ቤተክርስቲያን ስሙ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አለመሆኑን ምስክር ነኝ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!!

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በጠየቁን መሠረት በብዕር ስማቸው በእያዩ ቢልልኝ ነው ያወጣነው። የሚኖሩት በጆርጂያ ነው። በዚህም ሆነ ቀደም ሲል በአወጡዋቸው ጽሑፎቻቸው የዘገቡት ከራሳቸው ልምድና ገጠመኝ በመመርኮዝ መሆኑን ገልጸዋል። እኔ ያልኩትን ልክ አይደለም የሚል ከአለ በዚሁ መድረክ ልክ ያልሆነውን ሊጽፍልኝ ይችላል ብለዋል።




Open 7:30 pm
Show Time
9:30 pm
Close 2:00 am; Sat. 3:00 am

LIVE REGGAE
AND
WORLD MUSIC
7 Nights a Week

Experience
the music
the groove
the culture
the fun!!

# በኮምፒውተር
# የአማርኛና የእንግሊዝኛ ሥራዎች

**መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣ ወይም የተለያዩ የአማርኛ ጽሑፎችን
በኮምፒውተር ለማሠራት ለምትፈልጉ ሁሉ!!**

ርካሽ በሆነ ዋጋ ከጥራት ጋር ማንኛውም ዓይነት ጽሑፍ
በአስቸኳይ ለማሠራት የምትፈልጉ ሁሉ
በስልክ ቁጥር (404) 508–4657 ደውለው ገነትን ያነጋግሩ።
ጽሑፎችዎንም በፋክስ ቁጥር (404) 508–2447 መላክ ይችላሉ።
ማስታወቂያዎች፣ የትርጉም ሥራዎች፣ የመጣጥፍ ረቂቆች፣
የጥሪ ካርዶች በፈለጉት ዲዛይን እንሠራለን።
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችንም በማዘጋጀት
በአስቸኳይ በኢ ሜይል ለመላክ እንችላለን። ደውሉልን።

# አዳምና ሔዋን

አዳምና ሔዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግኑኝነት ላይ ነው። የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ። በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተዋጽኦችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## "ዕጣዬ"

### ከአብረኸት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብረኸት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነውም ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

### ክፍል 15

አዲስ ከተከራየሁት ቤት ገብቼ ባለኝ አቅም በጣም አስፈላጊ የሆኑ የቤት ዕቃዎችን በርካሽ ገዝቼ አሟላሁ። ከመጣሁ ያፈራሁዋቸው ጓደኞቼም አንዳንድ ዕቃ በመግዛት ረዱኝ። ሰይፍዬም ሁሉ ነገር ተሳክቶለት በተከራየሁት ቤት በገባሁ በአስረኛው ቀን መጣ። በዚያን ወቅት የነበርኩበትን ሁኔታ ለመረዳት የሚያዳግታችሁ አይመስለኝም። ከሁለት ዓመት በላይ የተለየሁት በጣም የምወደው ሰይፍዬ ሲመጣ የተሰማኝን ደስታ ልገልፅላችሁ ቃላት ያጥረኛል። ሊመጣ ሁለት ቀን ሲቀረው ጀምሮ እንቅልፍ በዓይኔ አልዞረም። በመጣበትም ቀን ሁለት ሰዓት ቀደም አድርጌ ከተዋወቅሁዋቸው ጓደኞቼ ሁለቱን በአጃቢነት ይዤ አይሮፕላን ማረፊያ ደረስኩ። ከሰይፉም ጋር በመጀመሪያ ስንገናኝ የነበረውን ሁኔታ ለመግለፅ ያዳግተኛል። ሁለታችንም በእንባ ተነክረን ደስታ አይሉት ምን ተቃቅፈን ስንሳሳምና ስንጨጨህ ከእኔ ጋር ሊቀበሉት የሄዱት ጓደኞቼ በሉ እንሂድ እንሂድ ባይሉን ኖሮ መሄድም የምንችል አይመስልም ነበር።

በመንገድ ላይ ወደ ቤት እየሄድን እያለን ምንም ማውራት አልቻልንም። ዝም ብለን እየተያየን እንባ ባዘሉ ዓይኖቻችን ሆጋግ ሁለታችንም ያለፍንበትንና ተለያይተን የነበረንበትን ወቅት ነበር የምናስታውሰው። ቃላት ከአፋችን ወጥቶ መናገር ባንችልም በመተያየት ብዙ ተነጋግረናል። እቤት ስንደርስ እንደተቀቀፍን ስንገባ የእሱን ዕቃ ተሸክመው የገቡት ጓደኞቼ ነበሩ።

እንግዲህ ይኸውላችሁ ከብዙ ድካም በኋላ ከምወደው ሰይፍዬ ጋር ተገናኘሁ እላችኋለሁ። በቅርብ የተዋወቁኝ ሁሉ እየመጡ የደስታዬ ተካፋይ ሆኑ። እህቴ ትብለፅ የመጣችው በሳምንቱ ነበር። እሱን "እንኳን ደህና መጣህ" ብላ ጥቂት ደቂቃዎች ቆይታ ሄደች። አሁን እንደሁ እሱ መጥቷል። እኔም ምን ያህል እንደምወደው ታውቃለች። ምን እንዲህ እንዳስጨከናት ሊገባኝ አልቻለም። ለሰይፉ ኃላፊነት ወስደው ያመጡልኝ የምሠራላቸው ቤተሰቦች እቤታቸው ልዩ ግብዣ አድርገው ጋበዙን። ከሰይፉም ጋር ተዋወቁ። የሰይፉ የሥራ ፈቃድ ወረቀት እስከሚጠናቀቅና አገሩን እስኪላመድ ድረስ ችግር እንዳይገጥመው ሊረዱት እንደሚችሉ ቃል ገቡልን። እኔም ደህና ሥራ ስለነበረኝ እሱ ሥራ እስኪያገኝ ለሁለታችን መሆን የሚያቅተኝ አልነበርኩም።

ሰይፉ እኔ ከመጣሁ በኋላ ሱዳን ውስጥ የደረሰበትን ችግር ሲነግረኝ በጣም አዘንኩ። እሱ ዕድሉ ተሳክቶለት እኔም ጭምር እዚህ ብንመጣም ከፍ ባለ ችግር ላይ ያሉ ብዙ ወገኖቻችን እዛው ሱዳን ቀርተዋል። በአገር ሰላም ተመስርቶ፣ ያለው ውጥንቅጥ ሁኔታ ተወግዶ ወደ አገሬ እመለስና ሰው እሆናለሁ በሚል ተስፋ የሚኖረውና የአገሬ ጉዳይ እንግዲህ አክትሞለታል ወደሰለጠኑት አገር ሄጄ ራሴን አሻሽዬ እኖራለሁ በሚል ተስፋ ማመልከቻውን ለተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ክፍል አግብቶ የሚጠባበቀው ሕዝብ ብዙ እንደሆነ እኔም እዛ እያለሁ ያየሁት ነገር ነበር። ይህ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መጥቶ የአገሬው ሰው (ሱዳናዊው) ከመሰላቸት ደረጃ ደርሶ ኢትዮጵያዊ ባየ ቁጥር ዓይንህ ላፈር እያለው መሆኑን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ በኛው ሰው መሐል እየጐላ የመጣውን የመለያየትና የመጣላት መንፈስ መኖሩን ሰይፉ ሲነግረኝ በጣም አዘንኩኝ።

እንግዲህ ይኸውላችሁ በጣም የምወደውንና ለእኔ ሲል ስንት ነገር የደረሰበትን፣ እናቱንና አገሩን ጥሎ የወጣውን ፍቅረኛዬን ከአለሁበት ድረስ ካመጣልኝ በኋላ ደስተኛ ሆንኩ። ኑሮአችንንም ጀመርን። ሰይፉ

አገር እስኪላመድ ያው እንደተለመደው ቤት ውስጥ ከቲቪ ጋር ዘግቼበት ለጥቂት ጊዜያት እንደተቀመጠ በመጣ በሶስተኛው ወር ገደማ አንድ መደብር ውስጥ ሥራ ተገኘለት። የቋንቋ ነገር እኔ ፊት ስመጣ ከነበርኩበት እሱ ሻል ያለ በመሆኑ ብዙም ችግር ባይገጥመውም ባለን ትርፍ ጊዜ ሁለታችንም ቋንቋችንን ለማሻሻል እንድንችል በአንድ የሃይማኖት በጐ አድራጐት ድርጅት ከሚሰጥ የቋንቋ ት/ቤት ገባን። ሁለታችንም እየሠራን፣ በትርፍ ጊዜያችንም ቋንቋ እየተማርን ሁለተኛውን የስደት ኑሮአችንን መግፋት ጀመርን።

## ሰይፉ ከመጣ ከአንድ ዓመት በኋላ

አንድ ዓመት የፍቅር፣ የሰላም፣ የመተሳሰብና የመረዳዳት መንፈስ ያለበት ኑሮ እንዳሳለፍን በኢትዮጵያ ብዙ ነገሮች መለዋወጥ ጀመሩ። በጄኔራሎች የተካሄደው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍ፣ በአሰብና በተለይም በምፅዋ የኢፒኤልኤፍ ማየል፣ በአጠቃላይ አገሪቷ ከፍ ያለ ችግር እየወደቀባት መጣ። ይህንንም በቅርብ እንከታተል ስለነበር ለአገር ለወገን ተቆርቋሪ በመሆን አልፎ አልፎ በኢትዮጵያውያን በሚዘጋጁ ስብሰባዎች ላይ እንገኝ ጀመር። ሰይፉም ሆነ እኔ ያፈራናቸው ጓደኞች ከተለያዩ አካባቢዎች ይሁኑ እንጂ በእኔ ና በሰይፉ መካከል ያለውን የፍቅር ግኑኙነት ልክ እንደ እህቴና የእህቴ ጓደኞች በከፍተኛ ጥላቻ ይመለከቱት ጀመር። እኔን በሚያገኙበት ቦታ ሁሉ ሰይፉን እያጥላሉ፣ እኔንም እያሸቀጡ ያስቸግሩኝ ጀመር።

በዚህ ላይ በአገር ቤት ነገሮች እየከረሩ ሄደው የምፅዋ ወደብ በኢፒኤልኤፍ መያዙ እንደተሰማ ወጪ አገር ባለን ኢትዮጵያውያኖች መካከል ከባድ አለመግባባትና መቃቃር ተፈጠረ። ኤርትራውያን ትልቅ ፌስታ እያደረጉ ድግስ በድግስ፣ ዘፈን በዘፈን መሆን ጀመሩ። በአንፃሩ ደግሞ በሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ብስጭትና ሀዘን ይታይ ጀመር። እህቴ አንድ ትልቅ ፓርቲ አዘጋጀች። ምን እንደታያት እንጃ በዚህ ፓርቲ ላይ እንድገኝ ጋበዘችኝ። የፓርቲው ዝግጅት ምክንያቱ ግልፅ ነበር። የእኔ ደግሞ በዚህ ፓርቲ ላይ መገኘት በመካሄድ ላይ ያለውን የአገር መገንጠል የምደግፍ ስለሚያስመስልብኝ ላለመሄድ ወሰንኩ። እህቴ ባደረገችው ፓርቲ ላይ አለመገኘቴ ደግሞ ባለንበት ከተማ በሚኖሩ ብዙ ኤርትራውያን ዘንድ የከባድ ጥላቻ ዒላማ ለመሆን በቃሁ። በአንፃሩ ደግሞ እህቴ ትብለፅ የምፅዋ ከተማ መያዝና የኢፒኤልኤፍ ድል ዋና

አቀንቃኝ በመሆኗ ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የጥላቻ ዒላማ ሆነች። ከተማው በአብዛኛው ስለእሷ ማውራት ጀመረ። ከእሷም ጋር ሆነው ስብሰባዎችን፣ ሰልፎችን እንዲሁም ፓርቲዎችን የሚያደርጉ የኤርትራ ልጆች ሁሉ ቀደም ሲል ከነበራቸው ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸው ጋር መለያየትና በጠላት ዓይን መተያየት ጀመሩ። እቤቴ ስልክ እየተደወለ ስድብና ማስጠንቀቂያ ይወርድብኝ ጀመር። ይህ ሁኔታ በእኔና በእህቴ መሐል ቀደም ሲል ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት የበለጠ እያካረረው መጣ። እህቴም ራሷ እየደወለች ክፉ ነገሮች ትናገረኝ ጀመር።

አንድ ቅዳሜ ምሽት ነው ትዝ ይለኛል። እኔም ሰይፉም ከሥራ ገብተን ቁጭ ብለን ቲቪ እናያለን። ስልኩ ይጮሃል። ከአጠገቡ የነበረው ሰይፉ ያነሳዋል።

"አሎ"፣ "አቤት!" ... ይልና ሰይፉ ፀጥ ይላል። ፀጥታው ገርሞኝ ዞር ብዬ ሳየው

"እና ምን ላድርግ ታዲያ?" ይላል ሰይፉ በስልኩ ለሚናገረው መልስ በመስጠት ዓይነት መልክ።

"የለችም!" ይላል በቁጣ፣

በመጨረሻ "ራስህ ሎቅማፅ" ብሎ ጆሮው ላይ ይዘጋበታል።

"ለምን ለእኔ አትሰጠኝም ነበር፣ ልክ ልኩን እነግረው ነበር" አልኩት።

"እኔን መስደቡ አንሶ ደግሞ አንቺንም ሊጨምር እሷን አቅርባት አይለኝ መሰለሽ" አለ ሰይፉ።

"አውቄአቸዋለሁ እነማን እንደሆኑ። ሰሞኑን እኮ እየደወሉ እንዲሁ ሲያስቸግሩኝ ነበር" አልኩት።

"ምነው አልነገርሽኝም?" አለ ሰይፉ

"ምን ይሠራል ባክህ፣ ተዋቸው" አልኩት፣ ነገሩን ችላ እንዲለው

"ምን አድርጊ ነው የሚሉሽ?" አለኝ ሰይፉ

"እኔ ምን አውቃለሁ። እንደነሱ ለምን አልፈነጠዝኩም፣ ለምን ገንዘብ አላዋጣሁም፣ ... ስንቱን ልንገርህ" አልኩት።

"እነማን እንደሆኑ ለምን አትነግሪኝም?" አለ ድምፁን ከረር አድርጎ

"ምን ያደርግልሃል? በቃ ተዋቸው" አልኩት። ነገሩን ማካረር አልፈለግሁም።

"እንደዚህ በየጊዜው የሚያስቸግሩ ከሆነ እኮ ባናግራቸው ጥሩ ነው። ሰው ቤት ደውለው እንዲህ ማለት የሚገባቸው አይመስለኝ" አለኝ።

"አታውቃቸውም፤ በዚህ ላይ ደግሞ ምንም በትነግራቸው የሚገባቸው ዓይነት አይደሉም። ቢሆንስ ምን ልትላቸው ነው?" አልኩት።

"አአይ! ማለቴ የማያውቁት ሰው ቤት እየደወሉ መሳደብና ማስፈራራት ወንጀል መሆኑን ማወቅ አለባቸው፤ አይመስልሽም?" አለኝ።

"አጥተውት ነው ብለህ ነው! ጥጋብና ንቀት እንጂ። ባክህ በዚህ ዓይነት እንካሰላንቲያ ጊዜያችንን ማጥፋት ጥሩ አይመስለኝም። ቢቀር ይሻላል ሰይፍዬ" አልኩት።

"እሺ እንዳልሽ" አለኝ።

ሰይፍዬን እንድወደው የሚያደርገኝ አንዱ ባህርይው ይኸው እኔ የምለውን መስማት መቻሉ ጭምር ነበር። (በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

# ከአበው

## ታሪክና ምሳሌዎች

ከመጋቤ አእላፍ መክብብ አጥናው
(ከሳንዲያጎ)

### በታማኝነት ለአደራ የመብቃት ባህላችን ተረሣ ይሆን?

አንድ የከተማ ነዋሪ ከአባቱ በውርስ ያገኛት ጊደር ነበረችው። የከተማው ኑሮ ለእንስሳት ምቹ ባለመሆኑ አገር ቤት ወስዶ ከአንድ የቅርብ ዘመዱ ቤት በአደራ ጠባቂነት ያኖራታል። ከአንድ ዓመት በኋላ ጥሩ መልክ ያለው ጥጃ መውለዱዋን ይገልጥና አደራ ጠባቂው ወተት አልቦ ይልክለታል። ባለቤቱም ራሱ ሄዶ የደስ ደስ ያለው እምቦሳ ስለወለደችለት ከመጠን በላይ ሐሴት በማድረግ ለአደራ ጠባቂው ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ ሰጠው፦

‹‹ወንድሜ ሆይ ይህ እንቦሳ ቀለሙ ያማረ(የተዋበ) ስለሆነ ወደፊት ለአውራነት የሚያገለግል ይመስለኛል። ስለዚህ በጥሩ ሁኔታ ያድግልኝ ዘንድ ስለምፈልግ ወተቱን ልሻማው አልፈልግም። ራሱ እንደልቡ እየጠባ ይደግልኝ። ለአንተም ውለታህን እከፍላለሁ።›› ብሎ ልዩ ስጦታ አድርጎለት ይመለሳል።

አደራ ጠባቂው ግን እምነት አጉዳይ በመሆን የዚያችን ጊደር ወተት እየመዠረገ በማለብ ለራሱ ሲጠጣ ለጥጃው ጠብታ ወተት እንኳ ሊተውለት አልፈቀደም። ያም እምቦሳ ወተትም ሆነ ሌላ ተመጣጣኝ ምግብ በማጣቱ ከስቶ መንምኖ ይቆይና ከጥቂት ወራት በኋላ ባለቤቱ ለጉብኝት ሲመጣ ሞቶ ቆዳው ሲገፈፍ ያገኘዋል። በጣም አዝኖ ወንድም የሞተበት ያህል ምርር ብሎ ያለቅሳል። የጥጃው ቆዳ ሲገፈፍ ሌላው ሰውነቱ ሁሉ ደርቆ ጆሮው ላይ ብቻ ትንሽ ስብ (ስባት) ወይም ሞማ ይገኛል። ታዲያ ይህን ያህል ከስቶ የመነመነ ጥጃ በጆሮው ላይ እንዴት ስብ ለማስገኘት ቻለ? ተብሎ ሲጠየቅ የተገኘው መልስ የእንስሳው ባለቤት ለአደራ ጠባቂው «ወተቱን ለብቻው እየጠባ ይደግልኝ» ሲል የሰጠውን ተስፋ ስለሰማበት ነው የሚል ነበር ይባላል።

አዎ እንደዚህ ያለውን የተስፋ ቃል የሚሰሙ ጆሮዎች ብዙ ናቸው። ነገር ግን የማይፈጸም ተስፋ ልብን ያሳዝናል ይለናል የታላቁ መጽሐፍ ቃል።

በተለይ በሦስተኛው ዓለም የሚገኙ መሪዎች የሥልጣን እርካብ ለመርገጥ በዕጩነት ለመመረጥ በሚቀርቡበት ጊዜ የማይሰጡት የተስፋ ቃል የለም። መና ከደመና፣ ውኃ ከአለት ደንጊያ አፍልቀው መመገብ እንደሚችሉ ቃል ይገባሉ። የሥልጣን ኮርቻቸው ከተደላደለ በኋላ ግን የገቡትን ቃልና የሰጡትን ተስፋ ይረሱታል። ከዚህም የተነሣ የሚመሩት ሕዝብ ለረኃብና ለእርዛት ተጋልጦ፣ መጠለያ አጥቶ በሕይወትና በሞት መካከል ሲንገላታ መኖሩ ደስ የሚላቸው ሁሉ አደራ በላዎች መሆናቸውን ከዚህ በላይ የተነገረው አጭር ታሪክና ምሳሌ ይጠቁመናል።

ለማዳበሪያ የሚሆንና ከዚሁ ጋር አብሮ የሚጓዝ ሌላ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ። በጥንት ግሪክ ከተማ ለፓርላማ (ብሔራዊ ሸንጐ) ምርጫ ዕጩ ሆኖ የቀረበ አንድ ሰው «እኔን ብትመርጡኝ የሀገሪቱን ማመላለሻ መሥመር ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በመዘርጋት አውራ ጐዳናዎች፣ የባቡር ሐዲድና ድልድዮች እንዲሠሩ አደርጋለሁ።» እያለ በድምፅ ማጉሊያ ሲናገር የሰሙት ሰዎች ገርሟቸው በሀገራችን ወንዞች የሉም። ታዲያ ድልድይ መሥራት ለምን ያስፈልጋል? ቢሉት ዕጩ ተመራጩ "ወንዝም እንሠራለን" አለ እየተባለ መተረቻ ሆኖ ቀርቶአል።

እንዲያው በአጭሩ እንደምንም ብላችሁ ብትመርጡን በችግር ላይ ችግር የመፍጠር ችሎታችን ከፍ ያለ ነው ለማለት ካልሆነ በስተቀር ወንዝም እንፈጥራለን ማለትን ምን አመጣው?

እንግዲህ ሁሉንም ከዚህ አንፃር በትዝብት ስንመለከተው ከብዙ የአፍሪቃ አህጉር የሚጠበቀው ጥሩ ማኅበራዊም ሆነ መንፈሳዊ የአመራር ተስፋ እንደዚህ እየጨለመ መምጣቱ በብርቱ የሚያሳዝን ነው። ታዲያ በእኛስ በኢትዮጵያውያኖች ዘንድ በኃላፊነት ተግባር ለአደራ ጠባቂነት የመብቃት ባህላችን እየተረሣ መምጣቱ አደገኛ አዝማሚያ አይመስላችሁምን? □

# እንዳው ለምክር ያህል!!

## «አልፎ አልፎ ጐተራ ባለበት አይጦች አይጠፉም»

(ከዲቡ ወልዴ)

በዚህ ባለንበት አገር አሜሪካ፣ አብዛኛው ሕዝብ ነጮች ናቸው። የአይጦቹ ቆዳ ቀለማቸው ግን ጠደይሞች ናቸው። ለብዙ ጊዜ የአይጦቹ ቀለም ለምን እንደ ሕዝቡ ነጭ አልሆነም እያልኩ በጣም እገረማለሁ። ከልዩ ልዩ አገሮች እንደእኛ ተሰደው የመጡትን ሰዎች ስመለከት፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እያደጉ ሲሄዱ አይቻለሁ። በሕብረት ያስቀመጡት ሐብት እየተባዛ፤ ሕብረተሰባቸውም እያደገ ሔዷል። አይጦችም ጐተራቸውን ደፍረው አይነኩም። እነኝህ ጠያይም አይጦች እኛን በልዩ ልዩ ቦታዎች አድቀው አስቀርተውናል።

የትኛውም ማሕበር ይሁን ጐተራ ካለበት ባፍንጫቸው እያነፈነፉ ይደርሱበትና ባዶ ያስቀሩታል። ስብሰባው ስፖርትን የሚለከት ከሆነ እስፖርተኛ ሆነው ይገባሉ። መረዳጃ ማሕበር ከሆነ አገልጋይ ሆነው ይጠጋሉ። ቤተክርስቲያን ከሆነ ደግሞ ሻሽ ጠምጥመው እንደቄስ ይገባሉ። እነኝህን ታዲያ አውሬ አትላቸው ወይ የቤት እንስሳ፣ በእውነት ከባድ ፍጥረቶች ናቸው። አንዴ ከነከሱህ ደግሞ ጥርሳቸው መርዝ ነው፡፡ ከሞላው ሕብረተሰቡ ጋር ያቆራርጡሐል። ጐተራው ጋ ለመድረስ ሲገቡ በዲሞክራሲ መልክ እርስ በእርሳቸው ተመራርጠው ይገባሉ። ከዛ በኋላ በሕብረተሰቡ ፊት አሳቢ፣ ሰብሳቢ፣ ተቆርቋሪ፣ ጨዋ፣ ጭምት፣ አገልጋይ መስለው ይታያሉ።

ስለዚህ እነሱን ብቻዬን ሆኜ እቋቋማቸዋለሁ ማለት ዘበት ነው። አይጦችን ለማጥፋት ይቻላል። በመጀመሪያ ሰፋ ያለ ጥናት ያስፈልጋል። ከዛ በኋላ በማሕበሩ ጐተራ አጠገብ ያሉትን አይጦች ጅራታቸውን እየጐተቱ ውጪ አውጥቶ መጣል። ወይም ዲዲቲ እፊታቸው ላይ እየነፉ ሙልጭ አድርጐ ማስወጣት፡፡ በአንዳንድ አሜሪካን ከተማዎች እንደምንሰማው ከሆነ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ታላቅ እርምጃ እያደረጉ ነው። በሳንሆዜ፣ በአትላንታ፣ እንዲሁም በቺካጐ አይጦች እንዳይገቡ መሠረታቸውን አጠንክረውታል። የእናንተስ ማሕበር እንዴት ነው? ምናልባት ለብዙ አመታቶች ስትበዘበዙ ስለኖራችሁ፤ ሰውነታችሁ ደንዝዞ ችላ ብላችሁታል። አይጦች እንደሆን ወይ አያድጉ ወይ አያሳድጉ ለሕብረተሰብ ጠር ናቸው። በዛ ቢል የእነሱ እድገት፤ ይህንን የተሰበሰበውን አረንጓዴ ቅጠሎች ይበሉና ሆዳቸው ወጠርጠር ጅራታቸው ደግሞ ሰፋ ሰፋ ይላል። የእነሱን ጠር አዲተሮች ማለትም ድመቶች በጐን ማቋቋም ነው። ወይም እነሱን መሰል ወጥመድ በጐተራው አጠገብ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። □

## «ከሕግ አስከባሪ ጠንቀቅ እንበል»

(ከዘውዱ መለሠ)

በዚህ ባለንበት አገር ፖሊሶች ሰውን ማንገላታት ከፈለጉ፣ ብዙ ምክንያቶች አቅርበው ሊጐዱ ይችላሉ። የአገሬው መንግሥትም ዱላ፣ ሽጉጥ፣ አይን ላይ የሚቢተን የመርዝ ጢስ ሳይቀር አስታጥቋቸዋል። በዚህ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ በተለይ ለአዲስ መጪዎች የሚሆን ጠቃሚ ምክሮችን እነሆ እላለሁ።

1ኛ) በምሽት መኪናህን ይዘህ ከመውጣትህ በፊት ለ3 ደቂቃዎች የግራና የቀኝ ምልክቶች መሥራታቸውን መመርመር፣ እንዲሁም የፊትና የኋላ መብራቶች ተቃጥለው እንዳይሆን ማየት ያስፈልጋል። በእነኝህ ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያት አድርጐ ፖሊስ እንዳያስቆምህ ተዘጋጅተህ ብትወጣ ጥሩ ነው።

2ኛ) ድንገት ያስቆሙህ እንደሆን ባለህበት እርፈህ ተቀመጥ፡፡ ፖሊሱ እንድትከፍት እስከሚጠይቅህ ድረስ ለመውጣትም ሆነ የጐን መስተዋቱን ለማውረድ አትሞክር። ምክንያቱም እንደቆምክ ንቅናቄ ካየ፣ መሣሪያ የምታወጣ መስሎት ሊተኩስብህ ይችላልና።

3ኛ) ለጠየቀህ ጉዳይ ሰላማዊ በሆነ አነጋገር መልስ መስጠት ይገባል። ነገር ግን በየጊዜው (SIR) ሰር! ማለት አያስፈልግም፡፡ የፍራቻ መልክ ካሳየኸው፣ የደበቅከው ነገር አለ በማለት የጠበቀ ፍተሻ እንዲያደርግ ያስገድደዋል።

4ኛ) ከመሸ ወዲያ ጨለም ባለበት መንገድ አትንዳ። በተቻለ መጠን ተሽከርካሪ መኪናዎች በበዙበት፣ ብርሐን ባለበት በኩል ቢሆን የተሻለ ነው። ምክንያቱም አሳፊ አግዳሚው ታዛቢ ስለሚሆን ፖሊሶቹ ሕገወጥ ተግባሮች እንዳይሰሩ ያደርጋቸዋል።

5ኛ) በምሽት ከሠርግ ወይም ከግብዣ ቦታ ሥ ርዓቱ አልቆ ሰው ሲበተን ብቻህን ባትጓዝ ጥሩ ነው። ቢቻል በቤትህ አቅራቢያ የሚኖሩ ፈልገህ እየተከታተልክ ብትነዳ ይሻላል። በድንገት ፖሊስ አንደኛውን ቢያቆመው፣ አልፈኸው አትሒድ። ጥግ ይዘህ አቁመህ መመልከት ትልቅ እርዳታ ነው። ነገር ግን አንተና ጓደኞችህ ከመኪናችሁ ወርዳችሁ ፖሊሱን ማዋከብ ጥፋት ነው። ሕግ አስከባሪው ግራ ከተጋባ፣ በራዲዮ መገናኛው እርዱኝ ብሎ ጠቅላላ የፖሊስ ሠራዊቱን ሊጠራ ይችላል። ስለዚህ ጓደኛህን እረዳለሁ ብለህ ከጥቅምህ ጉዳትህ የበዛ ይሆናልና ባለህበት ሆነው ሁኔታውን መከታተሉ የተሻለ ነው።

ምክሬን በጥያቄ ላብቃ— ለምንድነው ፖሊስ ከተኩሰ በአንድ ጥይት የማይቆመው? መልሱ ከሕክምና ሒሳብ ነፃ ለመውጣት፤ ከጀመርክ መጨረስ አለብህ የሚል አስተሳሰብ ስላላቸው ነው ይባላል። እና ይህ እንዳይደርስ ጠንቀቅ እንበል እላለሁ። □

## ዜና ቤተክርስትያናት

# ኮሎምበስ (ኦሃዮ)

በኮሎምበስ ኦሃዮ በሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች የራሳቸውን ሕንፃ በመግዛት ያቋቋሙትን የመድኃኒያለም ቤተክርስቲያን፤ከተለያዩ ስቴቶች የተጋበዙ ካህናት፤ መዘምራንና ምዕመናን በተገኙበት ባለፈው ወር በብፁዓን ጳጳሳት አስባርከው፤በታላቅ ድምቀት የምረቃ በዓላቸውን ማክበራቸው ታውቋል። የደብሩ አለቃ መላከ ሰላም ሲሳይ ይመር ናቸው።







# እኔ የምለው !

ከውሂብ ጥሩነህ

## ወፈር አበጥ ያለ ንቀት

እንዴት አላችሁሳ? ለመሆኑ ይሄ እንደሆሊፊልድ ጥርስ የሚያንገጫግጭ የሰው ሃገር ብርድ እንዴት ይዟችኋል? (‘ብርድ ወደ ሽቦነት የቀየረው ከንፈሬ ከንፈር ሲሆን እነግርሃለሁ!’ እንዳትሉኝ ብቻ!!) ድሮ አስቴር አወቀ ዘፈን ስታወጣ ወይና ደጋ አገር በጋቢ ተሸፍኖ “ምን ታለቃቅሳለች?” እያለ ይቆጣ የነበረ ጉበዝ አትላንቲክን ተሻግሮ “ብርድ ያለበት” አገር ጉጆ ከቀለሰ ወዲህ በቀጭን ድምፅ አብሯት ማንጎራጎር ጀምሯል አሉ ... “እትትት ..ትት” የሚለውን ዘፈን!!

የብርዱን ነገር (ከተገኘች ለሚስት ካልሆነም ለደህና ብርድ ልብስ) ግን ... ይሄ ወሰን እያጣ የመጣውና ሽጉጥ የሚያማዝዘው የአበሾች መናናቅ ነገር ግን መፍትሔው ምን ይሆን? (‘አንተን ብሎ መፍትሔ ፈላጊ!’ ብላችሁ በንቀት አይነት ስድብ እንዳትጀምሩኝ ብቻ ... አደራ!)

እውነት ግን ... ይቺ የመናናቅ ነገር እኮ ከአበሾች ጋር በሽ ነች!! ከቆንጆዬ ጋር ሲምነሸነሽ የከረመ ጉረምሳ ቀን ተቀይሮ ‘ብርድ ቢመታው’ “መለያየት ያለ ነው! ጥሩ ልጅ ነበረች!” የሚል እንዳይመስላችሁ!! “ያለእኩያዬ ራሴን ዝቅ አድርጌ እንደለማዳ ቡችላ ስከተላት የከረምኩት፣ ጥፋተኛው እኔ ነኝ! እንዴት የዚች ‘እንትን’ መጫወቻ ስሆን ልከረም!” እያለ ጆሮውን ለሰጠው ሰው ሁሉ ሲያናንቃት ትሰሙታላችሁ፤ ታዲያ “ዓይንህን አያሳየኝ!” ብላ የተሰናበተችው ቆንጆም ዝም ብላ የምትታማ እንዳይመስላችሁ! እሷም በበኩሏ ባልንጀሮቿን ትሰበስብና በቃ ... እንዳይሞት እንዳይተርፍ አድርጋ ‘ታናንቀዋለች’!! “ለማንም የሰፈር ኩታራ ልቤን ሰጥቼ በገዛ እጄ የሰው መሣቂያ ሆንኩ! ዕድሜ ለእኔ ይበል ... ከምግብ አበላል እስከልብስ አለባበስ የጨዋ ደምብ አስተምሬ ሰው ባደርገው ቀን አልፎለት ቁልቁል ያየኝ ጀመር! ‘ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይፀድቃል’ አሉ!” እያለች ስትወርድበት ብትሰሙ እንዲህ የሚናናቁ ሰዎች ለበርካታ ወራት “ተፋቅረው” መክረማቸው ግራ ይገባችኋል። ‘ከእኔና አንቺ በቀር እነማን ነበሩ ...’ በሚለው መከራውን ባየ ዘፈን ብርድ ሲከላከሉ ከርሞ እንዲህ መናናቅ ግን ትንሽ አይገርምም ወይ?

ትምህርት ቤት ከርሞ ዲግሪ ቢጤ የያዘው ትምህርት ሲሉት የሚያመውን፣ ደህና ገንዘብ ያለው “አረ ገንዘብ አጣሁ” እያለ የሚያማርረውን፣ ‘ዘናጭ’ መኪና የሚነዳው ‘የሆነች ቆርቆሮ’ የሚጉትተውን፣ ቆንጆዬ ሚስት ያለው እንኳንስ ሚስት ውሻ ማልመድ ያቃተውን፣ ሃይማኖተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ‘የተቀያየመ’ የሚመስለውን፣ ቀዩ አበሻ ጠየም ያለውን፣ አፍሮው ራሰ በራውን፣ ረጅሙ አጠር ያለውን፣ የከተማው ልጅ የባላገሩን አበሻ ይንቀዋል ... ይሄ ሁሉ መናናቅ እኮ እንግዲህ በሰው ሃገር ነው!!

የሆነ ድግስ ቤት ቁጭ ብላችሁ የቀረበላችሁን እህል ውሃ ታጣጥማላችሁ እንበል። ጆሮ መቼም (ይሄ የሚያቆረፍድ ብርድ ካላገኘው በስተቀር) አይሰማው የለምና አጠገባችሁ ቁጭ ብለው የደራ ወሬ የያዙና በቆንጆ ሽቶ የታወዱ ሁለት ሴቶች የሚያወሩትን ነገር በደምብ ትሰማላችሁ። ነገሩ የደህናም ወሬ አይደል ... ሐሜት ቢጤ ነው ... ንቀት የሞላበት ሐሜት!!

“ያቺ ከእንትና ጋር ቀይ ቀሚስ ለብሳ ቁጭ ያለችው የእንትና እህት አይደለችም ወይ?” ... ትጠይቃለች አንዷ!

“ወይኔ አንቺ! ... እሷው ናት! ... ምን አከላለች በእናትሽ? ... ማይ ጋድ!! ...” ትመልሳለች ሌላኛዋ!

“በጤናዋ ነው ወይስ ስትበላ እየዋለች ነው? ልትፈነዳ ደርሳለች እኮ!” ትላለች የመጀመሪያዋ!

“አሁን ባለፈው አንድ አረንጓዴ ሸሚዝ በቢጫ ሱሪና በነጭ ጫማ የሚያደርግ ባላገር ቦይፍሬንድ ይዛ ብጥስጥስ ማለት ጀምራ ነበር! እሱም ባቅሙ ኮርቶባት ነው መሰለኝ ሰው የተሰበሰበበት ቦታ እኮ አብሯት አይታይም!” ትመልሳለች ሌላኛዋ!

“አጅሪት እኮ የምታርፍ እንዳይመስልሽ! ከጥቁሮች ጋር ሁሉ ትወጣለች ብላ ማናት ነግራኝ ነበረ!” ትላለች የመጀመሪያዋ!

“ታዲያ ያረገዘች ላም መስላ ማን ደህና አበሻ ይጠጋታል? እንዲህም ሆና ግን ስትበጣጠስ እኮ በቃ ... ትንሽ ቀጠን ብትል ኖሮማ አታስቀምጠንም ነበር!”

ይሄኔ ነው ሴትዮዋን በጥቅሻ ጠርታችሁ ... በቃ .. “ስሞትልሽ! እንዴ ውደቂባቸው!” ለማለት የሚከጅላችሁ!! አሁን ሰው ወፈረ ተብሎ አርፎ በተቀመጠበት እንዴት ይሄ ሁሉ ስድብ ይወርድበታል? ታዲያ ይቺ ‘የንቀት ሐሜት’ ያለቀች እንዳይመስላችሁ!

“ያቺ ከእንትና ጋር አፍ ለአፍ ገጥማ ቁጭ ያለችው ልጅ ማናት? ... ወንድ አግኝታ እኮ ልቧ ወልቋል!” ትቀጥላለች የመጀመሪያዋ!

“አዲስ ናት መሰለኝ ... አይቻት አላውቅም!” ትመልሳለች ሌላኛዋ።

“ከሌላ ስቴት የመጣች የዋህ መሆን አለባት እንጂ እዚህ ከተማ የኖረች ሴት ‘እንትናን’ ወንድ ብላ አብራው አደባባይ አትታይም ነበር!” ትላለች የመጀመሪያዋ!

"እሱ ግን ... ወይ አይሠራ ወይ አይማር ... ለመሆኑ ገንዘቡን ከየት እያመጣ ነው ቀሚስ ለብሳ ባጠገቡ ላለፈችው ሁሉ በየሣምንቱ ውስኪ የሚያወርደው?" "ምን አገባሽ?" ለማለት ይከጅላችሁና ... በቃ ቆሽታችሁ እንዳረረ ከእነዚህ 'የእፍፍ ኮሌጅ' ምሩቆች አካባቢ ጥፍት ለማለት ትነሳላችሁ!! እንዲህ ያለ 'ወፍራም' ንቀት ግን አይገርምም ወይ?

ሌላ ደግሞ አለላችሁ ... የወንድ ሐሜተኛ!! እሱ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ ስለሆነ ብቻ "አውደልዳይ" ባልንጀሮቹን ሁሉ በንቀት የሚያማ!! "እገሌ ሲጠይቅህ ነበር!" የሚል አይነት የናፍቆት መልዕክት ቢሰማ "እኔ እኮ ትምህርቴን ትቼ ከአዳሚ ጋር መንደር ለመንደር የምዞርበት ጊዜ የለኝም! ሥራ ፈት ሁላ!!" የሚል ቁጣ ያዘለ መልስ የሚሰጥ!! ይሄ ታዲያ በሰላሙ ጊዜ ነው! 'ሥራ ፈት' ከሆኑት ጓደኞቹ ከአንዱ ጋር በሆነ ነገር የተቀያየመ ለታ ስልክ ይደውልና ... በቃ በንቀት የተሞላ መልዕክት ይተውለታል ...

"አጅሬው! ስማኝ! ድሮም እኮ አገር ሰፈሩ ልጁ ወመኔ ነው! አገር ያሰለቸ ወሬኛ፣ 'ሲ ኤን ኤን' ነው! ከእሱ ጋር ጓደኝነት ይቅርብህ! ደረጃችሁ አንድ አይደለም እያለ ሲመክረኝ አልሰማ ብዬ ጓደኛዬ ያደረግኩህ ጥፋተኛው እኔ ነኝ! ትምህርት በዝቶብኝ ከአበሻ ሠፈር ብጠፋ ስሜን ከነዛ የማድቤት ጓደኞችህ ጋር ሆነህ ታብጠለጥለዋለህ አሉ። የእኔ ወንድም! ከነጓደኞችህ በቅናት ተንጨርጭረህ ከምትሞት ተመክረህ ተመክረህ አልሰማ ያልከውን ምክር ደግሜ ልምከርህ ... የወሬ ስልቻህን ለባልንጀሮችህ በአደራ ስጥና ትምህርት ቤት ገብተህ ሰው ለመሆን ሞክር! የቤተሰብህንም የአገራችንንም ስም በሰው ሃገር በክፉ ባታስነሳው መልካም ነው! በኋላ ቀን ጨልሞብህ በአንድ ዓይንህ ስታለቅስ እንዳላይህ ብቻ ... ዋ!" ይለዋል ... ጉርንን ባለ ድምፅ!!

ይሄ የአበሾች መናናቅ ታዲያ ሃይማኖተኞችም ጋ አልፎ አልፎ ይታያል። እግዚአብሔር "በዓለም ዙሪያ ቃሌን ሳይሆን የሌላውን ሃይማኖት ቆሻሻነት ስበኩ!" ያለ ይመስል አንዳንዱ "ሃይማኖተኛ" የሌላውን ሃይማኖት እያናናቀ ሲያማ እግዚአብሔር "አደራህን! ልክ ልካቸውን ንገርልኝ!" ያለው ይመስላል።

"የዛኛው ሃይማኖት መሪዎች እኮ አባሎቻቸውን ጥቁር ልብስ አልብሰው ወደገሃነም ለመላክ ከሰይጣን ጋር ውል ተፈራርመዋል ይባላል። እንደውም አሁን በቅርብ ቀን ሰይጣን ራሱ በሰባኪ ተመስሎ ከቤተክርስቲያኑ አባላት ገንዘብ ይሰበስብ እንደነበር ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ቁጭ ብሎ ነገሩን ባይኑ ያየ ሰው ምሎ ነው የነገረኝ! እኔ የሚያሳዝኑኝ እነዚህ ሳያውቁት በገዛ ገንዘባቸው ገሃነም ውስጥ ቪላ ቤት የተገዛላቸው ምስኪኖች ናቸው። 'ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛው መንገድ የእኛ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው' ብለን ደጋግመን ነግረናቸው አልሰማ ብለዋል። የቀራቸው ነገር ቢኖር እንግዲህ በቅርብ ቀን በአሮጌ አውቶቢስ ተጭነው ወደገሃነም መጓዝ ብቻ ነው! ሰው እንዴት ..."

አንዴ ይህንን "የንቀት ሰበካ" አቋርጬ ደህና እንክረም ብላችሁስ?



# በኮምፒውተር
# የአማርኛና የእንግሊዝኛ ሥራዎች


## መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣ ወይም የተለያዩ የአማርኛ ጽሑፎችን በኮምፒውተር ለማሠራት ለምትፈልጉ ሁሉ!!

ርካሽ በሆነ ዋጋ ከጥራት ጋር ማንኛውም ዓይነት ጽሑፍ
በአስቸኳይ ለማሠራት የምትፈልጉ ሁሉ
በስልክ ቁጥር (404) 508-4657 ደውለው ገነትን ያነጋግሩ።
ጽሑፎችዎንም በፋክስ ቁጥር (404) 508-2447 መላክ ይችላሉ።
ማስታወቂያዎች፣ የትርጉም ሥራዎች፣ የመጣጥፍ ረቂቆች፣
የጥሪ ካርዶች በፈለጉት ዲዛይን እንሠራለን።
የእንግሊዝኛ ጽሑፎችንም በማዘጋጀት
በአስቸኳይ በኢ ሜይል ለመላክ እንችላለን። ደውሉልን።

# ቃላት በሰንጠረዥ

የጥቅምት ወር ሰንጠረዥ መልስ በትክክል የላኩልን አቶ ታጠቅ ውብሸት ከዋሽንግተን ዲሲ ብቻ ናቸው። በተከታታይ አምስት ሰንጠረዦችን በትክክል መልሱን ለሚልኩልን የ3 እትም ነፃ ሽልማት እንሰጣለን።





## ወደ ጐን

1. የአገራችን የጠጠር ጨዋታ
4. ዓፈ
7. መናገሪያ
9. ጠየቃት
14. የወታደር ማዕረግ
19. የሰውነት ክፍል
21. የድሮ ጠመንጃ
27. የእንጨት ወለል
31. ሊወለድ ሲል
33. ሸፍን
38. ሲያበቃ
43. ደግነት
47. ችግኝ
49. አንድና አንድ
52. ንጋት
56. ጠፍ ሆነ (ተቃራኒው)
58. ከባድ መኪና
62. መጠሪያ
64. ትቀቀል
68. በእግሩ ቆመበት
71. ችክ
74. ማንገራገር

## ወደታች

1. ዘወር
2. በመቅደድ
3. የኢትዮጵያ ሐይቅ
5. ተጋራት
6. የወያኔ አለቃ
7. የክህነት ማዕረግ
8. የድሮ ሽጉጥ
13. ከቁም ነገር አትቆጠርም
16. ከየቦታው የተለቃቀመ
28. ትንቢት
32. የእጅ ሥራ
33. ተመለከትኩለት
37. እህል
41. የእግር አጥንት
46. የአዳም ሚስት
50. ለመቀወስ
54. ትስማማ
58. የትንሽ ተቃራኒ
62. ውሃ ሲያስፈልገኝ
66. መሬት ውስጥ የሚውል የአዝዕርት ክፍል
69. ጠነባ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።

| | 12 ISSUES | 6 ISSUES |
|---|---|---|
| U.S. | $30.00 ☐ | $16.00 ☐ |
| Canada | $40.00 ☐ | $22.00 ☐ |
| Europe | $56.00 ☐ | $30.00 ☐ |
| Asia | $70.00 ☐ | $38.00 ☐ |
| Institutions | $80.00 ☐ | $40.00 ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* ____________________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* ____________________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*




# ናዝሬት ምግብ ቤት

## NAZARETH RESTAURANT

*Authentic Ethiopian Cusine*
5291 Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083

በቅርቡ የተከፈተው
የናዝሬት የአገር ባህል ምግብ ቤት
የተሟላ የባር አገልግሎት አለው።
ዓርብና ቅዳሜና እሁድ ምሽቶች
የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።

እንኳን ለብርሃን ልደቱና ለፈረንጆችአዲሱ
ዓመት በሰላም አደረሳችሁ እያልን መልካም
ምኞታችንን እንገልጻለን።



ና
ዝ
ሬ
ት

የአገርን ትዝታ የሚቀሰቅስ የባህል ምግብ ተመግቦ ምሽቱን
ከአገር ልጆች ጋር ለማሳለፍ የናዝሬት ምግብ ቤት አለላችሁ።



ብቅ ብላችሁ ጎብኙን!!
በመስተንግዷችን ትደሰታላችሁ!!
በምግባችን ጣዕምን ትረካላችሁ!!

Phone: (404) 294-0043

**NEVER UNDERESTIMATE THE MIND OF AN ETHIOPIAN... or what he or she can do when given the freedom to be creative!!**

**⇩ This could be your business card ⇩**

**MicroMall 2000**
**THE FUTURE IS NOW**

**LOUL ASFAW**
Senior Managing Partner

(770) 991-6002 • Fax (770) 991-9533 • Toll Free (888) 6-INCOME
908 Forest Pond Drive • Marietta, GA 30068
An affiliate of MicroMall U.S.A.

**MicroMall 2000**
**THE FUTURE IS NOW**

**KIDANE TEGEGNE**
Independent Managing Partner

(214) 373-4813 • Fax (214) 373-4318 • Toll Free (888) 6-INCOME
P.O. Box 823634 • Dallas, TX 75382
An affiliate of MicroMall U.S.A.

## The result is an unparalleled business opportunity in America: The first of its kind... A HOME-BASED MALL

# MicroMall 2000 ™

**A revolutionary home-based business which provides proven solutions to many of America's problems. In the meantime, it gives you the opportunity to achieve the total financial freedom that you deserve**

**Friends...** the world is in the midst of the information revolution, and MicroMall 2000 is right in the front line. The education you once had is no longer enough to keep you competitive. You need to keep up with the changes. We are inviting you to join us in the revolution and become well informed and knowledgeable while earning high five and six figure income from diversified sources right away.

If you feel like you are trapped in an unsatisfying profession or in a dead-end job, let us show you the way out to a magnificent career that you will be proud of.

***MicroMall 2000 is:***

- *A business owned 100% by you, with Ethiopian and American partners to assist you every step of the way.*
- *A business you can run from almost anywhere and earn more money than you ever dreamed.*
- *A business which does not require large start-up capital, that you can do full or part time.*
- *A business that provides on-going support and training and offers a no risk guarantee.*

**We are looking for a few good associates and partners who have a serious interest in making money in their own business by following our proven step-by-step plan. WE ARE NOT INTERESTED IN YOUR MONEY! WE ARE INTERESTED IN GETTING THIS LIFE CHANGING INFORMATION IN YOUR HANDS SO THAT YOU CAN START MAKING MONEY IMMEDIATELY! TAKE ACTION NOW!!!**

**Name:** ______________________ **Home Phone:** ______________

**Address:** ______________________ **Work Phone:** ______________

**City/State/Zip Code:** ______________________

**Special Offer** — If you join now, you will receive a FREE training kit on "The Science of Getting Rich"

**Fax this form or call:**

**(770) 991-6002 or Toll Free (888) 646-2663 or (888) 6-INCOME Fax (770) 991-9533**
**If you live in Atlanta, Dallas, Washington D.C., Los Angeles, or the Bay Area, MicroMall 2000 will be happy to set you up in your new business right away!**

***MicroMall 2000™*** - **P.O. Box 78033, Atlanta, GA**